# መጽሐፈ ኢያሱ

## መግቢያ

መጽሐፈ ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ በሙሴ እግር ተተክቶ በተሾመው በኢያሱ መሪነት በጦርነት ድል ነሥተው ከነዓንን እንዴት እንደያዙ የሚገልጠውን ታሪክ ይዞአል ፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተመዘገቡት ታላላቅ ታሪኮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፦ የዮርዳኖስን ወንዝ ስለ መሻገር ፥ ስለ ኢያሪኮ ግንብ መፍረስ ፥ በዐይ ስለተደረገው ጦርነትና ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ስለማደሳቸው የሚናገሩት ናቸው ። በመጽሐፉ ውስጥ በጣም ታዋቂ ከሆኑት ክፍሎች አንዱ "የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ ፤ እኔና ቤተሰቤ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን" የሚለው ነው ። (24፥15)

---

## ምዕራፍ 1

### ድል ነሥቶ የከነዓንን ምድር ስለ መውረስ እግዚአብሔር ለኢያሱ የሰጠው ትእዛዝ

1 የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ከሞተ
በኋላ ፥ የሙሴ የቅርብ ረዳት የነበረውን የነዌን
ልጅ ኢያሱን እግዚአብሔር እንዲህ ሲል አነጋገ
ረው ፤ 2 "እነሆ ፥ አገልጋዬ ሙሴ ሞቶአል ፤
እንግዲህ አንተና የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ተዘ
ጋጁ ፤ እኔ ወደማወርሳችሁም ምድር ለመግባት
የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ ። 3 ለሙሴ በነገር
ሁት መሠረት በምትዘምቱበት ጊዜ በእግራችሁ
የምትረግጡትን ምድር በአጠቃላይ ለእናንተ
ሰጥቼአለሁ ። 4 ድንበራችሁም በስተደቡብ
በኩል ካለው በረሓ ተነሥቶ ፥ በስተሰሜን እስከ
ሚገኙት እስከ ሊባኖስ ተራራዎች ይደርሳል ፤
በስተምሥራቅ ከታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ በመነ
ሣት የሒታውያንን አገር አልፎ ፥ በስተ ምዕ
ራብ በኩል እስከሚገኘው እስከ ሜድትራኒያን
ባሕር ይደርሳል ። 5 አንተ ኢያሱ ፥ በምትኖር
በት ዘመን ሁሉ አንተን ተቋቁሞ ድል የሚነ
ሣህ ማንም አይኖርም ፤ እኔ ከሙሴ ጋር እንደነ
በርሁ ከአንተም ጋር እሆናለሁ ፤ ሁልጊዜም
ከአንተ ጋር ነኝ ፤ ከቶም አልተውህም ፤ 6 አይ
ዞህ! በርታ! እኔ ለቀድሞ አባቶቻቸው ልሰጣ
ቸው ቃል የገባሁላቸውን ምድር ለማውረስ ለእ
ነዚህ ሕዝብ መሪ ትሆናለህ ። 7 አንተ ብቻ አይ
ዞህ! በርታ! አገልጋዬ ሙሴ ለሰጠህም ሕግ
ሁሉ እውነተኛ ታዛዥ ሁን ፤ በምትሄድበት
ስፍራ ሁሉ ማናቸውም ነገር እንዲከናወንልህ
ከዚህ ሕግ ከቶ ዝንፍ አትበል ፤ 8 ይህን የሕግ
መጽሐፍ ምን ጊዜም ከማንበብ አትቈጠብ ፤
በእርሱ የተጻፈውን ሁሉ መፈጸም ትችል ዘንድ
እርሱን ሌሊትና ቀን አሰላስለው ፤ ይህንን ብታ
ደርግ ሁሉ ነገር በተቃና ሁኔታ ይከናወንል
ሃል ። 9 'አይዞህ! በርታ!' ብዬ ያዘዝኩህን አስ
ታውስ ፤ ከቶ አትፍራ ፤ ተስፋም አትቍረጥ ፤
ምክንያቱም በምትሄድበት ስፍራ ሁሉ እኔ እግ
ዚአብሔር አምላክህ ከአንተ ጋር ነኝ ።"

### ኢያሱ ለሕዝቡ ትእዛዝ ሰጠ

10 ከዚህ በኋላ ኢያሱ የሕዝቡን አለቆች እን
ዲህ ብሎ አዘዘ ፥ 11 "ወደ ሰፈር ገብታችሁ
ሕዝቡን 'ስንቃችሁን አዘጋጁ ፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር አምላካችሁ የሚሰጣችሁን
ምድር ለመውረስ በሦስት ቀን ውስጥ የዮርዳኖ
ስን ወንዝ ትሻገራላችሁ' ብላችሁ ንገሩ ።"
12 ኢያሱ የሮቤልንና የጋድን ነገዶች ፥ እንዲ
ሁም የምናሴን ነገድ እኩሌታ እንዲህ አላ
ቸው ፥ 13 "እግዚአብሔር አምላካችሁ እዚህ
ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ያለውን ምድር ለእና
ንተ መኖሪያ አድርጎ የሚሰጣችሁ መሆኑን የእ
ግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ የነገራችሁን አስታ
ውሱ ። 14 ሚስቶቻችሁ ፥ ልጆቻችሁና ከብቶቻ
ችሁ በዚህ ይቆዩ ፤ የጦር ልብስ ለብሰው ለው
ጊያ የተዘጋጁ ሰዎቻችሁ ግን ወገኖቻቸውን እስ
ራኤላውያንን ለመርዳት ግንባር ቀደም ሆነው
ዮርዳኖስን ይሻገሩ ፤ 15 እግዚአብሔር አምላካ
ቸው የሰጣቸውን በምዕራብ በኩል ከዮርዳኖስ
ማዶ ያለውን ምድር እስከሚወርሱም ድረስ
አብረው ይዝመቱ ፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ

---

1፥3-5 ፦ ዘዳ. 11፥24-25 ። 1፥5 ፦ ዘዳ. 31፥6 ፥8 ፤ ዕብ. 13፥5 ። 1፥6 ፦ ዘዳ. 31፥6 ፥7 ፥23 ።
1፥12-15 ፦ ዘኍ. 32፥28-32 ፤ ዘዳ. 3፥18 ፤ ኢያሱ 22፥1-6 ።

መብላት ከጀመሩበት ቀን ማግሥት እንሥቶ
መና መዝነሙን አቋረጠ፤ እስራኤላውያንም
ከዚያን በኋላ ያን መና ማግኘት አልቻሉም፤
ከዚያን ጊዜ አንሥቶ በከነዓን የበቀለውን እህል
መብላት ጀመሩ።

### ኢያሱና ሰይፍ የያዘው ጐልማሳ

13 ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ሰይፍ የያዘ
አንድ ጐልማሳ በድንገት በፊቱ ቆሞ ታየው፤
ኢያሱም ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ “አንተ የእኛ
ሰው ነህ ወይስ የጠላቶቻችን ወገን?” አለው።
14 ጐልማሳውም “የእናንተም ሆነ የጠላት
ወገን አይደለሁም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር
ሠራዊት አዛዥ እንደመሆኔ መጠን እነሆ መጥ
ቻለሁ” አለ።
ኢያሱም ወደ መሬት ወድቆ ሰገደለትና
“ጌታዬ ሆይ! እኔ አገልጋይህ ነኝ፤ ምን ልታ
ዘዝ?” አለው።
15 የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥም “የቆም
ከባት ምድር የተቀደሰች ስለሆነች ጫማህን
አውልቅ” አለው፤ ኢያሱም እርሱ እንዳዘዘው
አደረገ።

## ምዕራፍ 6

### የኢያሪኮ አወዳደቅ

1 እስራኤላውያንን ከመፍራት የተነሣ የኢያ
ሪኮ ቅጽር በሮች ተዘግተው በዘብ ይጠበቁ
ነበር፤ ወደ ከተማይቱ መግባትም ሆነ መው
ጣት የሚችል ማንም አልነበረም፤ 2 እግዚአብ
ሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፦ “ኢያሪኮን ከንጉ
ሥዋና ከጀግኖች ወታደሮችዋ ጋር በእጅህ አሳ
ልፌ እሰጥሃለሁ፤ 3 አንተና ወታደሮችህ እስከ
ስድስት ቀን ድረስ በቀን አንድ ጊዜ የከተማይ
ቱን ቅጽር በሰልፍ ትዞሩአታላችሁ። 4 እያንዳን
ዳቸው መለከት የያዙ ሰባት ካህናት ከቃል
ኪዳኑ ታቦት ፊት ቀድመው ይሂዱ፤ በሰባተ
ኛው ቀን ካህናቱ ቀንደ መለከት እየነፉ አንተና
ወታደሮችህ ከተማይቱን በቀን ሰባት ጊዜ ትዞሩ
አታላችሁ፤ 5 ከዚያን በኋላ ካህናቱ በቀንደ መለ
ከታቸው ከፍተኛ ድምፅ እንዲሰማ ያድርጉ፤
እርሱንም እንደሰማችሁ ወዲያውኑ ሰዎቹ ሁሉ
በከፍተኛ ድምፅ በመጮኽ ይደንፉ፤ የከተማይ
ቱም ቅጽር ይፈርሳል፤ ከዚህም በኋላ መላው
ሠራዊት ወደ ከተማይቱ ሰተት ብሎ በቀጥታ
ይግባ።”
6 ኢያሱም ካህናቱን ጠርቶ “የቃል ኪዳኑን
ታቦት ተሸከሙ፤ ከእናንተም ሰባታችሁ መለ
ከት ይዛችሁ ከታቦቱ ፊት በመቅደም ሂዱ።”
7 ከእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ፊት ግን
ባር ቀደም ሆኖ የአንድ ዘብ ጠባቂ ሰልፍ ሲያ
መራ ሠራዊቱ ከተማይቱን በሰልፍ እንዲዞር
ኢያሱ ትእዛዝ ሰጠ።
8-9 ኢያሱ በሰጠውም ትእዛዝ መሠረት፥
ቀንደ መለከት ከሚነፉት ካህናት ፊት ግንባር
ቀደም የሆነው ዘብ ጠባቂ ሰልፈኛ አለፈ፤ ከእነ
ርሱም በኋላ የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት
ካህናት ከኋላ ደጀን በሆነ ሰልፈኛ ተጠብቀው
ተጓዙ፤ በዚህም ጊዜ ሁሉ የመለከቶቹ ድምፅ
ይሰማ ነበር፤ 10 ኢያሱ ምልክት እስከሚሰጥበት
ጊዜ ድረስ ሠራዊቱ እንዳይጮኹ፥ አንድም
ቃል እንዳይናገሩ አዘዘ። 11 ይህም ሰልፍ ከቃል
ኪዳኑ ታቦት ጋር ከተማይቱን አንድ ጊዜ እንዲ
ዞር አደረገ፤ ከዚያም በኋላ ወደ ሰፈር ተመል
ሰው አዳር በዚያው ሆነ።
12-13 በማግሥቱም ኢያሱ በማለዳ ተነሣ፤
ባለፈው ቀን በተደረገው ዐይነት በዘብ ጥበቃው
ሰልፍ ተቀዳሚነት ሰባቱ ካህናት የመለከት
ድምፅ እያሰሙ፥ ካህናቱና ወታደሮቹ ከተማይ
ቱን ለሁለተኛ ጊዜ ዞሩ፤ ከዚያም በኋላ የቃል
ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናትና የኋላ
ደጀን የሆነው ሰልፍ አለፈ፤ በዚህም ጊዜ ሁሉ
የመለከቶቹ ድምፅ ይሰማ ነበር። 14 በዚህም
በሁለተኛው ቀን ከተማይቱን አንድ ጊዜ ዞረው
ወደ ሰፈር ተመለሱ፤ እስከ ስድስት ቀንም
በዚሁ ዐይነት አደረጉ።
15 በሰባተኛው ቀን ጎሕ ሲቀድ ማልደው
ተነሥተው በዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ከተማይ
ቱን ሰባት ጊዜ ዞሩአት፤ ከተማይቱን ሰባት
ጊዜ የዞሩበት ቀን ያ ብቻ ነበር። 16 በሰባተ
ኛው ዙር ካህናቱ መለከት ሊነፉ በሚዘጋጁ
በት ጊዜ ወታደሮቹ ድምፃቸውን ከፍ አድር
ገው እንዲደነፉ ኢያሱ እንዲህ የሚል ትእዛዝ
ሰጠ፦ “እግዚአብሔር ከተማይቱን አሳልፎ ሰጥ
ቶአችኋል፤ 17 በከተማይቱና በውስጡ ያለው
ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር እንደሚቀርብ መሥ
ዋዕት ሆኖ መደምሰስ አለበት፤ መትረፍ የሚገ
ባቸው ጋለሞታይቱ ረዓብና ከእርስዋ ጋር በቤ
ትዋ ያሉት ብቻ ናቸው፤ ምክንያቱም እርስዋ
ሰላዮቻችንን ደብቃ አድናለች። 18 እናንተ ግን
መደምሰስ ከሚገባው ሁሉ ምንም ነገር አታ
ንሡ፤ ይህን ብታደርጉ በእስራኤል ሰፈር መከ
ራንና ጥፋትን ታስከትላላችሁ፤ 19 ከብር፥ ከወ
ርቅ፥ ከነሐስ ወይም ከብረት የተሠራ ማናቸ
ውም ነገር ለእግዚአብሔር የተለየ ይሁን፤ እር
ሱም በእግዚአብሔር የዕቃ ግምጃ ቤት መቀ
መጥ አለበት።”
20 ስለዚህም ካህናቱ የመለከቶቹን ድምፅ
አሰሙ፤ ሠራዊቱም ያን ድምፅ በሰማ ጊዜ በከ
ፍተኛ ጩኸት ደነፋ፤ የከተማይቱም ቅጽሮች
ፈረሱ፤ ከዚህም በኋላ ሠራዊቱ ኮረብታውን
ወጥቶ ሰተት ብሎ ወደ ከተማይቱ በመግባት
በቊጥጥሩ ሥር አደረጋት፤ 21 ሰይፋቸውንም
መዝዘው በከተማይቱ የተገኘውን ወንዱንም
ሴቱንም ወጣቱንና ሽማግሌውን ሁሉ ገደሉ፤
የከብት፥ የበግና የአህያውን መንጋ ሁሉ ፈጁ።

መሠረት በረከቱንም መርገሙንም ጭምር ሕጉ
ንም በሙሉ አነበበ ። 35 ሴቶች ፥ ሕፃናትና በመ
ካከላቸውም የሚኖሩ የውጭ አገር ስደተኞች
ባሉበት የእስራኤል ሕዝብ ጉባኤ ኢያሱ እያንዳ
ንዱን የሙሴን ትእዛዝ አነበበ ።

## ምዕራፍ 9

### የገባዖን ሰዎች ኢያሱን አታለሉ

1 በሰሜን እስከ ሊባኖስ በሜድትራኒያን
ባሕር ጠረፍና ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ በደጋ
ውም በቆላውም ያሉት ነገሥታት ሁሉ የእስራ
ኤልን ድል አድራጊነት ሰሙ ፤ እነዚህም የሒ
ታውያን ፥ የአሞራውያን ፥ የከነዓናውያን ፥ የፈ
ሪዛውያን ፥ የሒዋውያንና የኢያቡሳውያን ነገሥ
ታት ነበሩ ። 2 እነዚህም ሁሉ ኀይላቸውን በአን
ድነት አስተባብረው በኢያሱና በእስራኤላውያን
ላይ ለመዝመት መጡ ።
3 የሒዋውያን ወገኖች የሆኑት የገባዖን
ሰዎች ግን ኢያሱ በኢያሪኮና በዐይ ከተማዎች
ላይ ያደረገውን ሁሉ ሰለ ሰሙ ፤ 4 እርሱን ለማ
ታለል ወሰኑ ፤ እነርሱም ስንቃቸውን አዘጋጅ
ተው ፥ አሮጌ ሰልቻና ቀዳዳው ተለጥፎ የተሰፋ
የወይን ጠጅ አቁማዳ በአህዮች ጫኑ ፤ 5 ተቀዳ
ድዶ ያለቀ አሮጌ ልብስ ለብሰው ፥ የተጠጋገነ
አላቂ ጫማ አደረጉ ፤ ለስንቅ የያዙትም እንጀራ
ደረቅና የሻገተ ነበር ። 6 ይህን ሁሉ ካደረጉ
በኋላ በጌልገላ ወደሚገኘው ሰፈር ሄደው ኢያ
ሱንና እስራኤላውያንን ፥ "እኛ የመጣነው
ከሩቅ አገር ነው ፤ የመጣነውም ከእናንተ ጋር
በሰላም መኖር የሚያስችል ውል ለማድረግ
ነው" አሉአቸው ።
7 የእስራኤል ሰዎች ግን "ከእናንተ ጋር እን
ዴት ውል እናደርጋለን? ምናልባትም እናንተ
በቅርብ የምትኖሩ ልትሆኑ ትችላላችሁ" አሉአ
ቸው ።
8 የገባዖንም ሰዎች ኢያሱን "እኛ አገልጋዮ
ችህ ነን" አሉት ።
ኢያሱም "እናንተ እነማን ናችሁ? የመጣች
ሁትስ ከየት ነው?" ሲል ጠየቃቸው ።
9 እነርሱም ይህን ታሪክ ነገሩት ፥ "ጌታው!
እኛ የመጣነው በጣም ሩቅ ከሆነ አገር ነው ፤
ምክንያቱም አምላካችሁ እግዚአብሔር እናን
ተን በመርዳት በግብጽ ላይ ያደረገውን ሁሉ
ሰምተናል ፤ 10 እንዲሁም ከዮርዳኖስ ማዶ በስተ
ምሥራቅ በነበሩት በሁለቱ አሞራውያን ነገሥ
ታት ላይ ያደረገውን ሁሉ ሰምተናል ፤ እነዚ
ህም ሁለቱ ነገሥታት በዐስታሮት ይኖሩ የነበ
ሩት የሐሴቦን ንጉሥ ሲሖንና የባሳን ንጉሥ ዖግ
ናቸው ። 11 መሪዎቻችንና በምድራችን የሚኖ
ሩት ሕዝብ ሁሉ ለመንገዳችን የሚሆነንን ስንቅ
አዘጋጅተን መጥተን ከእናንተ ጋር እንድንገናኝ
ልከውናል ፤ ለእናንተ የምንታዘዝ አገልጋዮች
እንድንሆንና እናንተም ከእኛ ጋር የሰላም ውል
እንድታደርጉ እንጠይቃችሁ ዘንድ አዝዘው
ናል ። 12 የያዝነውን ስንቅ ተመልከቱ ፤ ከቤት
ተነሥተን ከእናንተ ጋር ለመገናኘት ጉዞ ስንጀ
ምር ገና ትኩስ እንጀራ ነበር ፤ አሁን ግን ደረ
ቅና የሻገተ መሆኑን ተመልከቱ! 13 እነዚህንም
የወይን አቁማዳዎች በሞላናቸው ጊዜ ገና አዲስ
ነበሩ ፤ አሁን ግን የተቀደዱ መሆናቸውን ተመ
ልከቱ! ከጉዞው ርቀት የተነሣ እነሆ ልብሳች
ንም ጫማችንም አልቆአል ።"
14 የእስራኤልም ሰዎች ከመንገደኞቹ ስንቅ
ጥቂት ወሰዱ ፤ ስለሁኔታው ግን የእግዚአብሔ
ርን ፈቃድ አልጠየቁም ። 15 ስለዚህም ኢያሱ
ከገባዖን ሕዝብ ጋር የወዳጅነት ስምምነት አድ
ርጎ በሰላም እንዲኖሩ ፈቀደላቸው ። የእስራኤል
ሕዝብ መሪዎችም ስምምነቱን ለመጠበቅ ቃል
ገቡላቸው ።
16 ስምምነቱ በተደረገ በሦስተኛውም ቀን
እነዚህ ሰዎች በቅርብ የሚኖሩ መሆናቸውን
እስራኤላውያን ዐወቁ ፤ 17 ስለዚህም የእስራኤል
ሕዝብ ጉዞ ጀምረው ከሦስት ቀን በኋላ እነዚህ
ሕዝብ ወደሚኖሩባቸው ከተሞች ደረሱ ፤ ከተ
ሞቻቸውም ገባዖን ፥ ከፊራ ፥ በኤሮትና ቂርያት
ይዓሪም ተብለው ይጠሩ ነበር ፤ 18 እስራኤላው
ያን ግን እነርሱን መግደል አልቻሉም ፤ ምክንያ
ቱም መሪዎቻቸው የእስራኤል አምላክ በሆነው
በእግዚአብሔር ስም ቃል ገብተውላቸው
ነበር ፤ ስለዚህም ጉዳይ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ
በመሪዎቻቸው ላይ አጒረመረሙ ፤ 19 መሪዎቹ
ግን እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው ፥ "እርግጥ ነው
የእስራኤል አምላክ በሆነው በእግዚአብሔር
ስም ቃል ገብተንላቸዋል ፤ ስለዚህም አሁን
ጒዳት ልናደርስባቸው አንችልም ፤ 20 የገባነውን
ቃል ለማክበር በሕይወት እንዲኖሩ እንፈቅድላ
ቸዋለን ፤ ይህን ባናደርግ ደግሞ እግዚአብሔር
ራሱ ይቀጣናል ። 21 በመካከላችን ይኑሩ ፤ ነገር
ግን እንጨት እየቈረጡ ፥ ውሃ እየቀዱ ያገልግ
ሉን ፤" መሪዎቹ ያቀረቡት አሳብ ይህ ነበር ።
22 ኢያሱም የገባዖን ሕዝብ ወደ እርሱ ፊት
እንዲቀርቡ አድርጎ እንዲህ ሲል ጠየቃቸው ፥
"በዚሁ በቅርብ የምትኖሩ ሲሆን በጣም ሩቅ
ከሆነ አገር የመጣን ነን ብላችሁ ስለምን አታለ
ላችሁን? 23 ይህን በማድረጋችሁ ምክንያት እግ
ዚአብሔር ረግሞአችኋል ፤ ስለዚህም የእናንተ
ሕዝብ እንጨት በመቊረጥና ውሃ በመቅዳት
ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለዘላ
ለም አገልጋዮች ይሆናሉ ።"
24 እነርሱም እንዲህ ሲሉ መለሱ ፥
"ጌታው! በእርግጥ ይህን አድርገናል ፤ ምክንያ
ቱም አምላካችሁ እግዚአብሔር እናንተ ወደ

9፡7 ፦ ዘጸ. 23፡32 ፤ 34፡12 ፤ ዘዳ. 7፡2 ። 9፡10 ፦ ዘኍ. 21፡21-35 ።

ፊት እየገፋችሁ በመጣችሁ መጠን በውስጧ
የሚኖሩትን ሕዝብ በመግደል ምድሪቱን ያወር
ሳችሁ ዘንድ አገልጋዩን ሙሴን ያዘዘው መሆኑን
ዐውቀናል ፤ ይህንንም ያደረግነው እናንተን ከመ
ፍራታችን የተነሣ ሕይወታችንን ለማትረፍ ፈል
ገን ነው ። [25]እነሆ አሁን በእናንተ ሥልጣን
ሥር ነን ፤ መልካም መስሎ የታየህን ሁሉ አድ
ርግብን ።” [26]ስለዚህም ኢያሱ ከእስራኤል
ሕዝብ ወገን ማንም እንዳይገድላቸውና ተጠብ
ቀው እንዲኖሩ አደረገ ። [27]ነገር ግን በዚሁ
ጊዜ እንጨት በመቊረጥና ውሃ በመቅዳት ለእስ
ራኤል ሕዝብና ለእግዚአብሔር መሠዊያ አገል
ጋዮች እንዲሆኑ አደረገ ። እነርሱም እስከ አሁን
ድረስ እግዚአብሔር ሲመለክበት በመረጠው
ቦታ ፥ ይህንኑ አገልግሎት በመፈጸም ላይ ይገ
ኛሉ ።

## ምዕራፍ 10

### አሞራውያን ተሸነፉ

[1]ኢያሱ የዐይን ከተማ በጦርነት ከያዘ በኋላ
በኢያሪኮና በንጉሥዋ ላይ ባደረገው ዐይነት በፍ
ጹም የደመሰሳት መሆኑንና ንጉሥዋንም መግደ
ሉን የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ ሰማ ፤
እንዲሁም የገባዖን ሰዎች ከእስራኤላውያን ጋር
ስምምነት አድርገው በሰላም መኖራቸውን
ተረዳ ። [2]ከዚህም የተነሣ የኢየሩሳሌም ነዋሪ
ሕዝብ ብርቱ ድንጋጤ አደረባቸው ፤ ምክንያ
ቱም ገባዖን በነገሥታት እንደሚተዳደሩት ከተ
ሞች ታላቅ ስትሆን ከዐይ ከተማም የምትበልጥ
ነበረች ፤ ሰዎችዋም ብርቱ ጦረኞች ነበሩ ።
[3]ስለዚህ አዶኒጼዴቅ ሆሃም ተብሎ ለሚጠራው
ለኬብሮን ንጉሥ ፥ ፒራም ለተባለው ለያርሙት
ንጉሥ ፥ ያፊዓ ለተባለው ለላኪሽ ንጉሥና
ደቢር ለተባለው ለዔግሎን ንጉሥ እንዲህ
የሚል መልእክት ላከ ፥ [4]“ገባዖንን ለመውጋት
መጥታችሁ እርዱኝ ፤ ምክንያቱም በእርስዋ
የሚኖሩት ሕዝብ ከኢያሱና ከእስራኤላውያን
ጋር በሰላም አብሮ የመኖር ስምምነት አድርገ
ዋል ።” [5]እነዚህ የኢየሩሳሌም ፥ የኬብሮን ፥
የያርሙት ፥ የላኪሽና የዔግሎን ገዦዎች የሆ
ኑት አምስቱ አሞራውያን ነገሥታት ሠራዊቶቻ
ቸውን አስተባብረው የጦር ግንባር በመፍጠር
ገባዖንን ከበው አደጋ ጣሉባት ።

[6]የገባዖን ሰዎችም ሰፈሩን በጌልገላ አድርጎ
ወደነበረው ወደ ኢያሱ እንዲህ ሲሉ መልእክት
ላኩበት ፥ “ጌታው! እባክህ ቸል ብለህ አትተ
ወን ፤ በፍጥነት መጥተህ እርዳን ፤ አድነንም ፤
ምክንያቱም በኰረብታማው አገር የሚኖሩ አሞ
ራውያን ነገሥታት ሁሉ ሠራዊቶቻቸውን በማስ
ተባበር በእኛ ላይ አደጋ ጥለውብናል ።”

[7]ስለዚህም ኢያሱና መላው ሠራዊት ፥
ምርጥ የሆኑት ወታደሮች ጭምር ከጌልገላ ተነ
ሥተው ጒዞ ጀመሩ ፤ [8]እግዚአብሔርም ኢያ
ሱን “እነርሱን አትፍራቸው ፥ እኔ ፍጹም
ድልን ሰጥቼሃለሁ ፤ ከእነርሱ አንድም የሚቋቋ
ምህ አይኖርም” አለው ። [9]ኢያሱና ሠራዊቱ
ሌሊቱን ሙሉ ከጌልገላ ወደ ገባዖን ሲገሠግሡ
አድረው በአሞራውያን ላይ ድንገተኛ አደጋ
ጣሉባቸው ። [10]እግዚአብሔርም በእስራኤል
ሠራዊት ፊት አሞራውያን በድንጋጤ እንዲሸ
በሩ አደረገ ፤ እስራኤላውያንም እነርሱን በገባ
ዖን ዐረዱአቸው ፤ የቀሩትንም በቤትሖሮን እስከ
ተራራው መተላለፊያ ቊልቊለት ድረስ አሳደዱ
አቸው ፤ በደቡብ በኩል እስከ ዐዜቃና እስከ
ማቄዳ ድረስ እያሳደዱ አደጋ ጣሉባቸው ።
[11]አሞራውያን በመተላለፊያው ቊልቊለት ከእስ
ራኤላውያን ሠራዊት በሚሸሹበት ጊዜ ፥ እግዚ
አብሔር እስከ ዐዜቃ ድረስ ከሰማይ ታላላቅ
በረዶ አወረደባቸው ፤ ስለዚህም እስራኤላውያን
ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶ የሞቱት እጅግ
ብዙዎች ሆኑ ።

[12]እግዚአብሔር ለእስራኤል በአሞራውያን
ላይ ድልን በሰጠበት ዕለት ኢያሱ ከእግዚአብ
ሔር ጋር ተነጋገረ ፤ በእስራኤላውያንም
ፊት ፥

“በገባዖን ላይ ፀሐይ ሳይጠልቅ ይቆይ ፤
ጨረቃም በአያሎን ሸለቆ ቆማ
ትታይ” አለ ።

[13]ስለዚህም የእስራኤል ሕዝብ ጠላቶቻቸ
ውን ድል እስኪመቱ ፀሐይ ቆመ ፤ ጨረቃም
ከለችበት ሳትንቀሳቀስ ቆየች ፤ ይህም በያሻር
መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል ፤ ፀሐይ ሳይንቀሳቀስ
በሰማይ መካከል ቆመ ፤ ቀኑንም ሙሉ ሳይጠ
ልቅ ቆየ ፤ [14]እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማ
በት እንደዚያ ያለ ቀን ከዚያም በፊት ሆነ
ከዚያ ወዲህ ታይቶ አይታወቅም ፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር ከእስራኤል ጐን ተሰልፎ ይዋጋላ
ቸው ነበር ።

[15]ከዚህ በኋላ ኢያሱና ሠራዊቱ በጌልገላ
ወደ ነበረው ሰፈር ተመለሱ ።

### ኢያሱ አምስቱን አሞራውያን ነገሥታት ማረከ

[16]የሆነ ሆኖ አምስቱ አሞራውያን ነገሥ
ታት አምልጠው በማቄዳ ዋሻ ተደብቀው
ነበር ፤ [17]ነገር ግን አንድ ሰው አይቶአቸው ስለ
ነበር የተደበቁበት ቦታ ለኢያሱ ተነገረው ፤
[18]እርሱም እንዲህ ሲል ትእዛዝ ሰጠ ፥ “ታላ
ላቅ ድንጋዮች አንከባልላችሁ የዋሻውን በር
ዝጉ ፤ በዚያም ዘብ ጠባቂ አቁሙበት ፤ [19]እና
ንተ ግን በዚያ አትቆዩ ፤ ጠላትን እያሳደዳችሁ

10፥13 ፦ 2ሳሙ. 1፥18 ።

ከኋላ በኩል አደጋ መጣላችሁን ቀጥሉ፤ ሸሽ
ተው ወደ ከተሞቻቸው እንዲገቡ መንገድ አት
ስጡአቸው፤ እምላካችሁ እግዚአብሔር በእነ
ርሱ ላይ ድልን ሰጥቶአችኋል።” 20 ጥቂቶች
ብቻ በየከተማቸው ባሉት ግንቦች ውስጥ ተደብ
ቀው ከሞት ለመትረፍ ቢችሉም፣ ኢያሱና የእ
ስራኤል ሰዎች ሁሉንም ዐረዱአቸው። 21 ከዚህ
በኋላ የኢያሱ ሰዎች ሁሉ በሰላም ተመልሰው
እርሱ ወደ ሰፈረበት ወደ ማቄዳ መጡ።
ከዚህም የተነሣ በምድሪቱ በእስራኤላውያን
ላይ ደፍሮ ቃል የሚናገር እንኳ አልነበረም።
22 ከዚህም በኋላ ኢያሱ “የዋሻውን በር ክፍ
ታችሁ በማውጣት እነዚያን አምስት ነገሥታት
ወደ እኔ አምጡ” ሲል ትእዛዝ ሰጠ፤ 23 ስለዚ
ህም ዋሻው ተከፍቶ እነዚያ አምስቱ የኢየሩሳ
ሌም፣ የኬብሮን፣ የያርሙት፣ የላኪሽና የዔግ
ሎን ነገሥታት እንዲወጡ ተደረገ፤ 24 ወደ
ኢያሱም አመጡአቸው፤ ኢያሱም የእስራኤልን
ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ጠራ፤ ከእርሱ ጋር የዘ
መቱት የጦር መኰንኖችም መጥተው እግራቸ
ውን በነገሥታቱ አንገት ላይ እንዲያደርጉ ትእ
ዛዝ ሰጠ፤ እነርሱም እንደ ታዘዙት አደረጉ።
25 ኢያሱም ስጦር መኰንኖቹ እንዲህ አለ፣
“ከቶ አትፍሩ፤ በርቱ! ቈራጥነትና ድፍረት
ይኑራችሁ! ምክንያቱም እግዚአብሔር በጠላቶ
ቻችሁ ሁሉ ላይ ልክ እንደዚህ ያደርጋል።”
26 ከዚህም በኋላ ኢያሱ አምስቱን ነገሥታት
ገድሎ በአምስት ዕንጨት ላይ ሰቀላቸው፤ ሬሳ
ቸውም እስከ ምሽት ድረስ በዚያው ዋለ።
27 ፀሐይም ስትጠልቅ የነዚያ ነገሥታት ሬሳ
ከየተሰቀሰበት እንጨት እንዲወርድና ቀድሞ
ተደብቀው ወደነበሩበት ዋሻ ውስጥ እንዲጣል
ኢያሱ ትእዛዝ ሰጠ፤ ታላላቅ ድንጋዮችንም እን
ከባልለው የዋሻውን ደጃፍ ገጠሙት፤ እስከሬና
ቸውም ሁሉ እስከ እሁን በዚያ ይገኛል።

### ኢያሱ በተጨማሪ ብዙ የአሞራውያንን ግዛት ያዘ

28 በዚያን ቀን ኢያሱ ማቄዳ ላይ አደጋ ጥሎ
ንጉሥዋን ማረከ፤ በከተማይቱ የነበሩትን ሰዎች
ሁሉ አንድም ሳያስቀር ፈጀ፤ በማቄዳም ንጉሥ
ላይ ቀድሞ በኢያሪኮ ንጉሥ ላይ ባደረገው ዐይ
ነት የሞት ቅጣት ፈጸመበት።
29 ከዚህም በኋላ ኢያሱና ሠራዊቱ ከማቄዳ
ወደ ሊብና ዘምተው አደጋ ጣሉባት፤ 30 እግዚ
አብሔርም ደግሞ በዚህች ከተማና በንጉሥዋ
ላይ ለእስራኤላውያን ድልን ሰጣቸው፤ አንድ
ሰው እንኳ ሳያስተርፉ በከተማይቱ የነበሩትን
ሰዎች ሁሉ በሰይፍ ገደሉ፤ በንጉሡም ላይ
ቀድሞ በኢያሪኮ ንጉሥ ላይ ባደረጉት ዐይነት
የሞት ቅጣት ፈጸሙበት።
31 ከዚህ በኋላ ኢያሱና ሠራዊቱ ከሊብና
ወደ ላኪሽ ዘምተው ከበባ በማድረግ አደጋ
ጣሉባት፤ 32 እግዚአብሔርም ጦርነቱ በተጀ
መረ በሁለተኛው ቀን ለእስራኤላውያን በላኪሽ
ላይ ድልን ሰጣቸው፤ በሊብና ባደረጉትም ዐይ
ነት በከተማይቱ ያገኙትን ሰው ሁሉ ፈጁ፤
33 በዚህን ጊዜ የጌዘር ንጉሥ ሆራም ላኪሽን
ለመርዳት መጥቶ ነበር፤ ነገር ግን ኢያሱ እርሱ
ንና ሠራዊቱን ድል አደረገ፤ ከእነርሱም በሕይ
ወት የተረፈ አንድ እንኳ አልነበረም።
34 ቀጥሎም ኢያሱና ሠራዊቱ ከላኪሽ ወደ
ዔግሎን ዘምተው ከበባ በማድረግ አደጋ ጣሉ
በት፤ 35 በዚያኑም ዕለት ከተማይቱን ያዙ፤
ልክ በላኪሽ ባደረጉትም ዐይነት ያገኙትን ሰው
ሁሉ ገደሉ።
36 ከዚህ በኋላ ኢያሱና ሠራዊቱ ከዔግሎን
ኰረብታውን ወጥተው በኬብሮን ላይ አደጋ
ጣሉባት። 37 እርስዋንም ይዘው ንጉሡን፣ በከ
ተማይቱና በአካባቢዋም የገጠር ከተሞች ያገኙ
ትን ሁሉ ገደሉ፤ ኢያሱም ልክ በዔግሎን ባደረ
ገው ዐይነት ከተማይቱ እንድትደመሰስ ፈረደ
ባት፤ በእርስዋም ውስጥ በሕይወት የተረፈ እን
ድም አልነበረም።
38 ከዚህ በኋላ ኢያሱና ሠራዊቱ ወደ ደቢር
ተመልሰው በመዝመት አደጋ ጣሉባት፤ 39 እር
ሱም ከተማይቱን፣ ንጉሥዋንና በአካባቢዋ ያሉ
ትን ታናናሽ ከተሞች ሁሉ ያዘ፤ እስራኤላው
ያን በዚያ የነበሩትን ሁሉ ገደሉ፤ ኢያሱ በደቢ
ርና በንጉሥዋ ላይ ልክ በኬብሮንና በሊብና
እንዲሁም በነገሥታቶቻቸው ላይ ባደረገው ዐይ
ነት ቅጣት ፈጸመባቸው።
40 በዚህ ዐይነት ኢያሱ ምድሪቱን በሙሉ
ያዘ፤ የተራራማውን አገር፣ በምሥራቅ ቈልቈለ
ትና ከኰረብታዎቹ ግርጌ በስተምዕራብ በኩል በደ
ቡብ በኩል እስካለው በረሓማው አገር ድረስ የነበ
ሩትን ነገሥታት ድል አደረገ። አንድ ሰው እንኳ
ሳያስተርፍ ሁሉንም በሞት ቀጣ፤ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር የሰጠው ትእዛዝ ይኸው
ነበር። 41 የኢያሱም የዘመቻ ድል በደቡብ በኩል
ከቃዴስ በርኔ ተነሥቶ በባሕር ጠረፍ እስካለችው
እስከ ጋዛ የጎሼንን አካባቢ ሁሉ ጨምሮ፣ በሰሜን
እስከ ገባዖን ድረስ ተስፋፋ። 42 ኢያሱ እነዚህን
ነገሥታትና ግዛቶቻቸውን ሁሉ በአንድ ዘመቻ
ድል አጠቃለለ፤ ምክንያቱም የእስራኤል አምላክ
የሆነ እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋላቸው
ነበር። 43 ከዚህም በኋላ ኢያሱና ሠራዊቱ በጌል
ገላ ወደነበረው ሰፈር ተመለሱ።

## ምዕራፍ 11

### ኢያሱ ያቢንንና የጦር ተባባሪዎቹን ድል አደረገ

1 የሐጾር ንጉሥ ያቢን የእስራኤልን ድል
አድራጊነት በሰማ ጊዜ ወደ ማዶን ንጉሥ
ዮባብ፣ ወደ ሺምሮንና ወደ አክሻፍ ነገሥ
ታት፣ 2 በሰሜን በኩል በኰረብታማው አገር፣

ነገሥታትን ድል ነሥተዋል ፤ [2]ከሁለቱ ነገሥ
ታት አንዱ ፥ በሐሴቦን ሆኖ የሚገዛው የአሞራ
ውያን ንጉሥ ሲሖን ነበር ፤ ግዛቱም የገለዓድን
እኩሌታ በማጠቃለል ፥ በአርኖን ሸለቆ ጠርዝ
ከምትገኘው ከዓሮዔር ተነሥቶ በዚያ ሸለቆ
መካከል ያለችውን ከተማ በመጨመር የዐሞና
ውያን ወሰን እስከሆነው እስከ ያቦቅ ወንዝ ይደ
ርስ ነበር ፤ [3]እርሱም ከገሊላ ባሕር ተነሥቶ
የዮርዳኖስን ሸለቆ በመጨመር በደቡብ በኩል
ከሙት ባሕር በስተምሥራቅ እስከምትገኘው
እስከ ቤትየሺሞትና እስከ ፒስጋ ተራራ ግርጌ
የሚደርሰውን ምድር ሁሉ ያጠቃልል ነበር ።

[4]እንዲሁም ከረፋያውያን ወገን መጨረሻ
የቀረውን የባሳንን ንጉሥ ዖግን ድል ነሡ ፤ እር
ሱም መኖሪያው በዐስታሮትና በኤድረዒ ነበር ፤
[5]ግዛቱም የሔርሞንን ተራራ ፥ ሳልካን ፥ እስከ
ገሹርና ማዕካ ድንበሮች የሚደርሰውን የባሳንን
ምድር ሁሉ ጠቅሎ ፥ የሐሴቦን ንጉሥ የሲሖን
ይዞታ እስከሆነው ግዛት የገለዓድን እኩሌታ
የሚጨምር ነበር ።

[6]እንግዲህ እነዚህ ሁለት ነገሥታት በሙሴና
በእስራኤል ሕዝብ ጦርነት ድል ሆነው ነበር ፤
የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴም ይህን ምድር
ለሮቤልና ለጋድ ነገዶች እንዲሁም ለምናሴ
ነገድ እኩሌታ በማከፋፈል ርስት አድርጎ ሰጣ
ቸው ።

### ኢያሱና ድል የነሣቸው ነገሥታት

[7]ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ ከዮርዳኖስ በስ
ተምዕራብ ባለው ግዛት የነበሩትን ነገሥታት
ሁሉ ድል ነሡ ፤ ይህም ግዛት በሊባኖስ ሸለቆ
ከሚገኘው ከባዓልጋድ ተነሥቶ ፥ በደቡብ
በኩል በኤዶም አጠገብ እስካለው እስከ ሐላቅ
ተራራ ይደርስ ነበር ፤ ኢያሱም ይህን ምድር
በማከፋፈል ለእያንዳንዱ ነገድ ርስት አድርጎ
ሰጠ ። [8]ይህም የርስት ድርሻ ኮረብታማውን
አገር ፥ በስተ ምዕራብ ያለውን የኮረብታ ግርጌ ፤
የዮርዳኖስን ሸለቆና በእርሱም ኮረብታዎች
ግርጌ ያሉትን በስተ ምሥራቅ በኩል የሚገኘ
ውን ረባዳ ቦታና በደቡብ በኩል የሚገኘውን
በረሓማ ምድር ሁሉ ያጠቃልል ነበር ፤ ይህም
ምድር ቀድሞ የሒታውያን ፥ የአሞራውያን ፥
የከነዓናውያን ፥ የፈሪዛውያን ፥ የሒዋውያንና
የኢያቡሳውያን መኖሪያ ነበር ። [9]የእስራኤል
ሕዝብ ነገሥታቶቻቸውን ድል ነሥተው የያዙ
አቸውም ከተሞች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ፥
ኢያሪኮ ፥ በቤትኤል አጠገብ ያለችው ዐይ ፥
[10]ኢየሩሳሌም ፥ ኬብሮን ፥ [11]ያርሙት ፥
ላኪሽ ፥ [12]ዔግሎን ፥ ጌዜር ፥ [13]ደቢር ፥
ጌዴር ፥ [14]ሖርማ ፥ ዐራድ ፥ [15]ሊብና ፥ ዐዱ
ላም ፥ [16]ማቄዳ ፥ ቤትኤል ፥ [17]ታፑሐ ፥
ሔፌር ፥ [18]አፌቅ ፥ ላሻሮን ፥ [19]ማዶን ፥
ሐጾር ፥ [20]ሺምሮንመሮን ፥ አክሻፍ ፥ [21]ታዕ
ናክ ፥ መጊዶ ፥ [22]ቄዴሽ ፥ በቀርሜሎስ የሚገ
ኘው ዮቅንዓም ፥ [23]በባሕር ጠረፍ የሚገኘው
ዶር ፥ በጌልገላ የሚገኘው ጎይምና [24]ቲርጻ
ሲሆኑ ፥ ነገሥታቱም በሙሉ ሠላሳ አንድ
ነበሩ ።

## ምዕራፍ 13

### መወረስ የነበረበት ገና ያልተያዘ ምድር

[1]እነሆ ኢያሱ በዕድሜ እየገፋ ስለሄደ
አረጀ ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ አለው ፥
“እነሆ አንተ አጅግ ሸምግለሃል ፤ ነገር ግን
መያዝ የነበረበት ገና ብዙ ምድር ቀርቶአል ፤
[2]ከዚህም ውስጥ የፍልስጥኤምና የገሹር ግዛት
በሙሉ ፤ [3]በደቡብ በኩልም እስከ ዓዊም የሚደ
ርሰው ግዛት በሙሉ ፤ ይኸውም በግብጽ ጠረፍ
ከሚገኘው ከሺሖር ምንጭ አንሥቶ በሰሜን
እስከ ዔቅሮን የሚደርሰው ምድር የከነዓን ሆኖ ፥
እነሆ አምስት የፍልስጥኤማውያን ነገሥታት
በጋዛ ፥ በአሽዶድ ፥ በአስቀሎና ፥ በጋትና በዔቅ
ሮን ይኖራሉ ። [4]በሌላም በኩል የሲዶናውያን
ይዞታ የሆነው የከነዓን አገር መዓራ ተብሎ የሚ
ጠራውን ሁሉ ጨምሮ በአሞራውያን ጠረፍ
እስከ አፌቅ ድረስ የሚገኘው ፥ [5]የጌባላውያን
ምድርና ከምሥራቅ በሔርሞን ተራራ ደቡብ
ከሚገኘው ከባዓልጋድ ተነሥቶ እስከ ሐማት
መተላለፊያ ያለው መላው ሊባኖስ ገና አልተያ
ዘም ። [6]ይህም በሊባኖስ ተራራዎችና በሚስረፎ
ትማይም መካከል በሚገኘው ኮረብታማ አገር
የሚኖሩትን የሲዶናውያንን ግዛት ሁሉ የሚጨ
ምር ነው ፤ የእስራኤል ሕዝብ ወደፊት እየገፋ
በሚሄዱ መጠን እኔ እነዚህን አሕዛብ አሳድዳ
ቸዋለሁ ፤ አንተም ባዘዝሁህ መሠረት ምድሩን
ሁሉ ለእስራኤላውያን ታከፋፍላለህ ። [7]ይህንንም
ምድር ርስት አድርገህ የምታካፍለው ለዘጠኙ
ነገዶችና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ነው ።”

### ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ያለው ግዛት አከፋፈል

[8]የሮቤልና የጋድ ነገዶች እንዲሁም የምናሴ
ነገድ እኩሌታ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ
የሰጣቸውን ምድር ቀደም ብለው ወርሰዋል ፡፡
ይህም ምድር የሚገኘው በስተምሥራቅ ከዮርዳ
ኖስ ወንዝ ማዶ ነው ። [9]ግዛታቸውም ከአርኖን
ሸለቆ ዳርቻ ተነሥቶ እስከ ዓሮዔርና በዚያም
ሸለቆ መካከል እስከምትገኘው ከተማ ይደርስና
ከሜደባ እስከ ዲቦን ያለውን ደጋማ አገር ሁሉ
ያጠቃልላል ። [10]በሌላም በኩል እስከ ዐሞን
ድንበር እየተዋሰነ በሐሴቦን ሆኖ የሚገዛውን
የአሞራውያን ንጉሥ የሲሖንን ከተሞች ሁሉ

12፡6 ፦ ዘኍ. 32፡33 ፤ ዘዳ. 3፡12 ።  13፡6 ፦ ዘኍ. 33፡54 ።  13፡8 ፦ ዘኍ. 32፡33 ፤ ዘዳ. 3፡12 ።

ያጠቃልላል ፤ 11 እርሱም ገለዓድን ፥ የገሹርንና
የማዕካን አውራጃዎችና የሔርሞንን ተራራ
በሙሉ እንዲሁም እስከ ሳለካ ድረስ ያለውን
ባሳንን ይጨምራል ። 12 እንዲሁም በዐስታሮትና
በኤድረዒ ሆኖ ይገዛ የነበረውን ከረፋያውያን
መጨረሻ የቀረውን የንጉሥ ዖግን ግዛት ባሳንን
አጠቃሎ ይዞአል ፤ ሙሴ እነዚህን ሕዝብ ሁሉ
ድል ነሥቶ አባረረ ። 13 ይሁን እንጂ እስራኤላ
ውያን የገሹርንና የማዕካን ሕዝብ አላስወጡም ፤
ስለዚህም እነርሱ እስከ አሁን በእስራኤላውያን
መካከል ይኖራሉ ።

14 ሙሴ ለሌዊ ነገድ የርስት ድርሻ አልሰ
ጠም ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት
የእስራኤል አምላክ ለሆነው ለእግዚአብሔር
በመሠዊያ ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ
ከሚቀርበው መባ የሚያገኙት ድርሻ እንደ
ርስት ሆኖ ተመድቦላቸዋል ።

### ለሮቤል ርስት ሆኖ የተመደበ ምድር

15 ሙሴ ከምድሪቱ ከፊሉን ለሮቤል ነገድ
ቤተሰቦች ሁሉ ርስት አድርጎ ሰጠ ፤ 16 ግዛታቸ
ውም በአርኖን ሸለቆ ዳርቻ እስከሚገኘው እስከ
ዓሮዔርና በዚያም ሸለቆ መካከል እስካለችው
ከተማ አልፎ በሜደባ ዙሪያ ያለውን ደጋማ
አገር ሁሉ ያጠቃልላል ፤ 17 እንዲሁም ሐሴቦ
ንን ፥ በደጋማው አገር ያሉትን ከተሞች ፤
ዲቦን ፥ ባሞትበዓል ፥ ቤትበዓልመዖን ፥
18 ያህጽ ፥ ቀዴሞት ፥ ሜፍዓት ፥ 19 ቂርያታ
ይም ፥ ሲበማ ፥ በኰረብታማው ሸለቆ የሚገኘው
ጼሬትሻሐር ፥ 20 ቤትፐዖር ፥ ከፒስጋ ተራራ
በታች ያለው ረባዳ ምድርና ቤትየሺሞት ተብ
ለው የሚጠሩትን ሁሉ ይጨምራል ። 21 በደጋ
ማውም አገር የሚገኙትን ከተሞችና መኖሪያ
ውን በሐሴቦን አድርጎ ይገዛ የነበረውን የአሞራ
ውያን ንጉሥ የሲሖንን ግዛት ሁሉ ይጨም
ራል ። ሙሴም ንጉሥ ሲሖንንና የምድያም
መሪዎች የነበሩትን ፥ ኤዊን ፥ ሬቄምን ፥
ጹርን ፥ ሑርንና ሬባዕን ድል ነሣ ፤ እነዚህ
ሁሉ ምድሪቱን የሚያስተዳድሩት የንጉሥ
ሲሖን ገባሮች በመሆን ነበር ። 22 የእስራኤል
ሕዝብ ከገደሉአቸውም መካከል አንዱ ጠንቋይ
እየተባለ ይጠራ የነበረው የቢዖር ልጅ በለዓም
ነበር ። 23 የዮርዳኖስም ወንዝ በምዕራብ በኩል
ለሮቤል ነገድ የግዛቱ ወሰን ነበር ፤ እንግዲህ
ለሮቤል ነገድ ቤተሰቦች ርስት ሆነው የተሰጡአ
ቸው ከተሞችና መንደሮች እነዚህ ነበሩ ።

### ለጋድ ርስት ሆኖ የተመደበ ምድር

24 ሙሴ ከምድሪቱ ከፊሉን ደግሞ ለጋድ
ነገድ ቤተሰቦች ሁሉ ርስት አድርጎ ሰጠ ፤
25 የእነርሱም ግዛት ያዕዜርንና በገለዓድ የሚገ
ኙትን ከተሞች ሁሉ የሀሞንን ምድር እኩሌታ
ጨምሮ ከራባ በስተምሥራቅ እስከምትገኘው
እስከ ዓሮዔር ይደርሳል ። 26 የምድራቸውም
ስፋት ከሐሴቦን ተነሥቶ እስከ ራማት ምጽጴና
እስከ ቤጦኒም እንዲሁም ከማሕናይም ተነሥቶ
እስከ ሎደባር ድንበር ይደርሳል ፤ 27 ከዮርዳኖ
ስም ሸለቆ በተለይ የሐሴቦን ንጉሥ የሲሖን
መንግሥት ቅሬታ የሆኑትን ቤትሀራም ፥ ቤትኒ
ምራ ፥ ሱኮትና ጻፎን ተብለው የሚጠሩትን
ጭምር ያጠቃልላል ፤ በምዕራብ በኩል የሚዋሰ
ናቸውም የዮርዳኖስ ወንዝ ሲሆን ፥ በሰሜን
እስከ ገሊላ ባሕር ይደርሳል ። 28 እንግዲህ
ለጋድ ነገድ ቤተሰቦች ርስት ሆነው የተሰጡአ
ቸው ከተሞችና መንደሮች እነዚህ ነበሩ ።

### በምሥራቅ በኩል ለሚኖረው ለምናሴ ነገድ እኩሌታ የተመደበ ምድር

29 ሙሴ ከምድሪቱ ከፊሉን ለምናሴ ነገድ
እኩሌታ ቤተሰቦች ሁሉ ርስት አድርጎ ሰጠ ፤
30 ግዛታቸውም ማሕናይምንና ባሳንን ሁሉ ያጠ
ቃልላል ፤ ይህም ባሳን መላውን የባሳን ንጉሥ
የዖግን ግዛት እንዲሁም በባሳን በተለይ ያኢር
ተብላ በምትጠራው ስፍራ የሚገኙትን ስልሳ
መንደሮች ይጨምራል ፤ 31 እርሱም የገለዓድን
እኩሌታ ጨምሮ በባሳን የዖግ መንግሥት ዋና
ከተሞች እስከሆኑት እስከ ዐስታሮትና ኤድረዒ
ይደርሳል ፤ ይህ ሁሉ ከምናሴ ነገድ ለተወለ
ደው ለማኪር ዝርያ ቤተሰቦች ተሰጠ ።

32 በሞአብ ሜዳ በነበረበት ጊዜ ሙሴ በኢያ
ሪኮና በዮርዳኖስ ወንዝ ምሥራቅ ያለውን
ምድር ያከፋፈለው በዚህ ዐይነት ሁኔታ ነበር ።
33 ይህ ሁሉ ሲሆን ሙሴ ለሌዊ ነገድ የሚሰጥ
የርስት ድርሻ አልመደበም ፤ የእነርሱ ርስት
የእስራኤል አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ስለ
ሆነ ፥ ድርሻቸውን የሚያገኙት ለእግዚአብሔር
ከሚቀርበው መሥዋዕት መሆኑን ነግሮአቸ
ዋል ።

## ምዕራፍ 14

### ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ያለው ምድር አከፋፈል

1 ከዚህ የሚከተለው ታሪክ ከዮርዳኖስ ወንዝ
በስተ ምዕራብ ያለው የከነዓን ምድር በእስራ
ኤል ሕዝብ መካከል እንዴት እንደተከፋፈለ
የሚያስረዳ ነው ፤ ካህኑ አልዓዛር ፥ የነዌ ልጅ
ኢያሱና የእስራኤላውያን ነገዶች የቤተሰብ አለ
ቆች ምድሪቱን ለሕዝቡ አከፋፈሉ ። 2 እግዚአብ
ሔር ሙሴን ባዘዘው መሠረት ከዮርዳኖስ ወንዝ
በስተምዕራብ ያለው ግዛት በሙሉ ለዘጠኙ
ነገድ ተኩል በዕጣ ተከፈለ ። 3-4 ከዮርዳኖስ
ወንዝ በስተ ምሥራቅ ያለውን ምድር ግን

13፥14 ፦ ዘዳ. 18፥1 ። 13፥33 ፦ ዘኍ. 18፥20 ፤ ዘዳ. 18፥2 ። 14፥2 ፦ ዘኍ. 26፥52-56 ፤ 34፥13 ።

58 እንዲሁም ሐልሑል ፥ ቤትጹር ፥ ጌዶር ፥
59 ማዕራት ፤ ቢትዓኖትና ኤልትቆን ተብለው
የሚጠሩ በድምሩ ስድስት ከተሞች ሲሆኑ ፥
በዙሪያቸው ያሉትን ታናናሽ ከተሞችን ያጠቃ
ልላሉ ።
60 ይግሞም ቂርያትባዓል ወይም ቂርያትይዓ
ሪምና ራባ ተብለው የሚጠሩ ሁለት ከተሞች
ሲሆኑ ፥ በዙሪያቸው ያሉትን ታናናሽ ከተሞ
ችን ያጠቃልላሉ ።
61 ከእነዚህም ሁሉ ጋር በበረሓማው ምድር
ቤትዐራባ ፥ ሚዲን ፥ ሴካካ ፥ 62 ኒብሻን ፥
የጨው ከተማና ዔንገዲ ተብለው የሚጠሩ በድ
ምሩ ስድስት ከተሞች ሲሆኑ በዙሪያቸው የሚ
ገኙትን ታናናሽ ከተሞችን ያጠቃልላሉ ።
63 ነገር ግን የይሁዳ ሕዝብ በኢየሩሳሌም
የሚኖሩትን ኢያቡሳውያንን ማባረር አልቻ
ሉም ፤ ስለዚህም ኢያቡሳውያን እስከ አሁን
ድረስ በኢየሩሳሌም ከይሁዳ ሕዝብ ጋር ይኖ
ራሉ ።

## ምዕራፍ 16

### ለኤፍሬምና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት ሆኖ የተመደበላቸው ምድር

1 ለዮሴፍ ዝርያዎች የተመደበው የምድራቱ
ደቡባዊ ክፍል በኢያሪኮ አጠገብ ከዮርዳኖስ
ወንዝ ይጀምራል ፤ ይኸውም ከኢያሪኮ ምን
ጮች ምሥራቃዊ ጫፍ በመነሣት ወደ በረሓው
ይዘልቃል ። ከኢያሪኮም ተነሥቶ ወደ ኮረብታ
ማው አገር በመውጣት እስከ ቤትኤል ይደር
ሳል ፤ 2 ከቤትኤልም ተነሥቶ አርካውያን የሚ
ኖሩበትን ዐጣሮትአዳርን በማለፍ ወደ ሎዛ ይዘ
ልቃል ። 3 ከዚያም በምዕራብ በኩል ወደሚገ
ኙት ወደ ያፍሌጣውያን ይዞታ በመዝለቅ እስከ
ታችኛው ቤትሖሮን ይደርሳል ፤ ከዚያም ወደ
ጌዜር ያልፍና መመለሻው የሜድትራኒያን
ባሕር ይሆናል ።
4 የዮሴፍ ዘሮች የሆኑት የኤፍሬምና በምዕ
ራብ በኩል የሰፈረው የምናሴ ነገዶች ይህን
ምድር ርስት አድርገው ወረሱ ።

### የኤፍሬም ድርሻ

5 የኤፍሬም ቤተሰቦች የርስት ድርሻ ይህ
ነው ፤ ድንበራቸው ከዐጣሮትአዳር በምሥራቅ
በኩል ወደ ላይኛው ቤትሖሮን ይወጣል ።
6 ከዚያም አልፎ እስከ ሜድትራኒያን ባሕር ይደ
ርሳል ፤ ሰሜናዊ ድንበራቸውም ሚክመታት
ነው ፤ ከዚያም ተነሥቶ ወደ ታአናት ሺሎ
ታጥፎ በምሥራቅ በኩል በማለፍ ወደ ያኖሐ
ይሄዳል ። 7 ከያኖሐም ተነሥቶ ወደ ዐጣሮትና
ወደ ናዓራት በመዘቅዘቅ ኢያሪኮ ደርሶ መመለ
ሻው የዮርዳኖስ ወንዝ ይሆናል ። 8 ይኸው ድን
በር በምዕራብ በኩል ከታፑሐ ተነሥቶ እስከ
ቃና ወንዝ ይደርስና መመለሻው የሜድትራኒ
ያን ባሕር ይሆናል ፤ ለኤፍሬም ቤተሰቦች ሁሉ
ርስት ሆኖ የተሰጠው ምድር ይህ ነበር ። 9 እር
ሱም በምናሴ ድንበሮች ክልል ውስጥ ያሉትንና
ለኤፍሬማውያን የተሰጡትን ከተሞችና መንደሮ
ችንም ይጨምራል ፤ 10 እነዚህ ኤፍሬማውያን
ግን በጌዜር የሚኖሩ ከነዓናውያንን አላስወጡም
ነበር ፤ ስለዚህም ከነዓናውያን እስከ አሁን ድረስ
በኤፍሬማውያን መካከል ይኖራሉ ፤ ሆኖም ለኤ
ፍሬማውያን የጕልበት ሥራ ለመሥራት ይገደ
ዳሉ ።

## ምዕራፍ 17

### በዮርዳኖስ ምዕራብ የሰፈረው የምናሴ ነገድ እኩሌታ

1 ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ ያለው
ምድር ተከፍሎ የዮሴፍ ታላቅ ልጅ ከሆነው
ከምናሴ ለተወለዱት ቤተሰቦች ተሰጠ ፤ የገለዓድ
አባት ማኪር የምናሴ በኲር ልጅና የጦር ሰው
ነበረ ፤ ስለዚህም ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥ
ራቅ የሚገኙት ገለዓድና ባሳን ለእርሱ ተሰጡ ፤
2 ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ ያለው ምድር ለቀ
ሩት ለምናሴ ቤተሰቦች ተሰጠ ፤ እነርሱም አቢ
ዔዜር ፥ ሔሌቅ ፥ አሥሪኤል ፥ ሼኬም ፥ ሔፌ
ርና ሸሚዳዕ የተባሉት ናቸው ፤ የዮሴፍ ልጅ
የምናሴ ዝርያዎች በተለይ ወንዶቹ እነዚህ
ሲሆኑ ፥ እነርሱም የቤተሰብ አለቆች ነበሩ ።
3 ጸለጰሐድ የሔፌር ልጅ ፥ ሔፌር የገለዓድ
ልጅ ፥ ገለዓድ የማኪር ልጅ ፥ ማኪርም የምናሴ
ልጅ ነው ፤ ታዲያ ይህ ጸለጰሐድ ሴቶች እንጂ
ወንዶች ልጆች አልነበሩትም ፤ አምስቱ ሴቶች
ልጆቹም ማሕላ ፥ ኖዓ ፥ ሖግላ ፥ ሚልካና ቲርጻ
ተብለው ይጠሩ ነበር ። 4 እነርሱም ወደ ካህኑ
አልዓዛር ፥ ወደ ነዌ ልጅ ኢያሱና ወደ መሪ
ዎቹ ቀርበው "እንደ ወንዶች ዘመዶቻችን የር
ስት ድርሻ እንዲሰጠን እግዚአብሔር ሙሴን
አዞታል" አሉአቸው ። ስለዚህም እግዚአብሔር
ባዘዘው መሠረት ለእነርሱ ከወንዶች ዘመዶቻ
ቸው ጋር የርስት ድርሻ ተሰጣቸው ፤ 5 ምናሴ
በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ ከሚገኙት ከገ
ለዓድና ከባሳን ጋር በተጨማሪ ዐሥር ዕጣ እን
ዲደርሰው የተደረገው ስለዚህ ነበር ። 6 ምክንያ
ቱም ሴቶች ዝርያዎቹም እንደ ወንዶች ዝርያ
ዎቹ የርስት ድርሻ ተሰጥቶአቸዋል ። የገለዓ
ድም ምድር ለቀሩት ለምናሴ ዝርያዎች
ተሰጠ ።
7 የምናሴ የርስት ይዞታ ከአሴር ተነሥቶ በሴ
ኬም በስተ ምሥራቅ እስከምትገኘው እስከ
ሚክመታት ይደርስ ነበር ፤ ድንበሩም ወደ

15፡63 ፦ መሳ. 1፡21 ፤ 2ሳሙ. 5፡6 ፤ 1ዜ.መ. 11፡4 ። 16፡10 ፦ መሳ. 1፡29 ። 17፡4 ፦ ዘኍ. 27፡1-7 ።

ደቡብ በማሰፍ የዔንታፑዓሕን ሕዝብ ይጨም
ራል፤ 8 በታፑሐ ዙሪያ የሚገኘውም ምድር
ለምናሴ ተሰጠ፤ በድንበር ላይ የምትገኘው ትን
ሽዋ የታፑሐ ከተማ ግን የኤፍሬም ዘሮች
ይዞታ ነበረች። 9 ድንበሩም ከዚያ ተነሥቶ
እስከ ቃና ወንዝ ይደርሳል፤ ከወንዙ በስተ
ደቡብ የሚገኙት ከተሞች ምንም እንኳ በም
ናሴ ግዛት ክልል ውስጥ ቢሆኑም የኤፍሬም
ይዞታዎች ነበሩ፤ የምናሴ ድንበር በሰሜን
በኩል ከወንዙ እየተዋሰነ መመለሻው የሜድት
ራኒያን ባሕር ነበር፤ 10 ከዚህም የተነሣ የሁለ
ቱም ምዕራባዊ ወሰን የሜድትራኒያን ባሕር
ሆኖ ኤፍሬም በደቡብ፥ ምናሴ በሰሜን እንዲስ
ፍሩ ተደረገ፤ አሴር በሰሜናዊ ምዕራብ ይሳኮር
ደግሞ በሰሜናዊ ምሥራቅ ሰፈሩ። 11 በይሳኮ
ርና በአሴር ግዛቶች ክልል ውስጥ በጠረፍ የም
ትገኘውን ዶርን፥ ዔንዶርን፥ ታዕናክን፥ መጊ
ዶንና በዙሪያቸው ያሉ ታናናሽ ከተሞችን
ጨምሮ ቤትሻንና ዩብለዓም ተብለው የሚጠ
ሩት ቦታዎች በዙሪያቸው ከሚገኙት ታናናሽ
ከተሞች ጋር የምናሴ ይዞታዎች ሆኑ።
12 ይሁን እንጂ የምናሴ ሕዝብ በነዚያ ከተሞች
የሚኖሩትን ሕዝብ ማባረር አልተቻላቸውም፤
ስለዚህም ከነዓናውያን በዚያ መኖርን ቀጠሉ፤
13 እስራኤላውያን በኀይል እየበረቱ ቢሄዱም
እንኳ ከነዓናውያንን ሁሉ አላባረሩአቸውም፤
ነገር ግን የጕልበት ሥራ እንዲሠሩላቸው ያስገ
ድዱአቸው ነበር።

### ኤፍሬምና ምዕራብ ምናሴ ተጨማሪ መሬት ጠየቁ

14 የዮሴፍ ዝርያዎች ወደ ኢያሱ ቀርበው
"ስለምን ከምድሪቱ አንድ ዕጣ ብቻ እንድንወ
ርስ አደረግህ? እኛ ብዙዎች ነን፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር ባርኮናል" አሉት። 15 ኢያሱም
መልሶ "ብዙዎች ከሆናችሁና ኮረብታማይቱ
የኤፍሬም ምድር ትንሽ ከሆነችባችሁ፥ ፈሪዛ
ውያንና ረፋያውያን ወደሚኖሩበት ምድር ሄዳ
ችሁ ጫካውን መንጥሩ" አላቸው። 16 እነር
ሱም "ኮረብታማይቱ አገር ለእኛ በቂ አይደለ
ችም፤ ከዚህም ሁሉ ጋር በኢይዝራኤል ሸለቆ
በቤትሻንና በዙሪያዋ ባሉት ታናናሽ ከተሞችና
በሜዳማው አገር የሚኖሩ ከነዓናውያን ብዙ
የብረት ሠረገላዎች አሉአቸው" ሲሉ መለሱ።
17 ኢያሱም ለኤፍሬምና በዮርዳኖስ ምዕራብ
ለሰፈረው ለምናሴ ነገዶች እንዲህ አላቸው፥
"እናንተ በእውነት ብዙዎች ናችሁ፤ በኀይ
ልም ብርቱዎች ናችሁ፤ ከአንድ የሚበልጥ
ድርሻ ሊኖራችሁ ይገባል፤ 18 ስለዚህ ኮረብታ
ማው አገር የእናንተ ይሆናል፤ ጫካም ቢሆን
መንጥራችሁ ዳር እስከ ዳር የራሳችሁ ርስት
አድርጉት፤ ስለ ከነዓናውያን ጕዳይ የሆነ እንደ
ሆነ ምንም የብረት ሠረገላዎች ቢኖራቸውና
ምንም ብርቱዎች ቢሆኑ ነቃቅላችሁ ልታባርሩ
አቸው ትችላላችሁ።"

## ምዕራፍ 18

### የቀረው ምድር አከፋፈል

1 ድል አድርገው ምድሪቱን ከያዙ በኋላ
መላው የእስራኤል ሕዝብ በሴሎ ተሰብስቦ እግ
ዚአብሔር የሚመለክበትን ድንኳን ተከሉ።
2 ከእስራኤልም ሕዝብ መካከል ገና የርስት
ድርሻ ያላገኙ ሰባት ነገዶች ነበሩ፤ 3 ስለዚህም
ኢያሱ ለእስራኤል ሕዝብ እንዲህ አለ፥ "ገብታ
ችሁ የቀድሞ አባቶቻችሁ አምላክ የሆነ እግዚ
አብሔር የሰጣችሁን ምድር ሳትወርሱ የምትቆ
ዩት እስከ መቼ ነው? 4 ከእያንዳንዱ ነገድ
ሦስት ሦስት ሰዎች ምረጡልኝ፤ እኔም እያንዳ
ንዱ ነገድ መውረስ የሚገባውን የርስት ድርሻ
ለማወቅ የምድሪቱን ሁኔታ አጥንተው እንዲመዘ
ግቡ በመላ አገሪቱ እልካቸዋለሁ፤ ከዚያም
በኋላ ተመልሰው ወደ እኔ ይመጣሉ። 5 እነር
ሱም የሚያጠኑት ምድር ለሰባቱ ነገድ ይከፋፈ
ላል፤ ይሁዳ በደቡብ በኩል፥ ዮሴፍም በሰሜን
በኩል የተመደበላቸውን የርስት ድርሻ ይዘው
ይኖራሉ፤ 6 የእነዚህን ሰባት ክፍያዎች የሚገል
ጠውንም ማስረጃ በጽሑፍ አድርጋችሁ አምጡ
ልኝ፤ አምላካችን የሆነውን እግዚአብሔርን
ለመጠየቅ ዕጣ እጥልላችኋለሁ። 7 ይሁን እንጂ
ሌዋውያን ከሌሎቻችሁ ጋር የርስት ድርሻ አይ
ኖራቸውም፤ ምክንያቱም የእነርሱ ድርሻ ካህ
ናት ሆነው እግዚአብሔርን ማገልገል ነው፤
የሮቤልና የጋድ እንዲሁም የምናሴ ነገድ እኩ
ሌታ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ በኩል
የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ የሰጣቸውን
ርስት አስቀድመው ወርሰዋል።"
8 ሰዎቹም የምድሪቱን ሁኔታ ለማጥናት ከመ
ሄዳቸው በፊት ኢያሱ፥ "ወደ ምድሪቱ ሁሉ
ሂዱ፤ አቀማመጥዋንም አጥንታችሁ መዝግቡ፤
ወደ እኔም ተመልሳችሁ ኑ፤ እኔም በዚህ
በሴሎ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ
ዕጣ እጥልላችኋለሁ" የሚል መመሪያ ሰጣ
ቸው፤ 9 ሰዎቹም በአገሪቱ በመላ ተዘዋወሩ፤
ከተሞቹንም ሁሉ መዝግበው ምድሪቱ ለሰባት
ነገድ እንዴት እንደምትከፈል በጽሑፍ ገለጡ፤
ከዚህም በኋላ ኢያሱ ወዳለበት ወደ ሴሎ ተመ
ልሰው መጡ፤ 10 ኢያሱም እግዚአብሔርን ለመ
ጠየቅ ዕጣ አወጣላቸው፤ ለቀሩትም ለእስራኤል
ነገዶች ለእያንዳንዳቸው ተመጣጣኝ የሆነ የር
ስት ድርሻ ተመደበላቸው።

---

17፥12-13 ፡- መሳ. 1፥27-28።

### ለብንያም ርስት ሆኖ የተመደበ ምድር

11 በመጀመሪያ የተመደበው ለብንያም ነገድ
ቤተሰቦች የተሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤ ለእነ
ርሱም የተመደበላቸው ርስት የሚገኘው በይሁ
ዳና በዮሴፍ ነገዶች መካከል ነበር፤ 12 በሰሜን
በኩል የሚገኘውም ድንበራቸው ከዮርዳኖስ
ወንዝ ተነሥቶ ወደ ኢያሪኮ ሰሜን ሸቀብ ይወ
ጣና በምዕራብ አቅጣጫ በሚገኘው ኮረብታማ
አገር በኩል እስከ ቤትአዌን በረሓ ይደርሳል፤
13 ይኸው ድንበር በደቡብ በኩል ቀድሞ ሎዛ
ተብላ ትጠራ ወደነበረችው ወደ ቤትኤል ይወ
ጣና በታችኛው ቤትሖሮን ተራራ በኩል ወደ
ዐጣሮትአዳር ይወርዳል። 14 ይኸው ድንበር
በሌላም አቅጣጫ ከዚህ ተራራ በስተ ምዕራብ
ወደ ደቡብ በመታጠፍ የይሁዳ ነገድ ይዞታ
ወደ ሆነችው ወደ ቂርያትባዓል ወይም ቂርያት
ይዓሪም ያልፋል፤ ይህም በምዕራብ በኩል የሚ
ገኘው ድንበር ነው፤ 15 የደቡቡም ድንበር በም
ዕራብ በኩል ከቂርያትይዓሪም ተነሥቶ ወደ
ኔፍቶሐ ምንጮች ያልፋል። 16 ከዚያም በራፋ
ይም ሸለቆ ሰሜናዊ መጨረሻ በሚገኘው በሂ
ኖም ሸለቆ ትይዩ ወደ ተራራው ግርጌ ይወር
ዳል፤ እንደገናም ተነሥቶ ከኢያቡሳውያን ተረ
ተር ደቡባዊ ክፍል በሚገኘው በሂኖም ሸለቆ
በኩል ወደ ዔንሮጌል ያልፋል፤ 17 በስተሰሜን
በኩል ወደ ዓንሼሜሽ ይታጠፍና በአዱሚም
መተላለፊያ ትይዩ ወደሚገኘው ወደ ገሊሎት
ይመለሳል፤ ከዚያም ተነሥቶ ቀድሞ በሮቤል
ልጅ ስም ይጠራ ወደነበረው ወደ ቦሄን ድን
ጋይ በመውረድ፥ 18 በስተበሜን በኩል በዮርዳ
ኖስ ሸለቆ ትይዩ የሚገኘውን ተረተር አልፎ
ይሄዳል፤ ከዚያም በኋላ ወደ ሸለቆው ይወር
ዳል፤ 19 የቤትሖግላን ተረተር ሰሜንም ያልፍና
የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ ስርጎ ወደሚገባበት
በሙት ባሕር ሰሜናዊ ጫፍ ላይ ሲደርስ ያበ
ቃል። እንግዲህ የደቡቡ ድንበር ይህ ሲሆን፥
20 የምሥራቁ ድንበር የዮርዳኖስ ወንዝ ነው፤
የብንያም ነገድ ቤተሰቦች ርስት አድርገው የወ
ረሱት ምድር ድንበሮቹ እነዚህ ነበሩ።
21 የብንያም ነገድ ቤተሰቦች ይዞታ የሆኑት
ከተሞችም ኢያሪኮ፥ ቤትሖግላ፥ ዔሜቀጺጽ፥
22 ቤትዐራባ፥ ጸማራይም፥ ቤትኤል፥
23 ዐዊም፥ ፋራ፥ ዖፍራ፥ 24 ከፋርዐሞናይ፥
ዖፍኒና፥ ጌባዕ ተብለው የሚጠሩ በድምሩ
ዐሥራ ሁለት ከተማዎች ሲሆኑ፥ በዙሪያቸው
የሚገኙ ታናናሽ ከተሞችንም ይጨምራሉ።
25 በተጨማሪም ገባዖን፥ ራማ፥ በኤሮት፥
26 ምጽጳ፥ ከፊራ፥ ሞጻ፥ 27 ሬቄም፥ ይርጵ
ኤል፥ ታርኣላ፥ 28 ጼላዕ፥ ኤሌፍ፥ ኢያቡስ
(ኢየሩሳሌም) ጊብዓና ቂርያትይዓሪም ተብለው
የሚጠሩ በድምሩ ዐሥራ አራት ከተሞች
ሲሆኑ፥ በዙሪያቸው የሚገኙትን ታናናሽ ከተ
ሞችንም ይጨምራሉ። እንግዲህ የብንያም
ነገድ ቤተሰቦች ርስት አድርገው የወረሱት
ምድር ይህ ነው።

## ምዕራፍ 19

### ለስምዖን ርስት ሆኖ የተመደበ ምድር

1 ሁለተኛው ምድብ ለስምዖን ቤተሰቦች የተ
ሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤ ግዛቱም ለይሁዳ
ነገድ እስከተመደበው ምድር ድረስ ገባ ያለ
ነበር፤ 2 እርሱም ቤርሳቤህ፥ ሼባዕ፥ ሞላዳ፥
3 ሐጻርሹዓል፥ ባላ፥ ዔጼም፥ 4 ኤልቶላድ፥
በቱል፥ ሖርማ፥ 5 ጺቅላግ፥ ቤትማርካቦት፥
ሐጻርሱሳ፥ 6 ቤትለባኦትና ሻሩሔን የተባሉትን
ዐሥራ ሦስት ከተሞች በዙሪያቸው ካሉት ታና
ናሽ ከተሞች ጋር ይጨምር ነበር።
7 ከዚህም ሁሉ ጋር በተጨማሪ ዓይን፥
ሪሞን፥ ዔቴርና ዐሻን ተብለው የሚጠሩትን
አራት ከተሞች በዙሪያቸው የሚገኙ ታናናሽ
ከተሞችን ያጠቃልል ነበር፤ 8 በደቡብ በኩል
እስከምትገኘው እስከ ባዕላትበኤር (ራማ) ድረስ
በእነዚህ ከተሞች ዙሪያ ያሉትን ታናናሽ ከተ
ሞች ሁሉ ያጠቃልል ነበር፤ የስምዖን ነገድ
ቤተሰቦች ርስት አድርገው የተቀበሉት ምድር
ይህ ነበር። 9 ለይሁዳ የተመደበው ድርሻ ከሚያ
ስፈልገው በላይ ስለነበር ከእርሱ ተከፍሎለት
ለስምዖን ነገድ ተሰጠ።

### ለዛብሎን ርስት ሆኖ የተመደበ ምድር

10 ሦስተኛው ምድብ ለዛብሎን ነገድ ቤተሰ
ቦች የተሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤ እነርሱም
የተቀበሉት ምድር እስከ ሣሪድ ይደርሳል፤
11 ድንበሩም ከዚያ በመነሣት ከዳባሼትና በዮቅ
ነዓም ምሥራቅ ከሚገኘው ወንዝ እየተዋሰነ
በምዕራብ በኩል እስከ ማርዓላ ይደርሳል።
12 ከሣሪድም ባሻገር በምሥራቅ በኩል ወደ
ኪስሎትታቦር አልፎ እስከ ዳብራትና እስከ
ያፊዓ ይደርሳል፤ 13 እንደገናም በዚሁ በምሥ
ራቅ በኩል ወደ ሪሞን በሚወስደው መንገድ
ወደ ኔዓ አቅጣጫ ይታጠፍና ወደ ጋትሔፌርና
ወደ ዒትቃጺን ያዘልቃል፤ 14 የሰሜኑም ድን
በር መመለሻው የይፍታሕኤል ሸለቆ ሆኖ ወደ
ሐናቶን አቅጣጫ ይታጠፋል፤ 15 እርሱም
ቃጣት፥ ናህላል፥ ሺምሮን፥ ይዳላና ቤተል
ሔም ተብለው የሚጠሩትን ዐሥራ ሁለት ከተ
ሞችና በዙሪያቸው ያሉትን ታናናሽ ከተሞች
ያጠቃልላል፤ 16 ስለዚህም እነዚህ ታላላቅና
ታናናሽ ከተሞች ለዛብሎን ነገድ ቤተሰቦች
ርስት ሆኖ በተሰጠው ምድር ክልል ውስጥ
የሚገኙ ናቸው።

19፥2-8 ፦ 1ዜ.መ. 4፥28-33።

### ለይሳኮር ርስት ሆኖ
### የተመደበ ምድር

[17] አራተኛው ምድብ ለይሳኮር ነገድ ቤተሰ
ቦች የተሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤ [18] የምድ
ሩም ክልል ኢይዝራኤልን፥ ከሱሎትን፥ ሹኔ
ምን፥ [19] ሐፍራይምን፥ ሺኦንን፥ አናሐራትን፥
[20] ራቢትን፥ ቂሽዮንን፥ አቤጽን፥ [21] ሬሜትን፥
ዔንጋኒምን፥ ዔንሐዳንና ቤትጳጼጽን ይጨም
ራል፤ [22] ድንበሩም መመለሻው የዮርዳኖስ
ወንዝ ሆኖ፥ ከታቦር፥ ከሻሐጹማና ከቤትሼ
ሜሽ ጋር ይዋሰናል፤ እርሱም ዐሥራ ስድስት
ከተሞችንና በዙሪያቸው ያሉትን ታናናሽ ከተ
ሞች ሁሉ ያጠቃልላል፤ [23] ስለዚህም እነዚህ
ከተሞችና መንደሮቻቸው ለይሳኮር ነገድ ቤተሰ
ቦች ርስት ሆኖ በተሰጠው ምድር ክልል ውስጥ
የሚገኙ ናቸው።

### ለአሴር ርስት ሆኖ
### የተመደበ ምድር

[24] አምስተኛው ምድብ ለአሴር ነገድ ቤተሰ
ቦች የተሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤ [25] የምድ
ሩም ክልል ሔልቃትን፥ ሐሊን፥ ቤጤንን፥
አክሻፍን፥ [26] አላሜሌክን፥ ዓምዓድንና ሚሽአ
ልን ይጨምራል፤ በምዕራብም ከቀርሜሎስና
ከሺሖርሊብናት ይዋሰናል፤ [27] ወደ ምሥራቅም
ይታጠፍና ድንበሩ ወደ ቤትዳጎን ወደ ነዒ
ኤል በሚወስደው መንገድ ከዛብሎንና ከይፍታ
ሕኤል ሸለቆ እየተዋሰነ ወደ ቤትዓሜቅና ይዘል
ቃል። በሰሜንም ወደ ካቡል፥ [28] ወደ ዔብ
ሮን፥ ረሖብ፥ ሐሞንና ቃና አልፎ እስከ ሲዶና
ይደርሳል። [29] ድንበሩ እስከተመሸገችው እስከ
ጢሮስ ከተማ ይደርስና ወደ ራማ ይታጠፋል፤
ከዚያም መመለሻው የሜድትራኒያን ባሕር ሆኖ
ወደ ሖሳ ይታጠፋል፤ እርሱም ማሐላብ፥ አክ
ዚብ፥ [30] ዑማ፥ አፌቅና ረሖብ ተብለው የሚ
ጠሩትን ሃያ ሁለት ከተሞችና በዙሪያቸው የሚ
ገኙ ታናናሽ ከተሞችንም ይጨምራል፤ [31] ስለ
ዚህ እነዚህ ታላላቅና ታናናሽ ከተሞች ለአሴር
ነገድ ቤተሰቦች ርስት ሆኖ በተሰጠው ምድር
ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

### ለንፍታሌም ርስት ሆኖ
### የተመደበ ምድር

[32] ስድስተኛው ምድብ ለንፍታሌም ነገድ
ቤተሰቦች የተሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤
[33] ድንበሩም ከሔሌፍ፥ በመነሣት በአዳሚኔቄብና
በያሚኒያ በኩል መመለሻው የዮርዳኖስ ወንዝ
ሆኖ እስከ ላቁም ድረስ እስከ ጻዕናኒም ወርካ
ይዘልቃል። [34] ከዚህ በኋላ ድንበሩ በምዕራብ
በኩል ወደ አዝኖትታቦር ይታጠፋል፤ ከዚያም
በመነሣት በደቡብ በኩል ከዛብሎን ምዕራብ
በኩል ከአሴርና ከዮርዳኖስ ምሥራቅ እየተዋሰነ
ወደ ሑቆቅ ይደርሳል፤ [35] እንዲሁም የተመሸ
ጉት ከተሞች ጺዲም፥ ጼር፥ ሐማት፥
ራቃት፥ ኪኖሬት፥ [36] አዳማ፥ ራማ፥ ሐጾር፥
[37] ቄዴሽ፥ ኤድረዒ፥ ዔንሐጾር፥ [38] ይርኦን፥
ሚግዳልኤል፥ ሖሬም፥ ቤትዐናትና ቤትሼሜሽ
ተብለው የሚጠሩ ዐሥራ ዘጠኝ ከተሞች በዙሪ
ያቸው ካሉት ታናናሽ ከተሞች ጋር ከዚህ
ክልል ውስጥ ይገኛሉ፤ [39] ስለዚህ እነዚህ ታላላ
ቅና ታናናሽ ከተሞች ለንፍታሌም ነገድ ቤተሰ
ቦች ርስት ሆኖ በተሰጠው ምድር ክልል ውስጥ
የሚገኙ ናቸው።

### ለዳን ርስት ሆኖ
### የተመደበ ምድር

[40] ሰባተኛው ምድብ ለዳን ነገድ ቤተሰቦች
የተሰጠው የርስት ድርሻ ነበር፤ [41] የምድሩም
ክልል ጾርዓን፥ ኤሽታኦልን፥ ዒርሼሜሽን፥
[42] ሻዓልቢምን፥ አያሎንን፥ ይትላን፥ [43] ኤሎ
ንን፥ ቲምናን፥ ዔቅሮንን፥ [44] ኤልተቄን፥ ጊበ
ቶንን፥ ባዕላትን፥ [45] ይሁድን፥ በኔበራቅን፥
ጋትሪሞንን፥ [46] ሜያርቆን፥ ራቆንና እንዲሁም
በኢዮጴ ዙሪያ ያለውን ግዛት ጭምር ያጠቃል
ላል። [47] የዳንም ሕዝብ ይህን ምድር ለመውረስ
የማይመች ሆኖ ባገኙት ጊዜ ወደ ላዪሽ ሄደው
አደጋ በመጣል ከተማይቱን ያዙ፤ ሕዝብዋንም
ፈጅተው የራሳቸው ይዞታ አደረጉአት፤ በዚ
ያም ሰፈሩ፤ ላዪሽ ትባል የነበረችውን ከተማ
ስሚን ለውጠው በቀድሞ አባታቸው ስም ዳን
ብለው ጠሩአት፤ [48] ስለዚህ እነዚህ ታላላቅና
ታናናሽ ከተሞች ለዳን ነገድ ቤተሰቦች ርስት
ሆኖ በተሰጠው ምድር ክልል ውስጥ የሚገኙ
ናቸው።

### ለኢያሱ ርስት ሆኖ የተመደበ
### የመጨረሻው ምድር

[49] የእስራኤል ሕዝብ ምድሪቱን ተከፋፍለው
በጨረሱ ጊዜ ለነዌ ልጅ ኢያሱ ከምድሪቱ ከፍ
ለው የራሱን ድርሻ ሰጡት፤ [50] እግዚአብሔርም
ባዘዘው መሠረት በኰረብታማው በኤፍሬም
አገር እንዲሰጡት የጠየቃቸውን ቲምናትሴራሕ
ተብላ የምትጠራውን ከተማ ሰጡት፤ ያችንም
ከተማ እንደገና ሠርቶ መኖሪያው አደረጋት።
[51] ካህኑ አልዓዛር፥ የነዌ ልጅ ኢያሱና የእስ
ራኤልን ነገዶች የሚወክሉት የቤተሰብ መሪ
ዎች እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት በሴሎ
ድንኳን ደጃፍ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠ
የቅ ዕጣ እየጣሉ ይህን ሁሉ የርስት ድርሻ አከ
ፋፈሉ። በዚህም ዐይነት ሁኔታ ምድሪቱን አከ
ፋፍለው ጨረሱ።

19፥47 ፦ መሳ 18፥27-29።

## ምዕራፍ 20

### የመማጸኛ ከተሞች

1 ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ኢያሱን፥ 2 ለእ
ስራኤል ሕዝብ እንዲህ ብለህ ንገር አለው፥
“ሙሴ እንዲነግራችሁ ባዘዝሁት መሠረት የመ
ማጸኛ ከተሞችን ምረጡ፤ 3 ማንም ሰው ሳያ
ውቅ በድንገት ሰው ቢገድል፥ ወደዚያ በመ
ሄድ ሊበቀለው ከሚፈልገው ሰው ይድናል፤
4 እርሱም ከእነዚህ ከተሞች ወደ አንዲቱ ፈጥኖ
በመሄድ በከተማይቱ መግቢያ በር ወደሚገኘው
ፍርድ ሸንጎ ቀርቦ የሆነውን ነገር ሁሉ ለመሪ
ዎቹ ይገልጣል፤ ከዚያም በኋላ ወደ ከተማይቱ
እንዲገባ ይፈቅዱለታል፤ የሚኖርበትንም ስፍራ
ይሰጡትና በዚያ ይቆያል፤ 5 ሊበቀለው የሚፈ
ልገው ሰው ተከትሎት ቢመጣ፥ የከተማይቱ
ሰዎች እርሱን አሳልፈው መስጠት አይገባቸ
ውም፤ ሰውን የገደለው በድንገተኛ አጋጣሚ
እንጂ በቂም በቀል ተነሣሥቶ ስላይደለ፥ ከአ
ደጋ ሊጠብቁት ይገባል። 6 በሸንጎ ቀርቦ ፍርድ
እስከሚቀበልና በዘመኑ ያለው ሊቀ ካህናት እስ
ከሚሞትበት ጊዜ ድረስ በዚያች ከተማ ሊቆይ
ይችላል፤ ከዚያም በኋላ ሸሽቶ ወደወጣበት
ከተማ በመመለስ ወደቤቱ ይገባል።”

7 ስለዚህም ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምዕራብ
የንፍታሌም ይዞታ በሆነችው በኰረብታማዋ
አገር በምትገኘው በገሊላ፥ ቄዴሽ ተብላ የም
ትጠራውን፥ በኰረብታማው በኤፍሬም አገር
ሴኬምንና በኰረብታማው በይሁዳ ምድር ኬብሮ
ንን መርጠው ለዩ፤ 8 በምሥራቅ ዮርዳኖስ፥
ከኢያሪኮም በስተ ምሥራቅ ከፍ ብሎ በሚገ
ኘው በረሓማ አገር፥ በሮቤል ግዛት ውስጥ የም
ትገኘውን ቤጼርን፥ በጋድ ግዛት ውስጥ በገለ
ዓድ የምትገኘውን ራሞትንና በምናሴ ግዛት በባ
ሳን የምትገኘውን ጎላንን መርጠው ለዩ፤ 9 ለእ
ስራኤል ሕዝብና በመካከላቸውም ለሚኖሩ
የውጭ አገር ሰዎች መማጸኛ ይሆኑ ዘንድ የተ
መረጡ ከተሞች እነዚህ ነበሩ፤ ማንም ሰው
በድንገተኛ አጋጣሚ ሰው ቢገድል፥ በሸንጎም
ሳይፈረድበት እንዳይገደል ከእነዚያ ከተሞች
ወደ አንዲቱ ሄዶ ሊበቀለው ከሚፈልገው ሰው
እጅ ያመልጣል።

## ምዕራፍ 21

### ለሌዋውያን የተመደቡ ከተሞች

1 የሌዊ ነገድ ቤተሰቦች መሪዎች ወደ ካህኑ
አልዓዛር፥ ወደ ነዌ ልጅ ኢያሱና ወደ እስራ
ኤል ሕዝብ ነገዶች ቤተሰብ መሪዎች ሄዱ፤
2 በዚያም በከነዓን ምድር በምትገኘው በሴሎ
ወደ እነርሱ ፊት ቀርበው “እግዚአብሔር
በሙሴ አማካይነት የምንኖርባቸው ከተሞችና
በዙሪያቸውም ለከብቶቻችን ግጦሽ የሚሆን
መሬት እንዲሰጠን አዝዞአል” አሉአቸው።
3 ስለዚህም በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት
የእስራኤል ሕዝብ ለሌዋውያን የተወሰኑ ከተሞ
ችንና ለከብት ግጦሽ የሚሆን መሬት ከግዛቶቻ
ቸው ከፍለው ሰጡአቸው።

4 በመጀመሪያ ከተሞችን የተረከቡ ከሌዊ
ነገድ የተወለደው የቀሃት ጐሳ ቤተሰቦች ነበሩ፤
የካህኑ አሮን ዝርያዎች የሆኑ ቤተሰቦች ከይሁዳ
ከስምዖንና ከብንያም ነገዶች ግዛት ዐሥራ
ሦስት ከተሞች ተመደቡላቸው፤ 5 ለቀረው ለቀ
ሃት ጐሳ ከኤፍሬም፥ ከዳንና ከምዕራብ ምናሴ
ዐሥር ከተሞች ተመደቡለት።

6 ለጌርሾን ጐሳ ከይሳኮር፥ ከአሴር፥ ከንፍታ
ሌምና በባሳን ካለው ከምሥራቅ ምናሴ ግዛት
ተከፍለው ዐሥራ ሦስት ከተሞች ተመደቡ
ለት።

7 ለመራሪ ጐሳ ቤተሰቦችም ከሮቤል፥ ከጋ
ድና ከዛብሎን ግዛቶች ተከፍለው ዐሥራ ሁለት
ከተሞች ተመደቡላቸው።

8 በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር ባዘዘው
መሠረት የእስራኤል ሕዝብ እነዚህን ከተሞችና
የግጦሽ ምድር ለሌዋውያን በዕጣ አካፈሉአ
ቸው። 9-10 ከይሁዳና ከስምዖን ግዛቶች ተከፍ
ለው፥ ከሌዊ ነገድ ለተወለደው የቀሃት ጐሳ
ለሆኑት የአሮን ዝርያዎች የተሰጡት ከተሞች
እነዚህ ናቸው፤ የእነርሱም ምድብ የመጀመ
ሪያ ሆኖ፥ 11 የአርባዕን ከተማ ተረከቡ፤ አርባዕ
የዐናቅ አባት ነበር፤ ይህችም አርባዕ አሁን በኰ
ረብታማው በይሁዳ አገር በዙሪያዋ ካለው የግ
ጦሽ ምድር ጭምር ኬብሮን ተብላ ትጠራለች፤
12 ይሁን እንጂ በከተማይቱ የሚገኘው የእርሻ
ቦታና በክልልዋ ውስጥ ያሉት መንደሮች አስቀ
ድሞ ለይፉኔ ልጅ ለካሌብ ርስት ሆነው ተሰጥ
ተዋል።

13 ከመማጸኛ ከተሞች አንድዋ ከሆነችው
ከኬብሮን ጋርም በተጨማሪ ለካህኑ ለአሮን
ዘሮች ከዚህ የሚከተሉት ከተሞች ተመደቡላ
ቸው፤ እነርሱም ሊብና፥ 14 ያቲር፥ ኤሽተ
ሞዓ፥ 15 ሖሎን፥ ደቢር፥ 16 ዓይን፥ ዩጣና
ቤትሼሜሽ ተብለው የሚጠሩት ከግጦሽ ምድ
ራቸው ጭምር ከይሁዳና ከስምዖን ምድር
ተከፍለው የተሰጡ ዘጠኝ ከተሞች ናቸው።
17 ከብንያም ግዛት ተከፍለው አራት ከተሞች
ተሰጡአቸው። እነርሱም ከግጦሽ ምድራቸው
ጋር ገባዖን፥ ጌባዕ፥ 18 ዐናቶትና ዐልሞን
ተብለው የሚጠሩት ናቸው። 19 የአሮን ዝርያ
ዎች ለሆኑት ካህናት ከግጦሽ ምድራቸው
ጋር በድምሩ ዐሥራ ሦስት ከተሞች ተመደቡ
ላቸው።

20፥1-9 ፦ ዘኍ. 35፥6-32፤ ዘዳ. 4፥41-43፤ 19፥1-13። 21፥2 ፦ ዘኍ. 35፥1-8።

9 በዚህም ዐይነት ሁኔታ የሮቤል፥ የጋድና
በምሥራቅ ያሉት የምናሴ ነገዶች ወደየመኖሪያ
ርስታቸው ተመልሰው ሄዱ፤ እነርሱም ተሰናብ
ተው በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር ባዘዛ
ቸው መሠረት ቀድሞ ርስት አድርገው ወደ
ወረሱአት ወደ ገለዓድ ምድር በተመለሱበት
ጊዜ ሌሎቹ እስራኤላውያን በሴሎ ነበሩ።

በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ የተሠራ መሠዊያ

10 የሮቤል፥ የጋድና የምሥራቅ ምናሴ ነገ
ዶች በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ በከነዓን ምድር
ወደሚገኘው ወደ ገሊሎት እንደደረሱ በወንዙ
አጠገብ አስደናቂ የሆነ ታላቅ መሠዊያ ሠሩ፤
11 የቀሩትም የእስራኤል ሕዝብ "እነሆ እድ
ምጡ! የሮቤል፥ የጋድና በምሥራቅ ያሉት
የምናሴ ነገዶች ሕዝብ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠ
ገብ በከነዓን ምድር በምትገኘው የእኛ ይዞታ
በሆነችው በገሊሎት መሠዊያ ሠርተዋል"
የሚል ወሬ ሰሙ፤ 12 የእስራኤልም ሕዝብ ይህ
ንን በሰሙ ጊዜ ሁሉም በአንድነት ወደ ሴሎ
መጥተው በመሰብሰብ በምሥራቅ ነገዶች ላይ
ሊዘምቱ ተዘጋጁ።
13 ይህም ከመሆኑ በፊት የእስራኤል ሕዝብ
የካህኑን የአልዓዛርን ልጅ ፊንሐስን በገለዓድ
ምድር ወደሚገኙት ወደ ሮቤል፥ ወደ ጋድና
በምሥራቅ ወደሚኖሩት የምናሴ ነገዶች ሕዝብ
ላኩት፤ 14 ከፊንሐስም ጋር ዐሥር ታላላቅ
ሰዎች ነበሩ፤ እነዚህም እያንዳንዱ በምዕራብ
ከሚገኙት ነገዶች የተውጣጡ በየጐሳቸው የቤ
ተሰብ መሪዎች የሆኑ ናቸው፤ 15 እነርሱም የሮ
ቤል፥ የጋድና በምሥራቅ የሚኖሩት የምናሴ
ሕዝብ ወደሚኖሩባት ወደ ገለዓድ ምድር
መጡ፤ 16 እዚያም ደርሰው ለመላው የእግዚአ
ብሔር ሕዝብ ሲናገሩ እንዲህ አሉአቸው፥
"በእስራኤል አምላክ ላይ ስለምን ይህንን ክፉ
ነገር አደረጋችሁ? ምክንያቱም ይህንን መሠዊያ
ለራሳችሁ በመሥራታችሁ በእግዚአብሔር ላይ
አምፃችኋል፤ እርሱንም መከተል ትታችኋል፤
17 እግዚአብሔር ሕዝቡን በሚቀሥፍ በሽታ
በቀጣ ጊዜ በፒዖር የሠራነውን ኃጢአት ረሳች
ሁትን? ከእርሱ የተነሣ እነሆ እስከ አሁን
ድረስ እየተሠቃየን ነን፤ ታዲያ ያ ኃጢአት
አይበቃምን? 18 እናንተስ አሁን እግዚአብሔርን
ለመከተል እምቢ ማለታችሁ ነውን? እናንተ
ዛሬ በእግዚአብሔር ላይ ብታምፁ፥ እርሱ ነገ
በመላው እስራኤል ላይ ይቈጣል፤ 19 እንግዲህ
ይህ ያላችሁበት ምድር ለአምልኮት የማይመች
ቢሆን፥ የእርሱ ድንኳን ወደ ተተከለችበት
ስፍራ ወደ እግዚአብሔር ኑ፤ የእኛ ይዞታ ከሆ
ነው ምድር የሚስማማችሁን ቦታ ያዙ፤ ነገር
ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ላይ አታ
ምፁ፤ ወይም አስቀድሞ ከተሠራው ከአምላካ
ችን ከእግዚአብሔር መሠዊያ ጋር በተጨማሪ
ሌላ መሠዊያ በመሥራት እኛንም ጭምር ዐመ
ፀኞች አታድርጉን። 20 የዛራሕ ልጅ ዓካን መደ
ምሰስ ስለሚገባቸው ነገሮች ለመታዘዝ እምቢ
ማለቱን አስታውሱ፤ በዚያም ምክንያት እግዚአ
ብሔር መላውን የእስራኤል ሕዝብ ተቈጥቶ
አል፤ ታዲያ በኃጢአቱ ምክንያት የሞተ አካን
ብቻ አይደለም።"
21 የሮቤል፥ የጋድና በምሥራቅ የሚኖሩት
የምናሴ ነገዶች ሕዝብም ለምዕራብ ነገዶች የቤ
ተሰብ መሪዎች እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው፥
22 "ከሁሉ የሚበልጥ ኀያል እግዚአብሔር
ነው! እርሱ የሁሉ ጌታ ነው! እርሱ ከሁሉ
የሚበልጥ ኀያል አምላክ ነው! እኛ ስለምን
ይህንን እንደሠራን እርሱ ያውቃል! እናንተም
ስለምን እንደሠራነው እንድታውቁት እንፈል
ጋለን፤ በእውነት ካመፅንና በእግዚአብሔር ላይ
ያለንን እምነት አጕድለን ከተገኘን፥ በሕይወት
እንድንኖር አትፍቀዱልን፤ 23 ለእግዚአብሔር
የማንታዘዝ ከሆንና የሠራነውን መሠዊያ የሚቃ
ጠል መሥዋዕት፥ የእህል ቍርባን፥ ወይም ለደ
ኅንነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕት ልናቀርብ
በት አስበን ከሆነ ራሱ እግዚአብሔር ይቅጣን፤
24 እኛ የሠራነው ለዚህ አይደለም! እኛ እርሱን
የሠራነው በሚመጡት ዘመናት የእናንተ ዝርያ
ዎች የእኛን ልጆች 'እናንተ የእስራኤል አም
ላክ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግንኙነት
አላችሁ? 25 እርሱ በእኛና በእናንተ፥ በሮቤልና
በጋድ ሕዝቦች መካከል የዮርዳኖስን ወንዝ
መለያ ድንበር አድርጎአል፤ ስለዚህ ከእግዚአብ
ሔር ጋር ምንም ግንኙነት አይኖራችሁም' ይሉ
አቸው ይሆናል ብለን ስለፈራን ብቻ ነው።
በዚህም ዐይነት የእናንተ ዝርያዎች የእኛን ዝር
ያዎች ለእግዚአብሔር እንዳይሰግዱ ይከለክሉአ
ቸው ይሆናል። 26 ስለዚህ እኛ የሠራነው መሠ
ዊያ የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት ለማቅ
ረብ አይደለም። 27 እኛ እርሱን የሠራነው በእ
ኛና በእናንተ ሕዝብ መካከል ምልክት ሆኖ
እንዲኖር ነው፤ ይኸውም ከእኛ በኋላ ለሚነ
ሡት ትውልዶች በተቀደሰ ድንኳኑ ፊት እግዚ
አብሔርን እንደምናመልክ የሚቃጠልና ሌላም
መሥዋዕት፥ እንዲሁም ለደኅንነት የሚሆን የኅ
ብረት መሥዋዕት ስናቀርብ ለመኖራችን ምስ
ክር ይሆናል፤ ይኸውም የእናንተ ዝርያዎች
የእኛን ዝርያዎች 'ከእግዚአብሔር ጋር ምንም
ግንኙነት የላችሁም' እንዳይሉአችው ለማድረግ
ይጠቅማል፤ 28 እንግዲህ ምናልባት ይህ ነገር
ቢሆን የእኛ ዕቅድ፥ ዝርያዎቻችን 'ተመል
ከቱ! የቀድሞ አባቶቻችን የሠሩት መሠዊያ ለእ
ግዚአብሔር ከተሠራው መሠዊያ ጋር አንድ

22፥16 ፡- ዘዳ. 12፥13-14 ። 22፥17 ፡- ዘኁ. 25፥1-9 ። 22፥20 ፡- ኢያሱ 7፥1-26 ።

ዐይነት ነው ፤ ይኸውም በእኛና በእናንተ ሕዝ
ቦች መካከል ምልክት ሆኖ እንዲኖር እንጂ
የሚቃጠል ወይም ሌላ መሥዋዕት እንዲቀርብ
በት ታስቦ አልነበረም!’ ማለት እንዲችሉ
ነው ፤ 29 እኛ በእርግጥ በእግዚአብሔር ላይ አላ
መፅንም ፤ የሚቃጠል መሥዋዕት ወይም የእ
ህል መባ ፥ ወይም ሌላ መሥዋዕት ለማቅረብ
አስበን ሌላ መሠዊያ በመሥራት እግዚአብሔ
ርን ማምለክ አልተውንም ፤ እርሱ በሚመለክ
በት ድንኳን ፊት ለፊት ለቆመው ለአምላካችን
ለእግዚአብሔር ከተሠራው ሌላ የተለየ መሠዊያ
አልሠራንም ።”

30 ካህኑ ፊንሐስና ከእርሱ ጋር የነበሩት
ሕዝቡ የላካቸው የምዕራብ ነገዶች የቤተሰብ
አለቆች የሆኑት ታላላቅ ሰዎች ፥ የሮቤል ፥ የጋ
ድና በምሥራቅ በሚኖሩ የምናሴ ነገዶች
ሕዝብ የተናገሩትን ሰምተው መልሱ አረካ
ቸው ፤ 31 ስለዚህም የአልዓዛር ልጅ ካህኑ ፊን
ሐስ እንዲህ አላቸው ፥ “እነሆ አሁን እግዚአብ
ሔር ከእኛ ጋር መሆኑን ሀወቅን ፤ እናንተ በእ
ርሱ ላይ አላመፃችሁም ፤ ስለዚህም የእስራኤ
ልን ሕዝብ ከእግዚአብሔር ቅጣት አድ
ናችኋል ።”

32 ከዚህም በኋላ የካህኑ የአልዓዛር ልጅ ፊን
ሐስና መሪዎቹ የሮቤልና የጋድን ሕዝቦች በዚ
ያው በገለዓድ ምድር ትተው በከነዓን ምድር
ወደሚገኙት ወደ እስራኤል ሕዝብ ተመልሰው
በመምጣት ፥ ያገኙትን ማስረጃ አቀረቡ ፤ 33 እስ
ራኤላውያንም በመልሱ ረክተው እግዚአብሔ
ርን አመሰገኑ ፤ ከዚያም በኋላ የሮቤልና የጋድ
ሕዝብ የሚኖሩባትን ምድር ለመደምሰስ ጦር
ነት ስለማንሣት ጉዳይ መናገር አልፈለጉም ።

34 የሮቤልና የጋድ ሕዝብም “ይህ መሠዊያ
እግዚአብሔር ብቻ አምላክ ስለመሆኑ ለሁላችን
ምስክር ነው” አሉ ፤ ከዚህም የተነሣ “ምስ
ክር” ብለው ጠሩት ።

## ምዕራፍ 23

### ኢያሱ የተናገረው የመሰናበቻ ቃል

1 ከብዙ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር እስራኤላ
ውያንን በዙሪያቸው ከሚገኙ ጠላቶቻቸው በማ
ሳረፍ የሰላምን ኑሮ ሰጣቸው ፤ በዚያን ጊዜ
ኢያሱ በዕድሜው ሸምግሎ ነበር ፤ 2 ስለዚህም
እርሱ መላውን እስራኤልን ፥ ሽማግሌዎችን ፥
መሪዎችን ፥ ዳኞችንና የጦር አዛዦችን በአን
ድነት ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥ “እነሆ እኔ በዕ
ድሜ ሸምግያለሁ ፤ 3 አምላካችን እግዚአብሔር
እናንተን ለመርዳት በእነዚህ አሕዛብ ላይ ያደረ
ገውን ሁሉ አይታችኋል ፤ አምላካችሁ እግዚአ
ብሔር ስለ እናንተ ተዋግቶላችኋል ፤ 4 እኔም
ገና ድል ያልተመቱትና ድል የመታኋቸው
አሕዛብ ይዞታ የነበረውና በምሥራቅ በኩል
ከዮርዳኖስ ወንዝ በመዋሰን በስተምዕራብ እስከ
ሜድትራኒያን ባሕር የሚደርሰውን ሁሉ ለነገዶ
ቻችሁ ርስት አድርጌ ሰጥቼአለሁ ፤ 5 አምላካ
ችሁ እግዚአብሔር እነርሱን በፊታችሁ እንዲ
ሸሹ ያደርጋል ፤ እናንተም ወደ ፊት በተራመዳ
ችሁ መጠን እነርሱን ነቃቅሎ ያጠፋል ፤ አምላ
ካችሁ እግዚአብሔር በሰጣችሁም ተስፋ መሠ
ረት ምድራቸውን ትወርሳላችሁ ። 6 ስለዚህም
በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጻፉትን ትእዛዛት
ሁሉ ለመጠበቅ ብርቱ ጥንቃቄ አድርጉ ፤ ከእነ
ርሱም ፈቀቅ አትበሉ ። 7 ከዚህም በኋላ በመካከ
ላችሁ ከቀሩት አሕዛብ ጋር ከቶ አትተባበሩ ፤
የአማልክቶቻቸውንም ስም አትጥሩ በእነርሱም
አትማሉ ፤ ለእነርሱም አገልጋዮች አትሁኑ ፤
አትስገዱላቸውም ። 8 ይልቅስ እስከ አሁን እንዳ
ደረጋችሁት ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ታማ
ኞች ሁኑ ፤ 9 እናንተ ወደ ፊት በተራመዳችሁ
መጠን ታላላቅና ብርቱዎች የሆኑትን አሕዛብ
እግዚአብሔር ነቃቅሎ አባርሮላችኋል ፤ እናን
ተን እስከ ዛሬ ድረስ ሊቋቋማችሁ የቻለ አን
ድም የለም ፤ 10 ከእናንተ አንዱ ብቻውን ሆኖ
ከእነርሱ ወገን አንዱን ሺ ማባረር ይችላል ፤
ምክንያቱም አምላካችሁ እግዚአብሔር በሰጣ
ችሁ ተስፋ መሠረት ስለእናንተ እየተዋጋላችሁ
ነው ። 11 እንግዲህ አምላካችሁን እግዚአብሔ
ርን የምትወዱ መሆን እንደሚገባችሁ በጥንቃቄ
አስቡ ። 12 እናንተ የማትታመኑ ከሐዲዎች ብት
ሆኑ በመካከላችሁም ከቀሩት አሕዛብ ጋር ብት
ተባበሩና ከእነርሱ ጋር በጋብቻ ብትደባለቁ
ግን ፥ 13 እናንተ ወደ ፊት በተራመዳችሁ
መጠን እግዚአብሔር አምላካችሁ እነዚህን አሕ
ዛብ ከፊታችሁ ነቃቅሎ ሊያባርርላችሁ የማይፈ
ቅድ መሆኑን ዕወቁ ፤ ይልቁንም እነርሱ ለእና
ንተ እንደ አደገኛ ወጥመድና መውደቂያ
ጉድጓድ ይሆኑባችኋል ፤ ለጀርባችሁ እንደ መር
ዘኛ አለንጋ ፥ ለዐይናችሁ እንደሚወጋ እሾኽ
ይሆኑባችኋል ፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰ
ጣችሁ ፥ ከዚህች መልካም ምድር ተነቃቅላ
ችሁ እስክትጠፉ ድረስ ይህ ሁሉ ጥፋት ይደር
ስባችኋል ።

14 “እነሆ እኔ የምሞትበት ጊዜ ደርሶአል ፤
አምላካችሁ እግዚአብሔር በሰጣችሁ ተስፋ
መሠረት ያደረገላችሁን መልካም ነገር ሁሉ
ከእናንተ እያንዳንዱ በፍጹም ልቡና በፍጹም
ነፍሱ ያውቃል ፤ እርሱ ከሰጣችሁ ተስፋ አን
ድም ሳይቀር ሁሉም ተፈጽሞአል ። 15 ስለዚ
ህም እርሱ እያንዳንዱን ተስፋ እንደፈጸመላ
ችሁ ሁሉ እንዲሁም አስፈላጊ በሚሆንበት በእ
ናንተ ላይ የሚፈጽመውን ቅጣት ሊያመጣባ
ችሁ ይችላል ። 16 አምላካችሁ እግዚአብሔር

23፥10 ፦ ዘዳ. 3፡22 ፤ 32፥30 ።

እንድትጠብቁት ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን ብታፈር
ሱና ሌሎችን አማልክት በማገልገል ብታመልኩ
አቸው በዚያን ጊዜ እርሱ በቍጣው ይቀ
ጣችኋል፤ እርሱ በሰጣችሁም መልካም ምድር
ከእናንተ መካከል የሚኖርባት አንድ እንኳ አይ
ገኝም።”

## ምዕራፍ 24

### ኢያሱ በሴኬም ለሕዝቡ ያደረገው ንግግር

1 ኢያሱ የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ በሴ
ኬም በአንድነት ሰበሰበ፤ ሽማግሌዎችን፥ መሪ
ዎችን፥ ዳኞችንና የእስራኤልን የጦር አዛዥ
ዎች ሁሉ ጠራ፤ እነርሱም በእግዚአብሔር
ፊት ተሰበሰቡ፤ 2 ኢያሱም ለሕዝቡ ሁሉ እን
ዲህ ሲል ተናገረ፥ “የእስራኤል አምላክ የሆነ
እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፥ ‘ከብዙ ዘመ
ናት በፊት የቀድሞ አባቶቻችሁ ከኤፍራጥስ
ወንዝ ማዶ ባዕዳን አማልክትን በማምለክ ይኖሩ
ነበር፤ ከነዚያም አባቶች አንዱ የአብርሃምና
የናኮር አባት ታራ ነበር፤ 3 ከዚህም በኋላ የቀ
ድሞ አባታችሁን አብርሃምን ከኤፍራጥስ ወንዝ
ማዶ ከሚገኘው ምድር ጠርቼ፥ በከነዓን ምድር
ሁሉ መራሁት፤ ዘሩንም አበዛሁለት፤ ይስሐቅ
ንም ሰጠሁት፤ 4 ለይስሐቅም ያዕቆብንና ዔሳውን
ሰጠሁ፤ ለዔሳውም የኤዶምን ኮረብታማ አገር
ርስት አድርጌ ሰጠሁት፤ ነገር ግን የእናንተ የቀ
ድሞ አባት የሆነው ያዕቆብና ልጆቹ ወደ ግብጽ
ተሰደደው ወረዱ፤ 5 ዘግየት ብሎም ሙሴንና
አሮንን በመላክ በግብጽ ላይ ታላቅ መከራ እንዲ
ደርስባት አደረግሁ፤ እናንተን ግን መርቼ
አወጣኋችሁ፤ 6 የቀድሞ አባቶቻችሁን ከግብጽ
መርቼ ባወጣኋቸውም ጊዜ ግብጻውያን በሠረገላ
ዎችና በፈረሰኞች አሳደዱአቸው፤ ነገር ግን የቀ
ድሞ አባቶቻችሁ ወደ ቀይ ባሕር በቀረቡ ጊዜ፥
7 እረዳቸው ዘንድ ወደ እኔ ጮኹ፤ እኔም በእነር
ሱና በግብጻውያን መካከል ጨለማ እንዲሆን አደ
ረግሁ። ባሕሩም እንዲከነበልባቸው አድርጌ ግብ
ጻውያንን አሰጠምሁ፤ ስለዚህም በግብጽ ላይ
ያደረግሁባትን እናንተ ታውቁታላችሁ።

“‘እናንተም ለረዥም ጊዜ ያህል በበረሓ
ኖራችሁ፤ 8 ከዚህም በኋላ በዮርዳኖስ ምሥራቅ
አሞራውያን ወደሚኖሩባት ምድር አመጣኋ
ችሁ፤ እነርሱ ተዋጉአችሁ፤ እኔ ግን በእነርሱ
ላይ ድልን ስለሰጠኋችሁ፥ ምድራቸውን ወረሳ
ችሁ፤ ወደፊትም በተራመዳችሁ መጠን እነር
ሱን ደመሰስሁላችሁ፤ 9 ከዚህም በኋላ የሞአብ
ንጉሥ የነበረው የጺፖር ልጅ ባላቅ ሊወጋችሁ
በእናንተ ላይ ተነሣሣ፤ እናንተንም ይረግምለት
ዘንድ በለዓም ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ቢዖር
ልጅ መልእክት ላከ፤ 10 እኔ ግን በለዓምን አል
ሰማሁትም፤ ስለዚህም በመርገም ፈንታ ባረካ
ችሁ፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ ከባላቅ እጅ በመ
ታደግ አዳንኩአችሁ፤ 11 እናንተም የዮርዳኖስን
ወንዝ ተሻግራችሁ ወደ ኢያሪኮ መጣችሁ፤
የኢያሪኮም ሰዎች፥ እንዲሁም አሞራውያን፥
ፌሪዛውያን፥ ከነዓናውያን፥ ሒታውያን፥ ጌርጌ
ሳውያን፥ ሒዋውያንና ኢያቡሳውያን እናንተን
ለመውጋት ተነሡ፤ እኔ ግን በእነርሱ ሁሉ ላይ
ድልን ሰጠኋችሁ። 12 እናንተም ወደፊት በተራ
መዳችሁ መጠን ሁለቱን የአሞራውያን ነገሥ
ታት ነቃቅዬ ለማጥፋት እነርሱ በከባድ ጭንቅ
ላይ እንዲወድቁ አደረግሁ፤ ይህም ሁሉ ሊሆን
የቻለው በእናንተ ሰይፍና ቀስት አይደለም፤
13 እናንተ በማረስ ያልደከማችሁበትን የለማ
ምድርና ያልሠራችኋቸውንም ከተሞች መኖሪያ
አድርጌ ሰጠኋችሁ፤ እነሆ አሁን ያልተከላችሁ
ትን የወይን ተክልና ያልደከማችሁበትን የወ
ይራ ዛፍ ፍሬ እየተመገባችሁ ትኖራላችሁ።’”

14 ኢያሱ ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ፥
“እንግዲህ እግዚአብሔርን አክብሩት፤ በፍጹም
ቅንነትና በታማኝነት አገልግሉት፤ የቀድሞ አባ
ቶቻችሁ በመስጴጦምያና በግብጽ ይሰግዱላቸው
የነበሩትን ባዕዳን አማልክት አስወግዳችሁ እግ
ዚአብሔርን ብቻ አምልኩ፤ 15 እርሱን ማምለክ
መልካም መስሎ ካልታያችሁ ግን የቀድሞ አባ
ቶቻችሁ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ በነበሩበት
ጊዜ ያመልኩአቸው የነበሩትን ወይም አሁን
በምድራቸው የምትኖሩባቸውን የአሞራውያንን
አማልክት ታመልኩ እንደሆን የምታመልኩትን
ዛሬውኑ ምረጡ፤ እኔና ቤተሰቤ ግን እግዚአብ
ሔርን እናመልካለን።”

16 ሕዝቡም እንዲህ ሲሉ መለሱለት፥ “እግ
ዚአብሔርን ትተን ሌሎች ባዕዳን አማልክትን
ማምለክ ከእኛ ይራቅ፤ 17 አምላካችን እግዚአብ
ሔር አባቶቻችንንና እኛን ከግብጽ ባርነት አው
ጥቶናል፤ ያደረገውን ተአምራት ሁሉ አይተ
ናል፤ አሕዛብን ሁሉ አልፈን በመጣንበት ጊዜ
በሰላም ጠብቆናል፤ 18 እኛም ወደዚህች ምድር
ለመግባት ወደፊት በተራመድን መጠን በዚያ
የሚኖሩትን አሞራውያንን ሁሉ ከፊታችን ነቃ
ቅሎ አባርሮልናል፤ በስዚህም እርሱ አምላካ
ችን ስለሆነ እግዚአብሔርን እናገለግላለን።”

19 ኢያሱም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፥ “እግዚአ
ብሔር ቅዱስና ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ፥ እና
ንተ እርሱን ማገልገል አትችሉም፤ የምትሠሩ
ትን ዐመፅና ኃጢአት ሁሉ ይቅር አይልም፤

24፥2 ፦ ዘፍ. 11፥27። 24፥3 ፦ ዘፍ. 12፥1-9፤ 21፥1-3። 24፥4 ፦ ዘፍ. 25፥24-26፤ 36፥8፤ 46፥1-7፤ ዘዳ. 2፥5።
24፥5 ፦ ዘጸ. 3፥1–12፥42። 24፥6-7 ፦ ዘጸ. 14፥1-31። 24፥8 ፦ ዘኍ. 21፥21-35። 24፥9-10 ፦ ዘኍ. 22፥1–24፥25።
24፥11 ፦ ኢያሱ 3፥14-17፤ 6፥1-21። 24፥12 ፦ ዘጸ. 23፥28፤ ዘዳ. 7፥20። 24፥13 ፦ ዘዳ. 6፥10-11።

20 እርሱን ትታችሁ ባዕዳን አማልክትን ብታመ
ልኩ ፥ እርሱም ከእናንተ ፊቱን ይመልሳል ፤
በእናንተ ላይ በቍጣ ተነሣሥቶ ይቀጣችኋል ፤
ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ለእናንተ መልካም
ነገር ያደረገላችሁ ቢሆንም ፥ ተመልሶ ያጠ
ፋችኋል ።”
21 ሕዝቡም ለኢያሱ “ይህ ከቶ አይደረግም!
እኛ እግዚአብሔርን እናመልካለን” አሉት ።
22 ኢያሱም “እንግዲህ እግዚአብሔርን ለማ
ምለክ ስለመምረጣችሁ ራሳችሁ ለራሳችሁ ምስ
ክሮች ናችሁ” ሲል ነገራቸው ።
እነርሱም “አዎ! ምስክሮች ነን!” አሉ ።
23 እርሱም “እንግዲያውስ በመካከላችሁ
የሚገኙትን ባዕዳን አማልክት አስወግዱ ፤ የእስ
ራኤል አምላክ ለሆነው ለእግዚአብሔርም ታማ
ኝነታችሁን ግለጡ” አላቸው ።
24 ከዚህም በኋላ ሕዝቡ ኢያሱን “እኛ አም
ላካችንን እግዚአብሔርን እናመልካለን ፥ ትእዛዛ
ቱንም እንፈጽማለን” አሉት ።
25 በዚያም ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል
ኪዳን ገባ ፤ በዚያም በሴኬም የሚመሩበትን
ሕግና ደንብ ሰጣቸው ፤ 26 ኢያሱም እነዚህን
ትእዛዛት በእግዚአብሔር የሕግ መጽሐፍ ጻፈ ፤
ከዚያም በኋላ አንድ ትልቅ ድንጋይ ወስዶ በእ
ግዚአብሔር መቅደስ አጠገብ በሚገኘው የወ
ርካ ዛፍ ሥር አቆመው ፤ 27 ለሕዝቡም ሁሉ
እንዲህ አለ ፥ “እንግዲህ ይህ ድንጋይ ምስክራ
ችን ይሆናል ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኛ
የተናገረውን ቃል ሁሉ ሰምቶአል ፤ ስለዚህ እና
ንተ በአምላካችሁ ላይ ከማመፅ እንድትገቱ ፥
በእናንተ ላይ ምስክር ይሆንባችኋል ።” 28 ከዚህ
በኋላ ኢያሱ ሕዝቡን ሁሉ አሰናበተ ፤ እያንዳን
ዱም ወደየርስት ይዞታው ተመልሶ ሄደ ።

### የኢያሱና የአልዓዛር መሞት

29 ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር አገልጋይ
የነዌ ልጅ ኢያሱ በአንድ መቶ ዐሥር ዓመት
ዕድሜው ሞተ ። 30 ሕዝቡም ከጋዓሽ ተራራ
በስተሰሜን በኩል በምትገኘው በኮረብታማይቱ
በኤፍሬም አገር የራሱ የኢያሱ ርስት በሆነችው
በቲምናትሴራሕ ቀበሩት ።
31 ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሁሉ የእ
ስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን አመለኩ ፤ ከእር
ሱም ሞት በኋላ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደ
ረገውን ድንቅ ነገር ሁሉ በዐይናቸው ያዩት
መሪዎች እስካሉበት ድረስ እርሱኑ በማምለክ
ኖሩ ።
32 የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ምድር ያመ
ጡት የዮሴፍ ዐፅም በሴኬም ተቀበረ ፤ ይህም
ምድር ያዕቆብ የሼኬም አባት ከሆነው ከሐሞር
ልጆች በአንድ መቶ ጥሬ ብር የገዛው ነበር ፤
ምድሩም የሚገኘው በዮሴፍ ዘሮች የርስት
ድርሻ ክልል ውስጥ ነው ።
33 የአሮን ልጅ አልዓዛርም ሞተ ፤ በጊብዓም
ተቀበረ ፤ እርስዋም በኮረብታማው በኤፍሬም
አገር የምትገኝና ለልጁ ለፊንሐስ መኖሪያ የተሰ
ጠች ትንሽ ከተማ ናት ።

# መጽሐፈ መሳፍንት

## መግቢያ

መጽሐፈ መሳፍንት ከነዓን ከተያዘችበት ጊዜ አንሥቶ ንጉሣዊው መንግሥት እስከ ተመሠረተበት ጊዜ ድረስ ፥ በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ሕግ ወጥ ከነበረው ዘመን የተገኙትን ታሪኮች የያዘ ነው ። እነዚህም ታሪኮች የሚያመለክቱት “መሳፍንት” የተባሉት ጀግኖች የፈጸሙአቸውን ተግባሮች ነው ፤ ከእነዚህም መሳፍንት መካከል አብዛኞዎቹ የጦር መሪዎች ነበሩ ፤ ከእነርሱም በጣም የታወቀው የጀግንነት ሥራው ከምዕራፍ 13-16 ተዘርዝሮ የሚገኘው ሳምሶን የተባለው ሰው ነው ። ከመጽሐፉ የምናገኘው ታላቅ ትምህርት የእስራኤል ሕዝብ ህልውና የሚረጋገጠው ለእግዚአብሔር ባላቸው ታማኝነት ሲሆን ፥ ለእርሱ ታማኞች ሳይሆኑ ሲቀሩ ዘወትር ጥፋት ይደርስባቸው እንደነበር የሚያስገነዝበው ነው ፤ ከዚህም የበለጠ ሌላ ነገር አለ ፤ ይኸውም ምንም እንኳ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት በማጓደላቸው ምክንያት ጥፋት ቢደርስባቸውም ፥ ንስሓ ገብተው ወደ እርሱ በተመለሱ ቍጥር እግዚአብሔር ሊያድናቸው ዝግጁ መሆኑን የሚያመለክተው ነው ።

---

24፡30 ፡- ኢያሱ 19፡49-50 ። 24፡32 ፡- ዘፍ. 33፡19 ፤ 50፡24-25 ፤ ዘጸ. 13፡19 ፤ ዮሐ. 4፡5 ፤ ሐ.ሥ. 7፡16 ።

## ምዕራፍ 1

### የይሁዳና የስምዖን ነገዶች አዶኒቤዜቅን ማረኩ

1 ኢያሱ ከሞተ በኋላ የእስራኤል ሕዝብ
“በከነዓናውያን ላይ አደጋ ለመጣል ከነገዶቻ
ችን መካከል ተቀዳሚ ሆኖ ማን ይዝመት?”
ሲሉ እግዚአብሔርን ጠየቁ።
2 እግዚአብሔርም “የይሁዳ ነገድ ተቀዳሚ
ሆኖ ይዝመት፤ እኔ ምድሪቱን ለእነርሱ አሳ
ልፌ እሰጣለሁ” አለ።
3 የይሁዳ ሕዝብ የስምዖንን ሕዝብ “ለእኛ
ወደተመደበልን ግዛት አብራችሁን ሂዱ፤ አብረ
ንም በከነዓናውያን ላይ አደጋ እንጣል፤ ከዚ
ያም በኋላ ለእናንተ ወደተመደበላችሁ ግዛት
አብረናችሁ እንሄዳለን” አሉአቸው። ስለዚህም
የስምዖንና፥ 4 የይሁዳ ሕዝብ በአንድነት ሆነው
ዘመቱ፤ እግዚአብሔርም በከነዓናውያንና በፌሪ
ዛውያን ላይ ድልን ሰጣቸው፤ እነርሱም በቤ
ዜቅ ዐሥር ሺ ሠራዊት አሸነፉ። 5 በዚያም
አዶኒቤዜቅን አግኝተው ከእርሱ ጋር ጦርነት
ገጠሙ፤ 6 እርሱም ከፊታቸው ሸሸ፤ እነርሱ
ግን አባርረው ከያዙት በኋላ የእጆቹንና የእግሮ
ቹን አውራ ጣቶች ቈረጡ፤ 7 አዶኒቤዜቅም
“የእጆቻቸውና የእግሮቻቸው አውራ ጣቶች
የተቈረጡባቸው ሰባ ነገሥታት ከገበታዬ ሥር
ፍርፋሪ እየለቀሙ ይበሉ ነበር፤ በእነርሱ ላይ
የፈጸምኩትን ግፍ ዛሬ እግዚአብሔር በእኔ ላይ
መልሶ አመጣብኝ” ሲል ተናገረ። ወደ ኢየሩሳ
ሌምም ተወስዶ በዚያው ሞተ።

### የይሁዳ ነገድ ኢየሩሳሌምንና ኬብሮንን ያዘ

8 የይሁዳ ሰዎች በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ
ጥለው ያዙአት፤ ሕዝብዋንም ገድለው ከተማይ
ቱን በእሳት አቃጠሉ። 9 ከዚህ በኋላ በደቡብ
በኩል ደረቅ በሆነው ምድር፥ በኮረብታዎች
ግርጌና ኮረብታማ በሆነችው አገር የሚኖሩትን
ከነዓናውያንን ለመውጋት ዘመቱ፤ 10 የቀድሞ
ስሟ “ቂርያትአርባዕ” ተብሎ በሚጠራው በኬ
ብሮን ከተማ የሚኖሩትን ከነዓናውያን ዘምተው
አደጋ ጣሉባቸው፤ በዚያም የሼሻይን፥ የአሒ
ማንንና የታልማይን ጐሳዎች አሸነፉ።

### ዖትኒኤል የደቢርን ከተማ ያዘ
(ኢያሱ 15፥13-19)

11 ከዚያም የይሁዳ ሰዎች ወደ ደቢር ከተማ
ዘመቱ፤ በዚያን ጊዜ ከተማይቱ “ቂርያትሴ
ፌር” ተብላ ትጠራ ነበር። 12 ከእነርሱም
ታዋቂ የሆነው ካሌብ “ቀድሞ ቂርያትሴፌርን
ለሚይዝ ሰው ሴት ልጄን ዓክሳን እድርለታ
ለሁ” አለ። 13 የካሌብ ታናሽ ወንድም የቀናዝ
ልጅ ዖትኒኤል ከተማይቱን ቀድሞ ያዘ፤ ስለዚ
ህም ካሌብ ሴት ልጁን ዓክሳን ዳረለት። 14 ቤጋ
ብቻቸውም ቀን ዖትኒኤል ዓክሳን “አባትሽ የእ
ርሻ መሬት እንዲሰጥሽ ጠይቂ”1* አላት፤ እርስ
ዋም ካሌብን ስታይ ከበቅሎዋ ላይ ወረደች፤
ካሌብም “ምን እንድሰጥሽ ትፈልጊአለሽ”
ብሎ ጠየቃት። 15 እርስዋም “ጥቂት የውሃ
ምንጮች እንዲኖሩኝ እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም
የሰጠኸኝ መሬት የሚገኘው በደረቅ ምድር
ነው” አለችው፤ ስለዚህ ካሌብ የላይኛውንና
የታችኛውን ምንጮች ሰጣት።

### የይሁዳና የብንያም ነገዶች የተቀዳጁት ድል

16 የሙሴ ዐማት የነበረው የቄናዊው ዝርያ
ዎች ከይሁዳ ሕዝብ ጋር በመሆን የተምር
ዛፎች ከሞሉባት ከኢያሪኮ ከተማ ተነሥተው፥
በይሁዳ ካለችው ከዐራድ በስተደቡብ ወዳለው
ደረቅ ምድር ተጓዙ፤ እዚያም በሀማሌቃውያን
መካከል2* ተቀመጡ። 17 የይሁዳ ሕዝብ ከስም
ዖን ሕዝብ ጋር በአንድነት ዘምተው በጸፋት
ከተማ ይኖሩ የነበሩትን ከነዓናውያን ድል አደ
ረጉ፤ ከተማይቱንም ፈጽመው ካጠፉአት በኋላ
“ሖርማ”3* ብለው ሰየሙአት፤ 18-19 እግዚአብ
ሔር የይሁዳን ሕዝብ ስለረዳ ኮረብታማዋን
አገር ወረሱ፤ እንዲሁም ጋዛን፥ አስቀሎናን
ወይም ዔቅሮንን በዙሪያቸው ካሉት ግዛቶች
ጋር ያዙ፤ እነዚህ በባሕር ዳርቻ የሚኖሩ
ሕዝብ ከብረት የተሠሩ ሠረገሎች ስለነበሩአ
ቸው የይሁዳ ሕዝብ እነርሱን ማባረር ተሣና
ቸው፤ 20 ሙሴ ባዘዘው መሠረት ኬብሮን የዐ
ናቅ ዝርያዎች የሆኑትን ሦስት ጐሳዎች ከከተ
ማይቱ ሳስወጣው ለካሌብ ተሰጠ። 21 የብንያም
ነገድ ሕዝብ ግን በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን
ኢያቡሳውያንን አላስወጡም ነበር፤ ከዚያን
ጊዜም ጀምሮ ኢያቡሳውያን ከብንያም ሕዝብ
ጋር አብረው መኖርን ቀጠሉ።

### የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች ቤትኤልን ያዙ

22-23 የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች በዚያን
ጊዜ “ሎዛ” ተብላ ትጠራ በነበረችው በቤት
ኤል ከተማ ላይ አደጋ ለመጣል አብረው
ዘመቱ፤ እግዚአብሔርም ረዳቸው፤ እነርሱም
ወደ ከተማይቱ ሰላዮችን ላኩ፤ 24 ሰላዮቹም
ከከተማይቱ የሚወጣ አንድ ሰው አግኝተው
“ወደ ከተማይቱ እንዴት መግባት እንደሚቻል

---

1* 1፥14 ጠይቂ አላት ፦ በዕብራይስጥ “ጠይቅ አለችው” ይላል (ኢ.ያ. 15፥18 ተመልከት)። 2* 1፥16 በዐማሌቃውያን መካከል ወይም “በሕዝቡ መካከል።” 3* 1፥17 ሖርማ ፦ በዕብራይስጥ “እርም አደረገው” ማለት ነው።

1፥21 ፦ ኢያሱ 15፥63፤ 2ሳሙ. 5፥6፤ 1ዜ.መ. 11፥4።

አባቶቻቸው አምላክ የሆነውንና ከግብጽ ያወጣ
ቸውን እግዚአብሔርን ማገልገል ተዉ፤ በዚ
ህም ፈንታ በዙሪያቸው ያሉ ሕዝብ የሚያመል
ኩአቸውን ሐሰተኞች አማልክት ማገልገል
ጀመሩ፤ ለእነርሱም በመስገድ እግዚአብሔርን
አስቈጡት። [13]እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው
“ባዓልና ዐስታሮት” ተብለው ለሚጠሩት ባዕ
ዳን አማልክት ሰገዱ፤ [14]ከዚህም የተነሣ እግዚ
አብሔር በእስራኤል ላይ በብርቱ ተቈጣ፤ ወን
በዴዎችም በእነርሱ ላይ አደጋ እየጣሉ እንዲዘ
ርፉአቸው ፈቀደ፤ በዙሪያቸው ያሉ ጠላቶቻቸ
ውም እንዲበረቱባቸው አደረገ። ከዚያም በኋላ
እስራኤላውያን ራሳቸውን መከላከል ተሣና
ቸው። [15]ወደ ጦርነት በሄዱም ቍጥር ቀደም
ብሎ በመሐላ በተናገረው መሠረት እግዚአብ
ሔር ራሱ ይቃወማቸው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ
እነርሱ በብርቱ ጭንቅ ላይ ወደቁ።
[16]ከዚህ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር ከወራሪ
ዎች የሚያድኑአቸውን መሪዎች ለእስራኤላው
ያን ሰጠ። [17]ነገር ግን እስራኤላውያን ለመሪዎ
ቻቸው የማይታዘዙ ሆኑ፤ እስራኤል ለእግዚአብ
ሔር ያለውን ታማኝነት አጓድሎ የሌሎች ባዕ
ዳን አማልክት አገልጋይ ሆነ፤ አባቶቻቸው የእ
ግዚአብሔርን ትእዛዛት ያከብሩ ነበር፤ ይህ
አዲስ ትውልድ ግን ይህን ማድረግ በፍጥነት
ተወ። [18]እግዚአብሔር ለእስራኤል አንድ መሪ
ባስነሣላቸው ቍጥር፥ ያ መሪ እግዚአብሔር
ስለሚረዳው በሕይወት እስካለበት ጊዜ ድረስ
ሕዝቡን ከጠላቶቻቸው እጅ በመታደግ ያድና
ቸው ነበር፤ ከሥቃይና ከጭቈና ብዛት ሕዝቡ
በሚጮኹበት ጊዜ እግዚአብሔር ምሕረት ያደ
ርግላቸው ነበር። [19]ነገር ግን መሪው በሚሞት
በት ጊዜ ሕዝቡ ወደ ጥንት መንገዳቸው ተመ
ልሰው፥ ከዚያ በፊት ከነበረው ትውልድ የባሰ
ክፉ ጠባይ ያሳያሉ፤ ለሌሎች ባዕዳን አማልክት
በመስገድ እያገለገሉ ክፉ መንገዳቸውንም
መተው አልፈለጉም፤ [20]በዚያን ጊዜ እግዚአብ
ሔር በእስራኤል ላይ ተቈጥቶ እንዲህ አለ፥
“ይህ ትውልድ አባቶቹ እንዲጠብቁት ያዘዝሁአ
ቸውን ቃል ኪዳን አፍርሶአል፤ እነርሱ ለእኔ
ስላልታዘዙ፥ [21]ኢያሱ በሞተ ጊዜ በምድሪቱ
ላይ ከነበሩት አሕዛብ አንዳቸውን እንኳ አላስወ
ጣም። [22]እንዲያውም እነዚህ እስራኤላውያን
እንደ ቀድሞ አባቶቻቸው መንገዴን ይከተሉ
ወይም አይከተሉ እንደሆን የማውቀው በእነዚህ
አሕዛብ መሣሪያነት በመፈተን ነው።” [23]ስለ
ዚህ እግዚአብሔር እነዚያም አሕዛብ በምድሪቱ
ላይ እንዲቆዩ አደረገ፤ እነርሱን እስከመጨረ
ሻው ያጠፋቸው ዘንድ ለኢያሱ እንኳ አልፈቀደ
ለትም፤ ኢያሱም ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር
ወዲያውኑ እንዲባረሩ አላደረገም።

## ምዕራፍ 3
### ሳይባረሩ በምድሪቱ ላይ የቀሩ አረማውያን ሕዝቦች

[1]በዚህ ዐይነት እግዚአብሔር በከነዓን ገና
የጦር ልምምድ የሌላቸውን እስራኤላውያን
ይፈትኑ ዘንድ አንዳንድ አረማውያን ሕዝብ
በምድሪቱ ላይ ተወ። [2]ይህንንም ማድረጉ እያን
ዳንዱን የእስራኤላውያን ትውልድ በተለይም
ከዚህ በፊት ወደ ጦርነት ሄደው የማያውቁትን
በእነርሱ አማካይነት የጦርነት ስልት እንዲማሩ
ነው። [3]በምድሪቱ ላይ የቀሩትም አምስቱ የፍ
ልስጥኤማውያን ከተሞች፥ ከነዓናውያን
በሙሉ፥ ሲዶናውያንና ከባዓልሔርሞን ተራራ
እንሥቶ እስከ ሐማት መተላለፊያ በሊባኖስ
ተራራዎች የሚኖሩት ሒዋውያን ነበሩ። [4]እነ
ርሱም እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለቀ
ድሞ አባቶቻቸው የሰጣቸውን ትእዛዛት እስራኤ
ላውያን ያከብሩ ወይም አያከብሩ እንደሆነ ለማ
ወቅ ለእስራኤል መፈተኛዎች ነበሩ። [5]በዚህም
ዐይነት የእስራኤል ሕዝብ ከከነዓናውያን፥ ከሒ
ታውያን፥ ከአሞራውያን፥ ከፈሪዛውያን፥ ከሒ
ዋውያንና ከኢያቡሳውያን ጋር አብረው ነዋሪ
ዎች ሆኑ። [6]ከእነርሱም ጋር ተጋብተው ለባዕ
ዳን አማልክቶቻቸው ሰገዱ።

### ዖትኒኤል

[7]የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት
በደል ሠሩ፤ እርሱንም ረስተው ባዓልና አሼራ
ለተባሉት ባዕዳን አማልክት ሰገዱ፤ [8]ከዚህም
የተነሣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ተቈጥቶ
ንጉሥ ኩሻን ሪሽዓታይም ድል ነሥቶ እንዲይዛ
ቸው ፈቀደ፤ ለስምንት ዓመትም ገዛቸው፤
[9]ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ፤ እርሱም በመታደግ ነፃ የሚያወጣቸ
ውን ሰው ላከላቸው፤ ይህም ሰው የካሌብ
ታናሽ ወንድም የሆነው የቀናዝ ልጅ ዖትኒኤል
ነበር። [10]የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ
ስላደረ የእስራኤል መሪ ሆነ፤ ዖትኒኤል በን
ጉሥ ኩሻን ላይ ዘምቶ በእግዚአብሔር ዕርዳታ
ድል አደረገው። [11]በምድሪቱም ላይ ለአርባ
ዓመት ያህል ሰላም ሰፍኖ ከቆየ በኋላ ዖትኒኤል
ሞተ።

### ኤሁድ[5*]

[12]የእስራኤል ሕዝብ እንደገና በእግዚአብ
ሔር ፊት በደል ሠሩ፤ በዚህም ምክንያት እግ
ዚአብሔር የሞአብን ንጉሥ ዔግሎንን ከእስራ
ኤል ይበልጥ የበረታ እንዲሆን አደረገው።
[13]ዔግሎንም ከዐሞናውያንና ከዐማሌቃውያን
ጋር ተባበረ፤ እስራኤላውያንም ድል ነሥተው

[5*] 3፥12 ኤሁድ ፦ በ1954 ዓ.ም. በታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ “ናዖድ” ይላል።

[9] እርስዋም “እሺ ፥ እኔም ከአንተ ጋር እሄዳ
ለሁ ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሲሣራን ስሴት
አሳልፎ ስለሚሰዋ ድሉ ለአንተ ክብር አይሆ
ንም” አለችው ፤ ስለዚህ ዲቦራ ከባራቅ ጋር
ወደ ቄዴሽ ዘመተች ። [10] ባራቅም የንፍታሌም
ንና የዛብሎንን ነገዶች ወደ ቄዴሽ አስጠራ ፤
ከእነርሱም ዐሥር ሺ ሰዎች ተከተሉት ፤ ዲቦ
ራም አብራው ዘመተች ።
[11] በዚያኑ ጊዜ ቄናዊው ሔቤር ወደ ቄዴሽ
ቀረብ ብሎ በጻዕናይም በሚገኘው በወርካ ዛፍ
አጠገብ ድንኳኑን ተከለ ፤ የሙሴ ሚስት ወን
ድም የሖባብ ዝርያ ከሆኑት ከሌሎቹ ቄናውያ
ንም ተለየ ።
[12] ባራቅ ወደ ታቦር ተራራ መሄዱን ሲሣራ
በሰማ ጊዜ ፥ [13] ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎች
ንና ወታደሮቹን ሁሉ አስጠርቶ የአረማውያን
ይዞታ ከሆነችው ከሐሮሼት ወደ ቂሾን ወንዝ
እንዲዘምቱ አዘዘ ።
[14] በዚያን ጊዜ ዲቦራ ባራቅን “ሂድ! እግዚ
አብሔር ይመራሃል ፤ ዛሬ በሲሣራ ላይ ድልን
ያጐናጽፍሃል” አለችው ። ስለዚህም ባራቅ
ዐሥር ሺ ወታደሮቹን አስከትሎ ከታቦር ተራራ
ወረደ ። [15] ባራቅ ከሠራዊቱ ጋር አደጋ በጣለ
ጊዜ እግዚአብሔር ሲሣራን ከሠረገላዎቹና ከሠ
ራዊቱ ሁሉ ጋር በአደናጋሪ ሁከት ላይ እንዲወ
ድቅ አደረገው ፤ ሲሣራም ከሠረገላው ወርዶ
በእግሩ ሸሸ ። [16] ባራቅም ሠረገላዎቹንና ሠራዊ
ቱን የአረማውያን ይዞታ እስከ ሆነችው እስከ
ሐሮሼት ድረስ አሳደዳቸው ፤ የሲሣራም ሠራ
ዊት በሙሉ ተገደለ ፤ አንድ ሰው እንኳ አልተ
ረፈም ።
[17] የሐጾር ንጉሥ ያቢን ከሔቤር ቤተሰብ
ጋር ሰላም መሥርቶ ይኖር ስለነበር ሲሣራ
ሸሽቶ የቄናዊው የሔቤር ሚስት ወደሆነችው
ወደ ያዔል ድንኳን ገባ ። [18] ያዔልም ሲሣራን
ልትቀበለው ወጥታ “ጌታዬ ና ፥ ወደ ድንኳኔ
ግባ ፤ ከቶ አትፍራ” አለችው ፤ እርሱም ወደ
ውስጥ በገባ ጊዜ ከመጋረጃ በስተኋላ ደበቀ
ችው ፤ [19] ሲሣራም “እባክሽ የምጠጣው ውሃ
ስጪኝ ፤ በጣም ጠምቶኛል” አላት ፤ እርስዋም
ከቆዳ የተሠራውን የወተት ዕቃ ከፍታ አጠጣች
ውና እንደገና ደበቀችው ። [20] ከዚህ በኋላ እርሱ
“በድንኳኑ በር ላይ ቁሚ ፤ አንድ ሰው መጥቶ
ከዚህ ሌላ ሰው እንዳለ ቢጠይቅሽ ማንም የለም
በይው” አላት ።
[21] ሲሣራ በጣም ደክሞት ስለነበር ከባድ እን
ቅልፍ ወሰደው ፤ ከዚህ በኋላ ያዔል መዶሻና
የድንኳን ካስማ ወስዳ በቀስታ ወደ እርሱ ቀረ
በች ፤ ካስማውንም በጆሮ ግንዱ ላይ በመዶሻ
መትታ ራሱን ከመሬት ጋር አጣበቀችው ።
[22] ባራቅ ሲሣራን እየፈለገ ሲመጣ ያዔል ልትቀ
በለው ወጥታ “ወደዚህ ና ፥ አንተ የምትፈልገ
ውን ሰው አሳይሃለሁ” አለችው ። ስለዚህም ከእ
ርስዋ ጋር ወደ ውስጥ በገባ ጊዜ የድንኳኑ
ካስማ በጆሮግንዱ ላይ እንደተቸነከረ ሬሳውን
በመሬት ላይ ተጋድሞ አየ ።
[23] እግዚአብሔርም በዚያን ቀን እስራኤላው
ያን በከነዓናዊው ንጉሥ በያቢን ላይ ድልን እን
ዲቀዳጁ አደረገ ። [24] እነርሱም እርሱን ፈጽ
መው እስከሚያጠፉት ድረስ በእርሱ ላይ በኀ
ይል እየበረቱ ሄዱ ።

## ምዕራፍ 5

### የዲቦራና የባራቅ መዝሙር

[1] በዚያን ቀን ዲቦራና የአቢኖዓም ልጅ
ባራቅ ይህን መዝሙር ዘመሩ ፦

[2] እግዚአብሔር ይመስገን!
እስራኤላውያን ለመዋጋት ቊርጥ
ውሳኔ አደረጉ ፤
ሕዝቡም ደስ ብሎአቸው በበጎ ፈቃድ
ተነሣሡ ።
[3] እናንተ ነገሥታት አድምጡ ፤
እናንተም ገዢዎች አስተውሉ ፤
የእስራኤል አምላክ ለሆነው
ለእግዚአብሔር ፥
በሙዚቃ መሣሪያ እዘምራለሁ ፤
[4] እግዚአብሔር ሆይ!
ከሴዒር ተራራ በተነሣህ ጊዜ ፥
ከኤዶምም ግዛት በወጣህ ጊዜ ፥
ምድር ተንቀጠቀጠች ፤
ከሰማይም ዝናም ዘነመ ፤
አዎ! ውሃ ከደመናዎች ወደታች
ጐረፈ ።
[5] በሲና አምላክ ፊት ተራራዎች ተናወጡ ፤
የእስራኤል አምላክ በሆነውም ፥
በእግዚአብሔር ፊት ተንቀጠቀጡ ።

[6] በዐናት ልጅ በሻምጋርና በያዔል ዘመን ፥
የጭነት አጋሰስ የሚነዱ ነጋዴዎች
በምድሪቱ አያልፉም ነበር ፤
መንገደኞችም ተደብቀው በዘወርዋራ
መንገድ ይሄዱ ነበር ፤
[7] ዲቦራ ሆይ! የእስራኤል ከተሞች ሰው
አልባ ሆነው ነበር ፤
አንቺም ለእስራኤል እናት ሆነሽ
እስክትነሺ ድረስ ፥ ወና ሆነው
ቀርተው ነበር ።
[8] እስራኤላውያን ቀድሞ የማያውቁአቸውን
ባዕዳን አማልክትን በመረጡ ጊዜ ፥
በምድሪቱ ላይ ጦርነት ሆነ ፤
ከአርባ ሺ እስራኤላውያን

5፥5 ፦ ዘጸ. 19፥18 ።

እግዚአብሔርም “አንተ እስከትመለስ ድረስ
እጠብቅሃለሁ” አለው ።
19 ጌዴዎንም ወደ ቤት ገባና የፍየል ጥቦት
ሀርዶ አዘጋጀ ፤ ዐሥር ኪሎ የሚያህልም ዱቄት
ወስዶ እርሾ ያልገባበት እንጀራ ጋገረ ፤ ሥጋ
ውን በመሶብ ፥ መረቁን በምንቸት አድርጎ በወ
ርካው ሥር ለተቀመጠው ለእግዚአብሔር መል
አክ ወስዶ አቀረበለት ። 20 መልአኩም “ሥጋው
ንና እንጀራውን በዚህ አለት ላይ አስቀምጠህ
መረቁን በላዩ አፍስስበት” ሲል አዘዘው ፤ ጌዴ
ዎንም እንደታዘዘው አደረገ ። 21 የእግዚአብሔር
መልአክ ቀረብ ብሎ በያዘው በትር ጫፍ ሥጋ
ውንና እንጀራውን ነካ ፤ እሳትም ከአለቱ ላይ
ተነሥቶ ሥጋውንና እንጀራውን በላ ፤ ከዚያም
በኋላ መልአኩ ተሰወረ ።
22 ጌዴዎን ያየው የእግዚአብሔር መልአክ
መሆኑን በተገነዘበ ጊዜ በፍርሃት እየተንቀጠ
ቀጠ “ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! የአንተን
መልአክ ፊት ለፊት አየሁ” አለ ።
23 እግዚአብሔር ግን “ሰላም ለአንተ
ይሁን ፤ አይዞህ አትፍራ ፤ አትሞትም” አለው ።
24 ጌዴዎንም በዚያ መሠዊያ ሠርቶ “እግዚአብ
ሔር የሰላም አምላክ ነው” ብሎ ሰየመው ፤
(ይህም መሠዊያ እስከ ዛሬ የአቢዔዜር ጐሳ
ይዞታ በሆነችው በዖፍራ ቆሞ ይገኛል ።)
25 በዚያን ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎንን
እንዲህ አለው ፥ “የአባትህን ኮርማና ሰባት
ዓመት የሞላው አንድ ሌላ ኮርማ ውሰድ ፤ አባ
ትህ ለባዓል የሠራውን መሠዊያ አፍርስ ፤ በአጠ
ገቡ ያለውንም ‘አሼራ’ ተብላ የምትጠራውን
የሴት አምላክ ምስል ሰባብረህ ጣል ፤ 26 በዚ
ያም የፍርስራሽ ጉብታ አናት ላይ ለአምላክህ
ለእግዚአብሔር በደንብ የተስተካከለ መሠዊያ
ሥራ ፤ ከዚያን በኋላ ሁለተኛውን ኮርማ
ውሰድ ፤ ሰባብረህ የጣልከውንም የአሼራን
ምስል ሰብርባሪ በማንደድ ኮርማውን በሙሉ
የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገህ አቅርብ ።”
27 ጌዴዎንም ከአገልጋዮቹ ዐሥሩን ወስዶ እግ
ዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ፤ ቤተሰቡንንና
የከተማይቱን ነዋሪዎች ከመፍራቱም የተነሣ
ይህን ያደረገው ቀን ሳይሆን በሌሊት ጨለማ
ለብሶ ነበር ።
28 በማግሥቱ የከተማይቱ ነዋሪዎች ማል
ደው በተነሡ ጊዜ ለባዓል የተሠራው መሠዊያ
መፍረሱንና የአሼራም ምስል ተሰባብሮ መውደ
ቁን አዩ ፤ ከዚያም በተሠራው መሠዊያ ላይ
ሁለተኛው ኮርማ ታርዶ የሚቃጠል መሥዋዕት
ሆኖ መቅረቡን ተመለከቱ ። 29 እርስ በርሳቸ
ውም “ይህን ያደረገ ማን ነው?” በማለት ተጠ
ያየቁ ፤ ብዙ ከተመራመሩም በኋላ ይህን ያደረ
ገው የዮአሽ ልጅ ጌዴዎን መሆኑን ደረሱበት ፤
30 ከዚህም በኋላ ዮአሽን “የባዓልን መሠዊያ
ስላፈረሰና በአጠገቡ ያለውንም የአሼራን ምስል
ሰባብሮ ስለጣለ ፥ እንገድለው ዘንድ ልጅህን
ወዲህ አውጣልን” አሉት ።
31 ዮአሽ ግን በቍጣ ተነሣሥተው ወደ
እርሱ የመጡትን ሰዎች እንዲህ አላቸው ፥
“ታዲያ እናንተ የምትከራከሩት ስባዓል ነውን?
ለእርሱስ ጥብቅና ትቆሙለታላችሁን? ከእናንተ
መካከል ለእርሱ የሚከራከር ቢኖር እስከነገ
ጠዋት ድረስ እርሱ ይሞታል ፤ እንግዲህ ባዓል
አምላክ ከሆነ ፥ ለራሱ ይከላከል ፤ ይህ የፈረሰው
እኮ የእርሱ መሠዊያ ነው ።” 32 ከዚህ በኋላ
ዮአሽ “ፈራርሶ የወደቀው የእርሱ መሠዊያ ስለ
ሆነ እስቲ ይችል እንደሆነ ባዓል ራሱን ይከላ
ከል!” ለማለት ፈልጎ ፥ ለጌዴዎን ይሩባዓል
የሚል ስም አወጣለት ።
33 ከዚያም በኋላ ምድያማውያን ፥ ዐማሌቃ
ውያንና በስተምሥራቅ በበረሓ የሚኖሩ ነገዶች
በአንድነት ተሰብስበው የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻ
ገሩ ፤ በኢይዝራኤል ሸለቆም ሰፈሩ ። 34 የእግዚ
አብሔር መንፈስ በጌዴዎን ላይ ወረደ ፤ የአቢዔ
ዜር ጐሳ ሰዎች ሁሉ እንዲከተሉት እነርሱን
ለመጥራት መለከት ነፋ ፤ 35 በሁለቱም የምናሴ
ነገድ ይዞታ በሆኑት ግዛቶች ወደሚኖሩት
ሕዝብ ሁሉ መልእክት ልኮ ይከተሉት ዘንድ
አስጠራቸው ፤ እንዲሁም ወደአሴር ፥ ወደዛብሎ
ንና ወደንፍታሌም ነገዶች መልእክተኞች ላከ ፤
እነርሱም ከእርሱ ጋር ለመሰለፍ ወጡ ።
36 ከዚህ በኋላ ጌዴዎን እግዚአብሔርን እን
ዲህ አለው ፥ “እስራኤላውያንን እታደግ ዘንድ
እኔን መምረጥህን ነግረኸኛል ፤ 37 እነሆ ስንዴ
በምንወቃበት አውድማ ላይ የበግ ጠጕር ባዘቶ
አስቀምጣለሁ ፤ ነገ ጠዋት በአካባቢው ባለው
ምድር ሳይሆን በዚህ ጠጕር ባዘቶ ላይ ብቻ
ጤዛ ከሆነ ፥ እስራኤልን ለመታደግ የመረጥኸኝ
መሆኑን ዐውቃለሁ ።” 38 ልክ እርሱ እንዳለ
ውም ሆነለት ፤ ጌዴዎን ጠዋት በማለዳ በተነሣ
ጊዜ የበግ ጠጕሩን ባዘቶ ሲጨምቀው በአንድ
መቅጃ የሚሞላ ውሃ ከውስጡ ወጣ ። 39 ቀጥ
ሎም ጌዴዎን እግዚአብሔርን እንዲህ አለው ፥
“እባክህ አትቈጣኝ ፤ እንደገና አንድ ጊዜ እንድ
ናገር ፍቀድልኝ ፤ ይኸውም በበግ ጠጕሩ ባዘቶ
ላይ ሌላ ምልክት እንዲታይ ልጠይቅ ፤ በዚህን
ጊዜ የጠጕሩ ባዘቶ ደረቅ ሆኖ በዙሪያው ያለው
ምድር እርጥብ እንዲሆን አድርግልኝ ።” 40 በዚ
ያን ሌሊት እግዚአብሔር ያንኑ ምልክት አደ
ረገ ፤ በማግሥቱ ጠዋት የጠጕሩ ባዘቶ ደረቅ
ሆኖ በዙሪያው ያለው መሬት ግን በጤዛ ርሶ
ተገኘ ።

## ምዕራፍ 7

### ጌዴዎን ምድያማውያንን ድል አደረገ

1 አንድ ቀን ጌዴዎንና ተከታዮቹ በጠዋት
ማልደው ተነሥተው በሐሮድ ምንጭ አጠገብ

ሰፈሩ ። የምድያማውያን ሰፈርም ከእነርሱ በስ
ተሰሜን በሞሬ ኮረብታ አጠገብ በሸለቆ ውስጥ
ነበር ።

2እግዚአብሔርም ጌዴዎንን እንዲህ አለው ፣
“በምድያማውያን ላይ ድልን አቀዳጃቸው ዘንድ
ከአንተ ጋር ያሉ ሰዎች ለእኔ እጅግ ብዙ ሆነ
ዋል ፤ በራሳቸው ኀይል የሚያሸንፉ በሰሚመስ
ላቸው ለእኔ ክብር ከመስጠት ይቈጠባሉ ፤ 3ስለ
ዚህ ለሕዝቡ ‘ከመካከላችሁ ፈሪ የሆነ ሰው ካለ
ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ ፤ እኛም በዚህ በገለ
ዓድ ተራራ ላይ እንቆያለን’ ብለህ ንገራቸው ።”
በዚህ ምክንያት ሃያ ሁለቱ ሺ ሲመለሱ ዐሥሩ
ሺ ቀሩ ።

4ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ጌዴዎንን እን
ዲህ አለው ፤ “አሁንም ገና ብዙ ሠራዊት
አሉህ ፤ እነርሱን ወደ ወንዝ ውሰዳቸውና በዚያ
እኔ የሚፈለጉትን እለይልሃለሁ ፤ ከአንተ ጋር
ይሂድ የምለው ሰው ይሂድ ፤ ይቅር የምለው
ሰው ደግሞ ይመለስ ።” 5ጌዴዎንም ሰዎቹን
ወደ ወንዝ ውሃ አወረዳቸው ፤ እግዚአብሔርም
“በጒልበቱ ተንበርክኮ ውሃ ከሚጠጣው መካ
ከል እንደ ውሻ በምላሱ እየጨለፈ የሚጠጣውን
ሁሉ ለየው” አለው ። 6በእጃቸው ውሃ እየዘገኑ
የሚጠጡት ቊጥር ሦስት መቶ ሆነ ፤ የቀሩት
ሁሉ የጠጡት ግን በጒልበታቸው ተንበርክከው
ነበር ። 7እግዚአብሔር ጌዴዎንን “በእጃቸው
ውሃ እየዘገኑ በጠጡት በእነዚህ ሦስት መቶ
ሰዎች አማካይነት እታደጋችኋለሁ ፤ በምድያማ
ውያንም ላይ ድልን አቀዳጃችኋለሁ ፤ ለቀሩት
ግን ወደቤታቸው እንዲመለሱ ንገራቸው”
አለው ። 8ስለዚህ ጌዴዎን የሕዝቡን ስንቅና
ቀንደ መለከቶቹን ከተረከበ·ት ከሦስት መቶዎቹ
በቀር ሌሎቹን እስራኤላውያን ሁሉ ወደየቤታ
ቸው እንዲመለሱ አሰናበታቸው ፤ ይህም ሁሉ
በሚሆንበት ጊዜ የምድያማውያን ሰፈር ከእነርሱ
በታች በሸለቆው ውስጥ ነበር ።

9በዚያም ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎንን
እንዲህ ሲል አዘዘው ፤ “ተነሥና በሰፈሩ ላይ
አደጋ ጣል ፤ እኔም ድልን አቀዳጅሃለሁ ፤
10አንተ በሰፈሩ ላይ አደጋ ለመጣል ከፈራህ
ግን ፑራ ተብሎ ከሚጠራው አገልጋይህ ጋር
ወደ ሰፈሩ ውረድ ፤ 11እነርሱም የሚሉትን
ትሰማለህ ፤ ከዚያም በኋላ በእነርሱ ላይ አደጋ
ለመጣል ድፍረት ታገኛለህ ፤” ስለዚህ ጌዴዎ
ንና አገልጋዩ ፑራ ወደ ጠላት ሰፈር ዳርቻ
ወረዱ ፤ 12ብዛታቸው እንደ አንበጣ መንጋ
የሆነ ምድያማውያን ፣ ዐማሌቃውያንና በስተም
ሥራቅ በኩል በበረሓ የሚኖሩ ነገዶች ፣ በሸለ
ቆው ውስጥ ሰፍረው ነበር ፤ ግመሎቻቸውም
ከብዛታቸው የተነሣ እንደ ባሕር ዳር አሸዋ
ሊቈጠር የማይቻል ነበር ።

13ጌዴዎን እዚያ በደረሰ ጊዜ አንድ ሰው
ያየውን ሕልም ለጓደኛው ሲነግረው ሰማ ፤ ሕል
ሙም እንዲህ የሚል ነበር ፤ “አንዲት የገብስ
ቂጣ ከላይ ተንከባልላ ወርዳ በሰፈራችን ያለውን
ድንኳን መታችው ፤ ድንኳኑም ተገልብጦ በም
ድር ላይ ተዘረጋ ።”

14ጓደኛውም “ይህማ የእስራኤላውያን
ሰይፍ የሆነው የዮአሽ ልጅ ጌዴዎን ነው ፤
ከቶ ሌላ ትርጒም ሊሰጠው አይችልም ፤ እግ
ዚአብሔር ለጌዴዎን በምድያምና በመላው
ሠራዊታችን ላይ ድልን ሰጥቶታል” ሲል መለ
ሰለት ።

15ጌዴዎን ስለ ሰውየው ሕልምና ስለ
ፍቹም ምንነት በሰማ ጊዜ በጒልበቱ ተንበርክኮ
ለእግዚአብሔር ሰገደ ፤ ወደ እስራኤላውያንም
ሰፈር ተመልሶ “ተነሡ ! እግዚአብሔር በምድ
ያማውያን ላይ ድልን ሊያቀዳጃችሁ ነው !”
አላቸው ። 16ሦስት መቶዎቹንም ሰዎች ከፍሎ
በሦስት ቡድን መደባቸው ፤ ለእያንዳንዱም
ሰው አንድ ቀንደ መለከትና በውስጡ ችቦ ያለ
በት አንድ ማሰሮ ሰጠ ። 17እንዲህም አላቸው ፤
“እኔ ወደ ሰፈሩ ዳርቻ ስደርስ ፣ የማደርገውን
በጥንቃቄ ተመልከታችሁ ያንኑ አድርጉ ።
18እኔና ከእኔ ጋር የተመደቡት ሰዎች በቀንደ
መለከቶቻችን ድምፅ ስናሰማ ፣ እናንተም የራሳ
ችሁን ቀንደ መለከት ድምፅ በሰፈሩ ዙሪያ እያ
ሰማችሁ ‘ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋ
ለን !’ ብላችሁ ጩኹ ።”

19ከእኩለ ሌሊት ጥቂት ቀደም ብሎ ፣ ዘብ
ጠባቂዎች ከተቀያየሩ በኋላ ጌዴዎንና ከእርሱ
ጋር የተመደቡት መቶ ሰዎች ወደ ሰፈሩ ዳርቻ
መጡ ፤ ቀንደ መለከቶቻቸውንም ነፉ ፤ የያዙት
ንም ማሰሮ ሁሉ ሰባበሩ ። 20በሌላም በኩል የነ
በሩት ሁለቱ ክፍሎች እንዲሁ አደረጉ ፤
ሁሉም የተለኮሱትን ችቦዎቻቸውን በግራ እጃ
ቸው ፣ ቀንደ መለከቶቻቸውን በቀኝ እጃቸው
ይዘው “ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋ
ለን !” እያሉ በመጮኽ ደነፉ ። 21እያንዳንዱ
ሰው በሰፈሩ ዙሪያ በተመደበለት ቦታ ቆመ ፤
መላው የጠላት ሠራዊትም የኡኡታ ድምፅ እያ
ሰማ ሸሸ ፤ 22የጌዴዎን ሰዎች ቀንደ መለከቶቻ
ቸውን በሚነፉበት ጊዜ እግዚአብሔር የጠላት
ወታደሮችን በገዛ ሰይፋቸው እንዲተላለቁ አደ
ረገ ፤ የተረፉትም ፊታቸውን ወደ ጸርታን በመ
መለስ እስከ ቤትሺጣ ፣ ከዚያም አልፈው በጣ
ባት አጠገብ እስካለው አቤልመሖላ ድረስ ሸሽ
ተው ሄዱ ።

23ከዚህ በኋላ የንፍታሌም ፣ የአሴርና ሁለቱ
የምናሴ ነገድ ክፍሎች ተጠርተው ወጥተው
ምድያማውያንን ማሳደድ ጀመሩ ፤ 24ጌዴዎ
ንም በኮረብታማው በኤፍሬም አገር ወዳሉት

7፥3 ፦ ዘዳ. 20፥8 ።

ሁሉ መልእክተኞች ልኮ “ወርዳችሁ ምድያማ
ውያንን ውጉ ፤ ምድያማውያን ተሻግረው እንዳ
ያመልጡ የዮርዳኖስን ወንዝና ወደ እርሱ የሚ
ገቡትንም መጋቢ ወንዞች እስከ ቤትባራ ድረስ
በር በሩን ዘግታችሁ በተጠናከረ ሁኔታ ጠብቁ”
አላቸው ። ስለዚህ የኤፍሬም ሰዎች በአንድነት
ተጠራርተው የዮርዳኖስን ወንዝና ወደዚያ የሚ
ገቡትን መጋቢ ወንዞች እስከ ቤተባራ ድረስ
ዘግተው ያዙ ። 25 ፆሬብና ዘኤብ የተባሉ ሁለት
የምድያማውያን መሪዎችንም ማረኩ ፤ ፆሬብን
“የፆሬብ አለት” ተብሎ ወደሚጠራው ስፍራ ፥
ዘኤብንም “የዘኤብ የወይን መጭመቂያ”
ተብሎ በሚጠራው ቦታ ገደሉአቸው ፤ ከዚህም
በኋላ የቀሩትን ምድያማውያን ማሳደድ
ቀጠሉ ፤ የፆሬብንና የዘኤብንም ራሶች ቈርጠው
ወደ ጌዴዎን አመጡለት ፤ በዚያን ጊዜ ጌዴ
ዎን ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ በኩል ነበረ ።

## ምዕራፍ 8

### የምድያማውያን የመጨረሻ መሸነፍ

1 ከዚህ በኋላ የኤፍሬም ሰዎች ጌዴዎንን
“ምድያማውያንን ለመውጋት ስትሄድ እኛን
ለምን አልጠራኸንም? ለምን እንዲህ አደረግ
ኸን?” ሲሉ በመረረ ሁኔታ ቅሬታቸውን በመግ
ለጥ አጕረመረሙ ።
2 እርሱ ግን እንዲህ አላቸው ፥ “እኔ ያደረግ
ሁት ሁሉ እናንተ ካደረጋችሁት ጋር ሲነጻጸር
እንዳልነበረ የሚቈጠር ነው ፤ የእኔ ጐሳ በሙሉ
ከሠራው ይልቅ ፥ እናንተ የኤፍሬም ሰዎች ያደ
ረጋችሁት ጥቂቱ ነገር እንኳ ይበልጣል ፤ 3 እና
ንተ በእግዚአብሔር ኀይል ሁለቱን የምድያማ
ውያን መሪዎች ፆሬብንና ዘኤብን ገደላችሁ ፤
ታዲያ እኔ ከዚህ ጋር የሚወዳደር ምን
ሠራሁ?” እርሱም ይህን ባለ ጊዜ ቍጣቸው
ተገታ ።
4 በዚህም ጊዜ ጌዴዎንና የእርሱ ሦስት
መቶ ሰዎች ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መጥተው
ተሻግረው ነበር ፤ ምንም እንኳ ድካም ቢሰማ
ቸው አሁንም ጠላትን በማሳደድ ላይ ነበሩ ።
5 ወደ ሱኮት በደረሱም ጊዜ ጌዴዎን ለከተማ
ይቱ ሰዎች እንዲህ አለ ፥ “እስቲ ለሰዎቼ እን
ጀራ ስጡልኝ ፤ እነርሱ እጅግ ደክመዋል ፤
እኔም ዜባሕና ጻልሙናዕ የተባሉትን የምድያማ
ውያን ነገሥታት በማሳደድ ላይ ነኝ ።”
6 የሱኮት መሪዎች ግን “ለአንተ ሠራዊት
ምግብ የምንሰጠው በምን ምክንያት ነው? ዜባ
ሕንና ጻልሙናዕን ገና አልማረክህም” አሉት ።
7 ጌዴዎንም “ደግ ነው! እግዚአብሔር ዜባ
ሕንና ጻልሙናዕን በእጄ አሳልፎ በሚሰጥበት
ጊዜ ከበረሓ በሚገኙ እሾኽና አሜከላ እገር
ፉችኋለሁ” አላቸው ። 8 ጌዴዎን ወደ ጵኑኤ
ልም ሄዶ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ያንኑ ጥያቄ
አቀረበላቸው ፤ ነገር ግን የጵኑኤልም ሰዎች
የሱኮት ሰዎች የሰጡትን ተመሳሳይ መልስ
ሰጡት ። 9 ስለዚህ እነርሱንም “ድልን ተቀዳ
ጅቼ በሰላም እመለሳለሁ ፤ በዚያን ጊዜ የከተማ
መጠበቂያ ግንባችሁን አፈርሳለሁ” አላቸው ።
10 ዜባሕና ጻልሙናዕ ከነሠራዊታቸው ቃርቆር
ተብሎ በሚጠራ ስፍራ ነበሩ ፤ ከበረሓ ነገዶች
ከተውጣጣው መላው ሠራዊት አንድ መቶ ሃያ
ሺ ያህል አልቆ የተረፈው ዐሥራ አምስት ሺ
የሚያህል ብቻ ነበር ። 11 ጌዴዎን መንገዱን
ተከትሎ በበረሓው ዳርቻ ከኖባሕና ከዮግበሃ በስ
ተምሥራቅ ገሥግሦ በዚያ ሠራዊት ላይ በድን
ገት አደጋ ጣለ ። 12 ሁለቱ የምድያማውያን ነገ
ሥታት ዜባሕና ጻልሙናዕ ሸሹ ፤ ነገር ግን
ጌዴዎን አሳድዶ ማረካቸው ፤ ሠራዊታቸውንም
በሙሉ በድንጋጤ ላይ እንዲወድቁ አደረገ ።
13 ጌዴዎን በሔሬስ መተላለፊያ በኩል ከጦ
ርነት ሲመለስ ፥ 14 አንድ ወጣት ከሱኮት ማርኮ
መረመረው ፤ ወጣቱም በሱኮት ታላላቅ መሪ
ዎች የነበሩትን የሰባ ሰባት ሰዎችን ስም ዝር
ዝር ጽፎ ሰጠው ። 15 ከዚህ በኋላ ጌዴዎን ወደ
ሱኮት ሰዎች መጥቶ “‘ዜባሕንና ጻልሙናዕን
ገና አልማረክህም ፤ ታዲያ አሁን በረሀብ ለደከ
ሙት ወታደሮችህ ምግብ የምንሰጠው ለምን
ድን ነው?’ ስትሉ ነበር ፤ ይሁን እንጂ ዜባሕና
ጻልሙናዕ እነሆ በእጄ ይገኛሉ” አላቸው ።
16 ከዚህ በኋላ እሾኽና አሜከላ ከበረሓ ወስዶ
የሱኮትን መሪዎች ገረፋቸው ። 17 በጵኑኤል
ያለውንም የከተማ መጠበቂያ ግንብ አፈረሰ ፤
በከተማይቱ ውስጥ የሚገኙትንም ወንዶች ሁሉ
ገደለ ።
18 ከዚህ በኋላ ጌዴዎን “በታቦር ስለገደ
ላችኋቸው ሰዎች ምን ታስባላችሁ?” ሲል ዜባ
ሕንና ጻልሙናዕን ጠየቀ ።
እነርሱም “አንተን ይመስሉ ነበር ፤ እያንዳን
ዳቸው የንጉሥ ልጅ ይመስላሉ” አሉት ።
19 ጌዴዎንም “እነርሱ የእናቴ ልጆች የሆኑ
ወንድሞቼ ነበሩ ፤ እናንተ እነርሱን ባትገድሉ
ኖሮ እኔም ምሕረት አደርግላችሁ እንደነበር
በእርግጥ እምላለሁ” አላቸው ። 20 ከዚህ በኋላ
የበኵር ልጁን ዬቴርን “በል አሁን ግደላ
ቸው!” ብሎ አዘዘው ። ልጁ ግን ሰይፉን ሳይ
መዝ ቀረ ፤ ገና ልጅ ስለነበር አመነታ ።
21 ከዚህ በኋላ ዜባሕና ጻልሙናዕ ጌዴዎንን
“በል እንግዲህ አንተው ራስህ ግደለን ፤ የወንድ
ነትን ሥራ ለመሥራት ወንድ ያጠይቃል
እኮ!” አሉት ፤ ስለዚህ ጌዴዎን እነርሱን
ገድሎ በግመሎቻቸው አንገት ላይ የነበረውን
ጌጣጌጥ በሙሉ ወሰደ ።

8፥3-5 ፦ መዝ. 83፥11 ።

22 ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን ጌዴዎንን
"አንተና ከአንተም በኋላ የሚነሡት ዘርያዎ
ችህ ገዥዎቻችን ሁኑ፤ ምክንያቱም አንተ ከም
ድያማውያን እጅ አድንኸናል" አሉት።
23 ጌዴዎንም "እኔም ሆንሁ ልጄ የእናንተ
ገዥዎች አንሆንም፤ የእናንተ ገዥ ራሱ እግዚ
አብሔር ነው" ሲል መለሰላቸው። 24 ቀጥሎም
"እሰቲ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ፤ እያንዳንዳ
ችሁ የወሰዳችሁትን የጆሮ ጉትቻ ስጡኝ" አላ
ቸው። (ምድያማውያን እንደ ሌሎቹ የበረሓ
ሰዎች የጆሮ ጉትቻ ማንጠልጠል ይወዱ
ነበር።)
25 ሕዝቡም "በደስታ እንሰጥሃለን" አሉት።
ልብስ አንጥፈውም እያንዳንዱ የወሰደውን
የጆሮ ጉትቻ በዚያ ላይ አኖረ። 26 ጌዴዎን የተ
ቀበለው የጆሮ ጉትቻ ሃያ ኪሎ ያህል የሚመ
ዝን ሆነ፤ ይህም ሌላውን ጌጣጌጥ፥ የአንገት
ሐብልና የምድያማውያን ነገሥታት ይለብሱት
የነበረውን ሐምራዊ ልብስ፥ እንዲሁም በግመ
ሎቻቸው አንገት ዙሪያ ያለውን ጌጥ ሳይጨ
ምር ነው። 27 ጌዴዎንም ከዚያ ወርቅ ኤፉድ
ሠርቶ በትውልድ ከተማው በዖፍራ አኖረው፤
እስራኤላውያንም በሙሉ ከእግዚአብሔር ተለይ
ተው ያንን ማምለክ ጀመሩ፤ ለጌዴዎንና ለቤተ
ሰቡ ሁሉ መሰናከያ ወጥመድ ሆነ።
28 በዚህ ዐይነት ምድያም ለእስራኤላውያን
ተሸነፈች፤ ዳግመኛም ለእስራኤላውያን የምታ
ሰጋ አልሆነችም፤ ጌዴዎን እስከሞተም ድረስ
በምድሪቱ ላይ አርባ ዓመት ሙሉ ሰላም ሆነ።

### የጌዴዎን ሞት

29 ጌዴዎን ወደ ተወለደበት ቦታ ሄዶ በዚያ
ኖረ፤ 30 ብዙ ሚስቶች ስላገባ ሰባ ወንዶች ልጆች
ነበሩት፤ 31 በሴኬም የምትኖርም ቁባት ነበረ
ችው፤ እርስዋም ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙ
ንም አቢሜሌክ ብሎ ጠራው። 32 የዮአሽ ልጅ
ጌዴዎን ዕድሜ ጠግቦ ሞተ፤ በአባቱም በዮአሽ
መቃብር ተቀበረ፤ ይህም መቃብር የአቢዔዜር
ጐሳ ከተማ በነበረችው በዖፍራ ይገኛል።
33 ጌዴዎን ከሞተ በኋላ የእስራኤል ሕዝብ
እንደገና ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት
አጉድለው ባዓል የተባሉትን ባዕዳን አማልክት
አመለኩ፤ ለባዓልበሪትም ሰገዱ። 34 ከዚያም
በኋላ በዙሪያቸው ከነበሩት ጠላቶቻቸው ሁሉ
ላዳናቸው ለአምላካቸው ለእግዚአብሔር አልሰገ
ዱም። 35 ለእስራኤል ያደረገውን መልካም ነገር
ሁሉ ካለማስታወሳቸው የተነሣ፥ ለጌዴዎን ቤተ
ሰብ ባለ ውለታዎች ሆነው አልተገኙም።

## ምዕራፍ 9

### አቢሜሌክ

1 የጌዴዎን ልጅ አቢሜሌክ የእናቱ ዘመዶች
ወደሚኖሩበት ወደ ሴኬም ከተማ ሄደ። 2 ዘመ
ዶቹም የሴኬምን ሕዝብ እንዲህ ብለው እንዲ
ጠይቁ ነገራቸው፥ "የቱን ትመርጣላችሁ? በሰ
ባውም የጌዴዎን ልጆች መገዛትን? ወይስ በአ
ንድ ሰው መገዛትን? አቢሜሌክ ለእናንተ የቅ
ርብ የሥጋ ዘመድ መሆኑን አትዘንጉ።" 3 የእና
ቱም ዘመዶች እርሱን ወክለው ይህንኑ ለሴኬም
ሰዎች ነገሩአቸው፤ የሴኬም ሰዎች ዘመዳቸው
ስለሆነ አቢሜሌክን ለመከተል ወሰኑ። 4 ባዓልበ
ሪትን ከሚያመልኩበት ቤት ሰባ ጥሬ ብር ወስ
ደው ሰጡት፤ አቢሜሌክም በዚያ በሰባ ጥሬ
ብር የማይጠቅሙ ዱርየ አዳሪዎችንና ወሮበሎ
ችን ቀጥሮ እንዲከተሉት አደረገ። 5 ወደ አባቱ
ቤት ወደ ዖፍራም ሄዶ የጌዴዎን ልጆች የሆኑ
ትን ሰባውን ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ
በረዳቸው፤ የጌዴዎን መጨረሻ ልጅ ኢዮአ
ታም ግን ተደብቆ ስለነበር ከሞት ተረፈ፤
6 ከዚያን በኋላ የሴኬምና የቤትሚሎ ሕዝብ
በአንድነት ተሰብስበው፥ በሴኬም ወደሚገኘው
ወደተቀደሰው ወርካ ዛፍ ሄዱ፤ በዚያም አቢሜ
ሌክን አነገሡ።
7 ኢዮአታም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ወደ ገሪ
ዛን ተራራ ጫፍ ላይ ወጥቶ እንዲህ በማለት
ወደ እነርሱ ጮኸ፥ "እናንተ የሴኬም ሰዎች!
እኔን ብታዳምጡኝ እግዚአብሔርም እናንተን
ያዳምጣችኋል! 8 ከዕለታት አንድ ቀን ዛፎች
ተሰብስበው በላያቸው ንጉሥ ሊያነግሡ ሄዱ፤
የወይራንም ዛፍ 'በእኛ ላይ ንገሥ' አሉት።
9 የወይራም ዛፍ 'በእናንተ ላይ ንጉሥ መሆን
ካስፈለገ ለአማልክትም ሆነ ለሰዎች ጠቃሚ
የሆነውን ዘይቴን መስጠት አቆማለሁ ማለት
ነው' አላቸው። 10 ከዚህ በኋላ ዛፎቹ የበለስን
ዛፍ 'መጥተህ በእኛ ላይ ንገሥ' አሉት። 11 የበ
ለስ ዛፍ ግን 'በእናንተ ላይ ንጉሥ መሆን ካስፈ
ለገ ጣፋጭ የሆነውን ፍሬዬን መስጠት አቆማ
ለሁ ማለት ነው' አላቸው። 12 ስለዚህ ዛፎቹ
የወይን ተክልን 'መጥተህ በእኛ ላይ ንገሥ'
አሉት። 13 የወይን ተክሉ ግን 'በእናንተ ላይ
መንገሥ ካስፈለገ ባዕዳን አማልክትንና ሰዎችን
የሚያስደስተውን የወይን ጠጄን መስጠት አቆ
ማለሁ ማለት ነው' ሲል መለሰላቸው። 14 ስለ
ዚህ ዛፎች ሁሉ የእሾኽ ቍጥቋጦን 'መጥተህ
በእኛ ላይ ንገሥ' አሉት። 15 የእሾኽ ቍጥቋ
ጦም 'በእርግጥ ንጉሥ ልታደርጉኝ ከፈለጋ
ችሁ፥ ኑና በጥላዬ ሥር ተጠለሉ፤ ይህን ባታደ
ርጉ ከእሾኽማዎቹ ቅርንጫፎቼ እሳት ወጥቶ
የሊባኖስን ዝግባዎች ያቃጥላል' ሲል መለሰላ
ቸው።"
16 ኢዮአታም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ
አላቸው፥ "አቢሜሌክን ስታነግሡ በእውነትና
ከልባችሁ ነውን? ጌዴዎን ያደረገውን በማስታ
ወስ ቤተሰቡን እንደሚገባ ረዳችሁለትን?
17 አባቴ ለእናንተ እንደተዋጋ አስታውሱ፤ እና
ንተንም ከምድያማውያን እጅ ለማዳን ሲል

አልተቋቋመም ፤ እኛንም ይወጋ ዘንድ ወደ
ጦርነት ለመውጣት አልደፈረም ፤ 26 ስለዚህ
ሦስት መቶ ዓመት ሙሉ እስራኤል ሐሴቦንን ፥
ዓሮዔርንና በእነርሱም ዙሪያ ያሉትን የገጠር
ከተሞች ፥ እንዲሁም በአርኖን ወንዝ ዳርቻ
ያሉትን ከተሞች በሙሉ ወርሰው ኖረዋል ፤
ታዲያ በነዚህ ዘመናት ሁሉ ስለምን መልሳችሁ
አልወሰዳችኋቸውም ነበር? 27 እኔ በበኩሌ
ምንም አልበደልኩም ፤ በእኔ ላይ ጦርነት በመ
ክፈት ልትበድለኝ የተነሣሣህ አንተ ነህ ፤ እንግ
ዲህ ፈራጅ እግዚአብሔር ነው ፤ እርሱ ዛሬ በእ
ስራኤላውያንና በሀሞናውያን መካከል ውሳኔ
ይሰጣል ።” 28 የሀሞን ንጉሥ ግን የዮፍታሔን
መልእክት ከቁም ነገር አልቈጠረውም ።

29 በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በዮ
ፍታሔ ላይ ወረደ ፤ ዮፍታሔም በገለዓድና በም
ናሴ ግዛቶች መካከል አቋርጦ ሄደ ፤ በገለዓድ
ወደምትገኘው ወደ ምጽጳ ተመለሰ ፤ ከዚያም
ወደ ዐሞን ጕዞውን ቀጠለ ። 30 ለእግዚአብሔ
ርም እንዲህ ሲል ተሳለ ፥ “በዐሞናውያን ላይ
ድልን ከሰጠኸኝ ፥ 31 ድል አድርጌ ከዘመቻ
ወደቤቱ ስመለስ ከቤት ወጥቶ ሊቀበለኝ የሚመ
ጣው ለአንተ ይሆናል ፤ እርሱንም ለአንተ የሚ
ቃጠል መሥዋዕት አድርጌ አቀርበዋለሁ ።”

32 ከዚህም በኋላ ዮፍታሔ ዐሞናውያንን
ለመውጋት ወንዙን ተሻግሮ ሄደ ፤ እግዚአብሔ
ርም ድልን አጐናጸፈው ። 33 ከዓሮዔር ጀምሮ
በሚኒት ዙሪያ እስካለው ስፍራ በአጠቃላይ ሃያ
ከተሞችን ፥ እንዲሁም እስከ አቤል ከራሚም
ድረስ ያሉትን ሁሉ ድባቅ መታ ፤ ብዙ ሕዝብ
ካለቀም በኋላ ዐሞናውያን በእስራኤል ውጊያ
ተሸነፉ ።

### የዮፍታሔ ሴት ልጅ

34 ዮፍታሔ በምጽጳ ወዳለው ቤቱ በተመለሰ
ጊዜ ሴት ልጁ አታሞ ይዛ እየዘፈነችና እየጨፈ
ረች ልትቀበለው ወጣች ፤ ያለ እርስዋም ሌላ
ልጅ አልነበረውም ። 35 ባያትም ጊዜ በሐዘን
ልብሱን በመቅደድ “ወይኔ ልጄ! ልቤን በሐ
ዘን ሰበርሽው! በእኔ ላይ ለሚደርሰው ሥቃይ
ስለምን አንቺ ምክንያት ሆንሽብኝ? እኔ ለእግዚ
አብሔር በመሐላ ቃል ገብቼ ተስያለሁ ፤ ልመ
ልሰውም አልችልም!” አለ ።

36 እርስዋም “አባቴ ሆይ! ለእግዚአብሔር
ቃል ገብተህ ከሆነስ ፥ እግዚአብሔር ጠላቶች
ህን ዐሞናውያንን ስለተበቀለልህ በእኔ ላይ ሊታ
ደርግ ያቀድከውን ፈጽም” አለችው ። 37 ነገር
ግን አባትዋን እንዲህ ስትል ጠየቀችው ፥
“ይህን አንድ ነገር ፍቀድልኝ ፤ ገና ልጃገረድ
ሳለሁ መሞቴ ስለሆነ ፥ ከጓደኞቼ ጋር በተራ
ራው ሄጄ አለቅስ ዘንድ የሁለት ወር ጊዜ ፍቀ
ድልኝ ።” 38 እርሱም እንድትሄድ ፈቅዶ ለሁ
ለት ወር አሰናበታት ፤ እርስዋና ጓደኞችዋም
ወደ ተራራዎች ወጡ ፤ ባል ሳታገባና ልጅ ሳት
ወልድ ለመሞት በመዘጋጀትዋም ስለ እርስዋ
አለቀሱላት ። 39 ከሁለት ወር በኋላ ወደ አባትዋ
ቤት ተመልሳ መጣች ፤ እርሱም ለእግዚአብ
ሔር ቃል የገባውን ፈጸመ ፤ እርስዋም ገና ድን
ግል እንደሆነች ሞተች ።

ከዚያም ጊዜ አንሥቶ ፥ 40 የእስራኤላውያን
ወጣት ሴቶች ልጆች በየዓመቱ ለአራት ቀን
ያህል ከቤታቸው ርቀው እየሄዱ ለገለዓዳዊው
ለዮፍታሔ ሴት ልጅ ማዘናቸውና ማልቀሳቸው
የተለመደ ሆነ ።

## ምዕራፍ 12

### ዮፍታሔና ኤፍሬማውያን

1 የኤፍሬም ሰዎች ለጦርነት ተዘጋጅተው
የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር ወደ ጻፎን በደረሱ
ጊዜ ዮፍታሔን “ዐሞናውያንን ለመውጋት
ወሰን አልፈህ ስትሄድ እኛን ያልጠራኸን ስለምን
ድን ነው? እንግዲህ እኛም ቤትህን በላይህ እና
ቃጥለዋለን” አሉት ።

2 ዮፍታሔም እንዲህ አላቸው ፥ “እኔና
ሕዝቤ ከዐሞናውያን ጋር በብርቱ ተጣልተን
በነበረበት ጊዜ እናንተን ጠርቼአችሁ ነበር ፤
ነገር ግን ከእነርሱ እጅ በመታደግ ልታድኑኝ
አልፈለጋችሁም ፤ 3 እናንተ እኔን ለመርዳት
ወደዚያ አለመሄዳችሁን ባየሁ ጊዜ ለሕይወቴ
ሳልሳሳ እነርሱን ለመውጋት ወሰኑን ተሻግሬ
ሄድሁ ፤ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ድልን
አቀዳጀኝ ፤ ታዲያ አሁን እኔን ለመውጋት የተነ
ሣችሁበት ምክንያት ምንድን ነው?” 4 ከዚህ
በኋላ ዮፍታሔ የገለዓድን ሰዎች አሰባስቦ በኤፍ
ሬም ሰዎች ላይ አደጋ በመጣል ድል አደረጋ
ቸው ፤ ምክንያቱም የኤፍሬም ሰዎች “እናንተ
በኤፍሬምና በምናሴ ግዛት ውስጥ የምትኖሩ
ገለዓዳውያን እኮ ኤፍሬምን ከድታችሁ የመጣ
ችሁ ናችሁ” ይሉአቸው ስለነበር ነው ። 5 የኤ
ፍሬም ሰዎች እንዳያመልጡ ለማድረግ ገለዓዳ
ውያን የዮርዳኖስን መሻገሪያ ቦታዎች ሁሉ ዘግ
ተው ያዙ ፤ ለማምለጥ የሚሞክር ማንኛውም
የኤፍሬም ሰው ለመሻገር ፈቃድ ቢጠይቅ ገለዓ
ዳውያን “አንተ የኤፍሬም ሰው ነህን?” ብለው
ይጠይቁት ነበር ፤ “አይደለሁም” ካለ ፥
6 “አስቲ ሺቦሌት” በል ይሉታል ፤ እርሱ ግን
“ሺ” የሚለውን ፊደል አስተካክሎ መናገር ስለ
ማይችል “ሲቦሌት” ይላል ፤ ከዚህ በኋላ እር
ሱን ይዘው የዮርዳኖስ መሸጋገሪያ ከሆኑት ስፍ
ራዎች በአንዱ ይገድሉታል ፤ ያንጊዜም በዚሁ
ሁኔታ አርባ ሁለት ሺ የኤፍሬም ሰዎች ተገ
ደሉ ።

11፡35 ፦ ዘኍ. 30፡2 ።

18 መልአኩም “ስሜን ለማወቅ የፈለግኸው
ለምንድን ነው? ስሜ ድንቅ የሆነ ምስጢራዊ
ነው” ሲል መለሰለት ።
19 ከዚህ በኋላ ማኑሄ አንድ የፍየል ጥቦትና
የእህል ቊርባን ወስዶ በአለቱ መሠዊያ ላይ ለእ
ግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ ፤ ማኑ
ሄና ሚስቱም እየተመለከቱ ሳለ እግዚአብሔር
አስደናቂ ነገር አደረገ ። 20-21 የእሳት ነበልባል
ከመሠዊያው ወደ ላይ በሚወጣበት ጊዜ ማኑ
ሄና ሚስቱ የእግዚአብሔር መልአክ በነበልባሉ
ውስጥ ወደ ሰማይ ሲወጣ አዩ ፤ ማኑሄም በዚህ
ጊዜ ያ ሰው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን
ተገነዘበ ፤ እርሱና ሚስቱም በግንባራቸው ወደ
መሬት ተደፉ ፤ ዳግመኛም መልአኩን አላ
ዩም ።
22 ማኑሄ ሚስቱን “እግዚአብሔርን ስላየን
በእርግጥ እንሞታለን” አላት ።
23 ሚስቱ ግን “እግዚአብሔር ሊገድለን ቢፈ
ልግ ኖሮ መሥዋዕታችንንና ቊርባናችንን ባልተ
ቀበለም ነበር ፤ ይህን ሁሉ አሁን ባላሳየንና እን
ዲህ ያለውን ነገር ሁሉ ባልነገረንም ነበር”
ስትል መለሰችለት ።
24 ሴቲቱም ወንድ ልጅ ወለደች ፤ ስሙንም
ሳምሶን ብላ ጠራችው ፤ ሕፃኑም አደገ ፤ እግዚ
አብሔርም ባረከው ፤ 25 በጾርዓና በኤሽታኦል
መካከል ባለው በዳን ሰፈር ውስጥ በነበረበት
ጊዜ የእግዚአብሔር ኀይል ያበረታው ጀመር ።

## ምዕራፍ 14
### የሳምሶን ጋብቻ

1 አንድ ቀን ሳምሶን ወደ ቲምና ወረደ ፤
በዚያም አንዲት ፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ
አየ ፤ 2 ወደ ቤቱም ተመልሶ ለአባቱና ለእናቱ
“በቲምና አንዲት ፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ
አይቼ ወድጃታለሁ ፤ ስለዚህ እርስዋን እጮኛ
ችሁ አጋቡኝ” አላቸው ።
3 አባቱና እናቱ ግን “ሚስት ለማግኘት እረ
ማውያን ወደ ሆኑ ፍልስጥኤማውያን መሄድ
ለምን አስፈለገህ? ከሕዝባችን ሁሉ መካከል
የራሳችን ጐሳ የሆነች ልጃገረድ ማግኘት አቅ
ቶህ ነውን?” ሲሉ ጠየቁት ።
ሳምሶን ግን አባቱን “እኔ እርስዋን በጣም
ስለምወዳት ከእርስዋ ጋር አጋባኝ” አለው ።
4 ሳምሶን ይህን እንዲያደርግ የሚመራው
እግዚአብሔር እንደሆነ ወላጆቹ አላወቁም ፤
በዚያም ጊዜ ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያ
ንን ይገዙ ስለነበር ፥ እግዚአብሔር ፍልስጥኤማ
ውያንን ለመቃወም ምክንያት ይፈልግ ነበር ።
5 ከዚህ በኋላ ሳምሶን ከአባቱና ከእናቱ ጋር
ወደ ቲምና ወረደ ፤ እዚያም በወይን ተክል
ውስጥ አልፈው ሲሄዱ አንድ ደቦል አንበሳ እያ
ገሣ መጣበት ፤ 6 በድንገትም የእግዚአብሔር
ኀይል ሳምሶንን አበረታው ፤ ስለዚህም አንበሳ
ውን እንደ አንድ የፍየል ጥቦት ያህል በመቆ
ጠር ያለ ምንም መሣሪያ በባዶ እጁ ገነጣጥሎ
ጣለው ፤ ያደረገውንም ነገር ለወላጆቹ አልነገራ
ቸውም ።
7 ከዚህ በኋላ ወደ ልጃገረዲቱ ሄዶ አነጋገ
ራት ፤ ወደዳትም ፤ 8 ከጥቂት ቀናት በኋላ እርስ
ዋን ለማግባት ወደዚያ ተመልሶ ሄደ ፤ በጕዞም
ላይ ሳሉ ያንን የገደለውን አንበሳ ሁኔታ ለማየት
ከመንገድ ዞር አለ ፤ በድኑን ንቦች ሰፍረውበት
በውስጡም ማር መኖሩን በተመለከተ ጊዜ
እጅግ ተደነቀ ፤ 9 ከማሩም ጥቂት በእጁ ቈርጦ
እየበላ መንገዱን ቀጠለ ፤ ወደ አባቱና ወደ
እናቱ ቀርቦ ከያዘው ማር ሰጥቶአቸው በሉ ፤
ነገር ግን ሳምሶን ያንን ማር ያገኘው ከሞተው
አንበሳ በድን ውስጥ መሆኑን አልነገራቸውም ።
10 አባቱ ወደ ልጃገረዲቱ ቤት በሄደ ጊዜ ፥
ሳምሶን በዚያ ትልቅ ግብዣ አደረገ ፤ ይህም
ዐይነቱ ግብዣ በወጣቶች ዘንድ የተለመደ
ነበር ፤ 11 ፍልስጥኤማውያን እርሱን ባዩት ጊዜ
ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ ሠላሳ ወንዶች ወጣቶችን
መርጠው ላኩለት ። 12 ሳምሶንም እንዲህ አላ
ቸው ፥ “እስቲ ታውቁ እንደሆን አንድ እንቆቅ
ልሽ ልንገራችሁ ፤ በሰባቱ የሠርጉ በዓል ቀኖች
ውስጥ ይህን እንቆቅልሽ ፈትታችሁ ብትነግ
ሩኝ ፥ ሠላሳ የበፍታ ቀሚስና ሠላሳ ቅያሬ
ልብስ እሰጣችኋለሁ ፤ 13 ፍቹን መንገር ባት
ችሉ ግን ሠላሳ የበፍታ ቀሚስና ሠላሳ ቅያሬ
ልብስ ትሰጡኛላችሁ ።”
እነርሱም “እንቆቅልሽን ንገረን ፤ እስቲ እን
ስማው” አሉት ።
14 እርሱም
“ከበላተኛው መብል ተገኘ ፤
ከብርቱውም ጣፋጭ ነገር ወጣ”
አላቸው ።
እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንቆቅልሹን መፍታት
አልቻሉም ።
15 በአራተኛው ቀን የሳምሶንን ሚስት እን
ዲህ አሉአት ፥ “ባልሽን አግባብተሽ የእንቆቅል
ሹን ፍች እንዲነግረን አድርጊ ፤ ይህን ካላደረ
ግሽ ግን የአባትሽን ቤት በእሳት አያይዘን አንቺ
ንም በውስጡ በመጨመር እናቃጥልሻለን ፤
ለካስ እናንተ ሁለታችሁም ወደ ግብዣችሁ
የጠራችሁን ልትዘርፉን ኖሮአልን?”
16 ስለዚህ የሳምሶን ሚስት እያለቀሰች ወደ
እርሱ ቀርባ “ለካስ አንተ እኔን አትወደኝም!
እንዲያውም በብርቱ ትጠላኛለህ ፤ ምክንያቱም
ወዳጆቼን እንቆቅልሽ ጠይቀህ ለእኔ እስከ አሁን
ፍችውን አልነገርኸኝም” አለችው ።

13፥18 ፥ ዘፍ. 32፥29 ።

እርሱም "ተመልከቺ! እኔ ይህን ለአባቴና
ለእናቴ እንኳ አልነገርኋቸውም፤ ታዲያ
ለአንቺ የምነግርበት ምክንያት ምንድን
ነው?" አላት። 17 ከዚህም የተነሣ እርስዋ
በሠርጉ በዓል ሰባት ቀን ሙሉ አለቀሰች፤
አጥብቃም ስለነዘነዘችው የእንቆቅልሹን ፍች
በሰባተኛው ቀን ነገራት፤ እርስዋም ሄዳ ለፍ
ልስጥኤማውያኑ ነገረቻቸው። 18 ስለዚህ በሰባ
ተኛው ቀን ፀሐይ ከመጥለቁ በፊት፥ የከተማ
ይቱ ሰዎች

"ከማር የጣፈጠ፥
ከአንበሳስ የበረታ ምን አለ?"

ሲሉ የእንቆቅልሹን ፍች ነገሩት።
ሳምሶንም

"በእኔ ጊደር ባታርሱ ኖሮ፥
መልሱን ማግኘት ባልቻላችሁም
ነበር" አላቸው።

19 የእግዚአብሔርም ኀይል በድንገት ብር
ታት ሰጠው፤ ወደ አስቀሎናም ወርዶ ሠላሳ
ሰዎችን ገደለ፤ ውብ የሆነውንም ልብሳቸውን
ሁሉ በመግፈፍ አምጥቶ የእንቆቅልሹን ፍች
ላወቁት ሰዎች ሰጣቸው። በሆነውም ነገር ሁሉ
እጅግ ተቈጥቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ 20 ሚስቱም
በሠርጉ ዋና ሚዜ ለነበረው ሰው ተዳረች።

## ምዕራፍ 15

1 ከጥቂት ጊዜ በኋላ በስንዴ መከር ወራት
ሳምሶን ሚስቱን ለመጐብኘት አንድ የፍየል
ጠቦት ይዞ ሄደ፤ አባትዋንም "ሚስቴ ወዳለች
በት ክፍል መግባት እፈልጋለሁ" አለው።
አባትዋ ግን እንዲገባ አልፈቀደለትም፤
2 ሳምሶንንም "አንተ የጠላሃት ስለመሰለኝ
ሚዜህ ለነበረው ሰው ዳርኋት፤ የሆነ ሆኖ
የእርስዋ ታናሽ ይበልጥ ውብ ስለሆነች በዚ
ያች ፈንታ ይህችን ማግባት ትችላለህ"
አለው።
3 ሳምሶንም "ከእንግዲህ ወዲህ በፍልስጥኤ
ማውያን ላይ ስለምወስደው እርምጃ በኀላፊነት
አልጠየቅበትም" አለ። 4 ሄዶም ሦስት መቶ
ቀበሮዎችን በማደን ያዘ፤ ጥንድ ጥንድ አድርጎ
ጭራቸውን በማያያዝ በገመድ አሰረ፤ ችቦዎ
ችም አምጥቶ በጭራቸው መካከል አሰረ።
5 ከዚያም በኋላ በችቦዎቹ ላይ እሳት በማቀጣ
ጠል ቀበሮዎቹን ገና ወዳልታጨደው ወደ
ፍልስጥኤማውያን የስንዴ ሰብል ውስጥ ለቀቃ
ቸው፤ በዚህም ዐይነት ሁኔታ ታጭዶ የተከመ
ረውን ብቻ ሳይሆን ገና በማሳ ላይ ያለውን
ስንዴ፥ የወይራና የወይን ተክል ጭምር አቃ
ጠለ። 6 ፍልስጥኤማውያን ይህን ያደረገው ማን
እንደሆነ በጠየቁ ጊዜ፥ ሳምሶን መሆኑን
ተረዱ፤ ምክንያቱም የቲምና ተወላጅ የሆነው
ዐማቱ የሳምሶንን ሚስት ሚዜው ለነበረ ሌላ
ሰው ሰጥቶበት ነበር፤ ስለዚህ ፍልስጥኤማው
ያን ሄደው ሴቲቱንና አባቷን በእሳት አቃ
ጠሉ።
7 ሳምሶንም "እንግዲህ እናንተ ይህን አድር
ጋችኋል፤ እኔ ደግሞ እናንተን ሳልበቀል እንደ
ማልተዋችሁ እምላለሁ" ብሎ ነገራቸው።
8 ወዲያውም ብርቱ አደጋ ጥሎባቸው ከእነርሱ
ብዙዎችን ገደለ፤ ከዚህም በኋላ ሄዶ ዔጣም
ተብላ በምትጠራ ስፍራ በዋሻ ውስጥ ተቀ
መጠ።

### ሳምሶን ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረገ

9 ፍልስጥኤማውያን መጥተው በይሁዳ
ሰፈሩ፤ ሌሒ ተብላ በምትጠራ ከተማም ላይ
አደጋ ጣሉባት፤ 10 የይሁዳም ሰዎች "በእኛ
ላይ አደጋ የምትጥሉት ስለምንድን ነው?"
ሲሉ ጠየቁአቸው።
እነርሱም "እኛ የመጣነው ሳምሶንን ልንይ
ዝና እስረኛ አድርገን ወስደን በእኛ ላይ ያደረገ
ውን ሁሉ በእርሱም ላይ ልንፈጽምበት ነው"
ሲሉ መለሱላቸው። 11 ስለዚህም ሦስት ሺ የሚ
ሆኑ የይሁዳ ሰዎች በዔጣም ወዳለው ዋሻ
ሄደው "ፍልስጥኤማውያን ገዢዎቻችን እንደ
ሆኑ አታውቅምን? ታዲያ ይህ ያደረግህብን
ምንድን ነው?" ሲሉ ሳምሶንን ጠየቁት።
እርሱም "እኔ በእነርሱ ላይ ያደረግሁት ልክ
እነርሱ በእኔ ላይ ያደረጉትን ነው" አላቸው።
12 እነርሱም "እኛ አሁን ወደዚህ የመጣ
ነው አንተን አስረን ለእነርሱ አሳልፈን ልንሰጥህ
ነው" አሉት።
ሳምሶንም "እናንተ ራሳችሁ እንደማትገድ
ሉኝ ቃል ግቡልኝ" አላቸው።
13 እነርሱም "መልካም ነው፤ አንተን በገ
መድ አስረን ለእነርሱ አሳልፈን እንሰጥሃለን
እንጂ እኛስ አንገድልህም" ሲሉ መለሱለት።
ከዚህም በኋላ በሁለት አዳዲስ ገመዶች አሰሩ
ትና ከዋሻው አውጥተው ወሰዱት።
14 ሳምሶንም ወደ ሌሒ በሄደ ጊዜ፥ ፍልስ
ጥኤማውያን እየተሯሯጡ ወደ እርሱ መጥ
ተው ደነፉበት፤ በድንገትም የእግዚአብሔር
ኀይል አበረታው፤ እጆቹ ላይ ተጠምጥመው
የታሰረባቸውን ገመዶች ልክ እሳት እንደነካው
ፈትል በጣጥሶ ጣለ፤ 15 ከዚህ በኋላ በቅርብ
ጊዜ የሞተ የአንድ አህያ መንጋጋ አገኘ፤
ጐንበስ ብሎ አንሥቶም አንድ ሺ ሰው ገደለ
በት።
16 ሳምሶንም፥

"በአህያ መንጋጋ አንድ ሺ ሰው
ገደልሁ፤
በዚህም የአህያ መንጋጋ
ሬሳውን በሬሳ ላይ ከመርሁ" ሲል
በመቀኘት ዘመረ።

[17]ከዚያም በኋላ ይዞት የነበረውን መንጋጋ
ወረወረው፤ ይህም የተፈጸመበት ያ ስፍራ
“ራማት ሌሒ”[7*] ተብሎ ተጠራ።
[18]ከዚህ በኋላ ሳምሶን እጅግ ስለተጠማ
“ይህን የመሰለ ታላቅ ድል ሰጠኸኝ፤ ታዲያ
አሁን በውሃ ጥም ልሞት ነውን? በእነዚህስ
አረማውያን በሆኑት ፍልስጥኤማውያን ልማረክ
ነውን? ሲል የእግዚአብሔርን ስም ጠራ።”
[19]እግዚአብሔርም በዚያችው በሌሒ የነበረውን
አንድ ጕድጓድ ከፈተለት፤ ከእርሱም ውሃ
ወጣ፤ ሳምሶንም ያንን ጠጥቶ በጣም ስለረካ
ብርታት አገኘ፤ ስለዚህም ያ ምንጭ
“ሃቆሬ”[8*] ተብሎ ተጠራ፤ እስከዛሬም ድረስ
በሌሒ ይገኛል።
[20]ፍልስጥኤማውያን በሀገሩ ላይ ገዥዎች
በነበሩበት ዘመን ሳምሶን እስራኤልን ለሃያ
ዓመት ሙሉ መራ።

## ምዕራፍ 16

### ሳምሶን በጋዛ

[1]አንድ ቀን ሳምሶን የፍልስጥኤማውያን
ከተማ ወደሆነችው ወደ ጋዛ ሄደ፤ እዚያም አን
ዲት አመንዝራ ሴት አግኝቶ ከእርስዋ ጋር ለማ
ደር ወደ ቤትዋ ገባ፤ [2]የጋዛም ሰዎች ሳምሶን
በዚያ መኖሩን ሰምተው ያንን ቦታ በመክበብ
በከተማይቱ በር ሌሊቱን ሙሉ ሲጠብቁት
አደሩ፤ “እስኪነጋ ጠብቀን እንገድለዋለን”
ብለው በማሰብ ሌሊቱን ሙሉ ጸጥ አሉ፤
[3]ነገር ግን ሳምሶን ከሴቲቱ ጋር ተኝቶ የቆየው
እስከ እኩለ ሌሊት ብቻ ነበር፤ ከዚያን በኋላ
ከመኝታው ተነሣ፤ የከተማይቱን ቅጽር በር፥
ሁለቱን ምሰሶዎችና መቈለፊያዎቹን ሁሉ ፈነ
ቃቀለው፤ ያንን ሁሉ በትከሻው ተሸክሞ ከኬ
ብሮን ፊት ለፊት እስካለው ኮረብታ ድረስ ወስ
ደው።

### ሳምሶንና ደሊላ

[4]ከዚህ በኋላ ሳምሶን በሶሬቅ ሸለቆ የምት
ኖር ደሊላ ተብላ የምትጠራ አንዲት ሴት
ወደደ፤ [5]አምስቱ የፍልስጥኤማውያን ነገሥ
ታት ወደ እርስዋ ሄደው እንዲህ አሉአት፥
“ሳምሶንን አግባብተሽ ይህን ሁሉ ብርታት ያገ
ኘው ከምን እንደሆነና እንዴትስ አስረን በቊጥ
ጥራችን ሥር በማድረግ ልናሸንፈው እንደምን
ችል ጠይቂው፤ እያንዳንዳችንም አንድ ሺ
አንድ መቶ ጥሬ ብር እንሰጥሻለን።”
[6]ስለዚህ ደሊላ ሳምሶንን “ይህን ያህል
ብርቱ የሚያደርግህ ምን እንደሆን እባክህ ንገ
ረኝ፤ አንድ ሰው አንተን አስሮ ሊያደክምህ
የሚችለው እንዴት ነው?” አለችው።
[7]ሳምሶንም “እርጥብ በሆኑ ሰባት አዳዲስ
ጠፍሮች ቢያስሩኝ እንደማንኛውም ሰው ደካማ
እሆናለሁ” አላት።
[8]ከዚህ በኋላ የፍልስጥኤማውያን ነገሥታት
እርጥብ የሆኑ ሰባት አዳዲስ ጠፍሮችን ለደሊላ
ይዘውላት መጡ፤ እርስዋም በእርሱ ሳምሶንን
አሰረችው። [9]በሌላ ክፍል ሆነው የሚጠባበቁ
ወንዶች ስለነበሩ “ሳምሶን! ፍልስጥኤማውያን
መጡብህ!” ስትል ጮኸች፤ እርሱ ግን ፈትል
እሳት ሲነካው እንደሚበጣጠስ ጠፍሮቹን በጣ
ጠሳቸው፤ ስለዚህ አሁንም ብርታት የሚያገኝበ
ትን ምስጢር ገና አልደረሱበትም ነበር።
[10]ደሊላም ሳምሶንን “እነሆ አታለልከኝ፤
እውነቱንም አልነገርከኝም፤ አሁንም አንተን
እንዴት ማሰር እንደሚቻል እባክህ ንገረኝ”
አለችው።
[11]እርሱም “ሥራ ባልተሠራበት አዲስ
ገመድ ቢያስሩኝ እንደማንኛውም ሰው ደካማ
እሆናለሁ” ሲል መለሰላት።
[12]ደሊላም አዲስ ገመድ ወስዳ አሰረችው፤
በሌላ ክፍል ሆነው የሚጠባበቁ ወንዶች ስለነ
በሩ “ሳምሶን! ፍልስጥኤማውያን መጡብህ!”
ስትል ጮኸች፤ እርሱ ግን ገመዱን ከክንዱ
እንደ ፈትል በጣጠሰው።
[13]ደሊላም ሳምሶንን “እስከ አሁን ድረስ
አሞኘኸኝ፤ እውነቱንም አልነገርኸኝም፤ አሁ
ንም አንተን እንዴት ማሰር እንደሚቻል እባክህ
ንገረኝ” አለችው።
እርሱም “የራሴን ጠጕር ሰባቱን ቁንዳላዎች
ከድር ጋር ብትጐነጕኚው፥ በችካልም ብትቸከ
ዪው እንደማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ”
አላት።
[14]ከዚህ በኋላ ደሊላ ሳምሶንን እየደባበሰች
እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገች፤ የራሱንም
ጠጕር በባቱን ቁንዳላዎች ከድር ጋር ጐንጕና
በችካል ቸከለችው፤ ከዚያ በኋላ “ሳምሶን!
ፍልስጥኤማውያን መጡብህ!” ብላ ጮኸች፤
እርሱ ግን ከእንቅልፉ ነቅቶ ጠጕሩን ከችካሉና
ከድሩ ላይ ነቀለው።
[15]ስለዚህ እርስዋ “ልብህ ከእኔ ጋር ሳይሆን
እንዴት እወድሻለሁ ትለኛለህ? ሦስት ጊዜ
አታለልከኝ፤ እስከ አሁንም ይህን ሁሉ ብር
ታት ያገኘኸው ከምን እንደሆነ አልነገርኸ
ኝም” አለችው። [16]ዕለት ዕለትም እየነዘነዘች
በብርቱ ስላስቸገረችውና ስላሰለቸችው፥ [17]በመ
ጨረሻ እውነቱን ነገራት፤ እንዲህም አላት
“ከተወለድሁበት ጊዜ ጀምሮ በናዝራዊነት ለእ
ግዚአብሔር የተለየሁ ስለሆነ ጠጕሬ ተላጭቶ
አያውቅም፤ ጠጕሬ ቢላጭ ግን ኀይል ተለይ
ቶኝ እንደማንኛውም በው ደካማ እሆናለሁ።”

---

7* 15፥17 ራማት ሌሒ ፦ በዕብራይስጥ “የመንጋጋ ኮረብታ” ማለት ነው።
8* 15፥19 ሃቆሬ ፦ በዕብራይስጥ “የሚጣራ” ማለት ነው።

18 ደሊላ እውነቱን እንደነገራት በተረዳች
ጊዜ "እውነቱን ስለነገረኝ አንድ ጊዜ ተመልሳ
ችሁ ኑ" ስትል ወደ ፍልስጥኤማውያን ነገሥ
ታት መልእክት ላከች ። እነርሱም ገንዘቡን
ይዘው መጡ ። 19 ደሊላ ሳምሶንን በጭንዋ ላይ
አጋድማ እየደባበሰች እንቅልፍ እንዲወስደው
አደረገች ፤ አንድ ሰውም ጠርታ ሰባቱን የጠጕ
ሩን ቁንዳላዎች እንዲላጭ አደረገች ፤ ኀይሉም
ከእርሱ ተለይቶት ስለነበር በማዋረድ ታሰጨን
ቀው ነበር ፤ 20 ከዚያም በኋላ "ሳምሶን! ፍልስ
ጥኤማውያን መጡብህ!" አለችው ፤ እርሱም
ከእንቅልፉ ነቅቶ "እንደ ወትሮው በጣጥሼ እሄ
ዳለሁ" ብሎ አሰበ ፤ እግዚአብሔርም እንደተለ
የው አላወቀም ነበር ፤ 21 ፍልስጥኤማውያንም
ከማረኩት በኋላ ሁለቱን ዐይኖቹን አወጡ ፤
ወደ ጋዛም ወስደው በነሐስ ሰንሰለት በማሰር
በታሰረበት ቤት እህል እንዲፈጭ አደረጉት ፤
22 በዚያን ጊዜ ውስጥ ፥ ጠጕሩ እንደገና ማደግ
ጀመረ ።

የሳምሶን አሟሟት

23 የደስታ በዓል ለማዘጋጀትና ለአምላካቸ
ውም ለዳጎን ታላቅ መሥዋዕት ለማቅረብ የፍል
ስጥኤማውያን ነገሥታት በአንድነት ተሰበሰቡ ፤
"አምላካችን በጠላታችን በሳምሶን ላይ ድልን
እንድንቀዳጅ አድርጎናል!" ሲሉም ዘመሩ ።
24-25 እጅግም ደስ ብሎአቸው ስለነበር "በፊታ
ችን እየተጫወተ እንዲያስደስተን ሳምሶንን
ጥሩት" አሉ ፤ ሳምሶንንም ከእስር ቤት አውጥ
ተው በማምጣት ያስደስታቸው ዘንድ በምሰሶች
መካከል አቆሙት ፤ ሕዝቡም ባዩት ጊዜ
"ምድራችንን ባጠፋውና ከእኛም ብዙዎቻችን
በገደለው ጠላታችን ላይ አምላካችን ድልን አቀ
ዳጅቶናል" በማለት አምላካቸውን በዝማሬ
አመሰገኑ ። 26 ሳምሶንም እጁን ይዞ የሚመራ
ውን ልጅ ፥ "ሕንጻውን ደግፈው የያዙትን ምሰ
ሶዎች አስጨብጠኝና እነርሱን ተደግፌ
ልቁም" አለው ። 27 በሕንጻውም ውስጥ ብዙ
ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም አምስቱ የፍልስጥ
ኤማውያን ነገሥታት ነበሩ ፤ በጣራ ላይ ሆነው
ሳምሶን ሲያጫውታቸው የሚመለከቱ ሦስት ሺ
ወንዶችና ሴቶች ነበሩ ።
28 ከዚህ በኋላ ሳምሶን "ልዑል እግዚአብ
ሔር ሆይ! እባክህ አስበኝ ፤ አምላኬ ሆይ! እባ
ክህ አንድ ጊዜ ኀይሌን መልስልኝና ፍልስጥኤ
ማውያን ዐይኖቼን ስላወጡ አንድ ጊዜ ብቻ እን
ድበቀላቸው አድርገኝ" ብሎ ጸለየ ። 29 ስለዚህ
ሳምሶን ሕንጻውን ደግፈው የያዙትን ሁለቱን
መካከለኛ ምሰሶዎች ጨበጠ ፤ በአንድ እጁ አን
ዱን ምሰሶ ፥ በሌላ እጁም ሌላውን ምሰሶ ከያዘ
በኋላ ፥ 30 "ሕይወቴ ከፍልስጥኤማውያን ጋር
ትለፍ!" ብሎ ጮኸ ፤ በሙሉ ኀይሉም በገፋ
ቸው ጊዜ ሕንጻው በአምስቱ ነገሥታትና እዚያ
ባሉት ሁሉ ላይ ተደረመሰ ፤ ሳምሶንም በሕይ
ወቱ ሳለ ከገደላቸው ይልቅ በሞተበት ጊዜ የገ
ደላቸው በዙ ።
31 ወንድሞቹና የቀሩት ቤተሰቡ ሁሉ ሬሳ
ውን ለማግኘት መጡ ፤ ወስደውም በጾርዓና
በኤሽታኦል መካከል በሚገኘው በአባቱ በማኑሄ
መቃብር ቀበሩት ፤ ሳምሶን ሃያ ዓመት ሙሉ
እስራኤልን መራ ።

## ምዕራፍ 17

### ሚካ ያሠራቸው ጣዖታት

1 ሚካ ተብሎ የሚጠራ አንድ ሰው በኰረብ
ታማው በኤፍሬም አገር ይኖር ነበር ፤ 2 ሚካም
አንድ ቀን እናቱን እንዲህ አላት ፥ "አንድ ሰው
አንድ ሺ አንድ መቶ ጥሬ ብር በሰረቀሽ ጊዜ
ያንን የሰረቀሽን ሰው ስትረግሚው ሰምቼሽ
ነበር ፤ እነሆ ያ ገንዘብ በእኔ እጅ ነው ፤ እርሱ
ንም የወሰድሁ እኔ ነበርሁ ።"
እናቱም "ልጄ እግዚአብሔር ይባርክህ"
አለችው ። 3 ልጁም ገንዘቡን መልሶ ለእናቱ
ሰጣት ፤ እርሰዋም "እርግማኑ በልጄ ላይ እንዳ
ይደርስ እኔ ራሴ ብሩን ለእግዚአብሔር የተለየ
አደርገዋለሁ ፤ ከእንጨት ተሠርቶ በብር የተለ
በጠ ጣዖት ማሠሪያም ይሆናል ፤ ስለዚህ ብሩን
ለአንተ መልሼ እሰጥሃለሁ" አለችው ። 4 ልጁም
ብሩን ለእናቱ ሰጣት ፤ እርሰዋም ከላዩ ሁለት
መቶ ብር አንሥታ እንጨት ጠርቦ በብር በመለ
በጥ ጣዖት ለሚሠራላት የብር አንጥረኛ ሰጠ
ችው ፤ ጣዖቱም በሚካ ቤት ተቀመጠ ።
5 ይህ ሚካ የተባለ ሰው የራሱ የሆነ የአም
ልኮ ስፍራ ነበረው ፤ በርከት ያሉ ጣዖታትና
አንድ ኤፉድ ሠርቶ ከልጆቹ አንዱን ካህን ሆኖ
እንዲያገለግለው ሾመው ፤ 6 በዚያን ጊዜ በእስራ
ኤል ንጉሥ አልነበረም ፤ እያንዳንዱም ሰው
ለራሱ ደስ ያለውን ነገር ሁሉ እንደፈለገ ያደ
ርግ ነበር ።
7 በዚያን ወቅት በይሁዳ ግዛት በቤተልሔም
ከተማ የሚኖር አንድ ወጣት ሌዋዊ ነበር ፤
8 ይህም ሰው የሚኖርበትን ስፍራ ለማግኘት
ከቤተልሔም ተነሥቶ ሄደ ፤ በጕዞም ላይ ሳለ
በኰረብታማው በኤፍሬም አገር ወደሚገኘው
ወደ ሚካ ቤት መጣ ፤ 9 ሚካም "ከወዴት
መጣህ?" አለው ።
እርሱም "እኔ በይሁዳ ግዛት ከምትገኘው
ከቤተልሔም የመጣሁ ሌዋዊ ነኝ ፤ የምኖርበ
ትን ስፍራ እየፈለግሁ ነው" ሲል መለሰለት ።
10 ሚካም "እንግዲያውስ ከእኔ ጋር ኑር ፤
የእኔ አማካሪና ካህን ሁንልኝ ፤ በዓመት ዐሥር
ብር እንዲሁም ልብስና ምግብ እሰጥሃለሁ"

17፥6 ፦ መሣ 21፥25 ።

ስመድረስ በጕዞ ላይ ነን፤ ወደ ቤቱ ወስዶ
የሚያሳድረን እስከ አሁን አላገኘንም፤ 19 እኛ
ግን ለአህዮቻችን ገፈራና ገለባ፥ ለቍባቴና
ለእኔ እንዲሁም ለአገልጋዩ እንጀራና የወይን
ጠጅ አለን፤ የሚያስፈልገንን ሁሉ ይዘናል።”

20 ሽማግሌውም “ሰላም ከእናንተ ጋር
ይሁን! እነሆ ወደ ቤቴ ግቡ፤ እኔ ማደሪያች
ሁን አዘጋጅላችኋለሁ፤ በዚህ አደባባይ ላይ
ማደር አይገባችሁም” አለ። 21 ስለዚህ ወደ
ቤት ወስዳቸውና ለአህዮቻቸው ምግብ ሰጠ፤
እንግዶቹም እግራቸውን ታጥበው ራታቸውን
በሉ።

22 እየተደሰቱ ሳለም ከከተማይቱ የመጡ የግ
ብረ ሥጋ ሥርዓት ስዋጮች በድንገት ቤቱን
ከበው በሩን መደብደብ ጀመሩ፤ ሽማግሌው
ንም “ያንን ወደ ቤትህ የገባውን ሰው አውጣ
ልን! ከእርሱም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እና
ደርጋለን!” አሉት።

23 ሽማግሌው ግን ወደ ውጭ ወጥቶ እን
ዲህ አላቸው፥ “አይሆንም ወዳጆቼ ሆይ!
እባካችሁ ይህን የመሰለ አስከፊ ነገር አታድ
ርጉ፤ ይህ ሰው የእኔ እንግዳ ነው፤ 24 እነሆ
የሰውየው ቍባትና ድንግል የሆነች የእኔም
ሴት ልጅ በዚህ አሉ፤ እነርሱን ላውጣላች
ሁና ወስዳችሁ የፈለጋችሁትን አድርጉባቸው፤
በዚህ ሰው ላይ ግን ይህን የመሰለ አስከፊ
ተግባር አትፈጽሙበት።” 25 ሰዎቹ ግን አልሰ
ሙትም፤ ስለዚህ ሌዋዊው ቍባቱን ወደ
ውጭ አውጥቶ ሰጣቸው፤ ሌሊቱንም ሙሉ
በእርስዋ ላይ ተራ በተራ በማመንዘር መጫ
ወቻ አደረጉዋት አደሩ፤ ሲነጋጋ ግን እንድት
ሄድ ፈቀዱላት።

26 ጠዋትም ጎሕ ሲቀድ ያች ሴት መጥታ
ባልዋ ባደረበት በሽማግሌው ቤት በር አጠገብ
ወደቀች፤ ፀሐይ እስከትወጣም ድረስ በዚያ
ነበረች፤ 27 በዚያም ጠዋት ባልየው ጕዞውን
ለመቀጠል በሩን ሲከፍት ቍባቱ እጅዋን ወደ
በሩ እንደዘረጋች በቤቱ ፊት ለፊት ወድቃ
አገኛትና፥ 28 “ተነሺ እንሂድ!” አላት፤ ነገር
ግን ምንም መልስ አላገኘም፤ ከዚህ በኋላ
ሬሳዋን በአህያ ላይ ጭኖ ወደ ቤቱ ጕዞውን
ቀጠለ፤ 29 እዚያም በደረሰ ጊዜ ወደ ቤቱ
ገባ፤ ቢለዋም አንሥቶ የቍባቱን ሬሳ ዐሥራ
ሁለት ቦታ ቈራረጠው፤ ስዐሥራ ሁለቱ የእስ
ራኤል ነገዶች ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ
ቍራጭ ላከ፤ 30 ያንንም ያየ ሁሉ “ይህን
የመሰለ ነገር ከቶ ሰምተን አናውቅም! እስራ
ኤላውያን ከግብጽ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ
ይህን የመሰለ ነገር ተደርጎ አያውቅም፤ ስለ
ዚህ ጕዳይ አንድ ነገር ማድረግ አለብን፤
ታዲያ ምን ሊሆን ይችላል?” አሉ።

## ምዕራፍ 20

### የእስራኤል ሕዝብ ለጦርነት መዘጋጀት

1 ከሰሜን እስከ ደቡብ፥ ማለትም ከዳን እስከ
ቤርሳቤህ እንዲሁም በስተምሥራቅ በገለዓድ
ምድር ያሉት የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ለጦር
ነት ተዘጋጁ፤ በአንድነትም ሆነው በምጽጳ በእ
ግዚአብሔር ፊት ተሰበሰቡ፤ 2 ከእነዚህ ከተሰበ
ሰቡት የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የእስራኤል
የነገድ አለቆች ነበሩ፤ እግረኛ ወታደሮች ብቻ
አራት መቶ ሺ ነበሩ፤ 3 በዚያን ጊዜ የብንያም
ሕዝብ እስራኤላውያን በሙሉ በምጽጳ መሰብሰ
ባቸውን ሰሙ።

እስራኤላውያንም “ይህ ወንጀል የተፈጸ
መው እንዴት እንደሆነ ንገሩን” አሉ፤
4 ቍባቱ የተገደለችበት ያ ሌዋዊ እንዲህ ሲል
መለሰ፥ “እኔና ቍባቴ ሌሊቱን ለማሳለፍ በብን
ያም ግዛት ወደምትገኘው ወደ ጊብዓ ሄድን፤
5 የጊብዓ ሰዎች በእኔ ላይ አደጋ ለመጣል መጥ
ተው በሌሊት ቤቱን ከበቡት፤ በመጀመሪያ
እኔን ለመግደል አስበው ነበር፤ በኋላ ግን በቍ
ባቴ ላይ ተረባርበው ስላመነዘሩባት ሞተች፤
6 ሬሳውንም ወስጄ ከቈራረጥሁት በኋላ ስዐሥራ
ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ለእያንዳንዳቸው አን
ዳንድ ቍራጭ ላክሁ፤ ምክንያቱም እነዚህ
ሕዝብ ሥነ ምግባር የጐደለው አስከፊ ነገር
በመካከላችን አድርገዋል፤ 7 እዚህ ያላችሁት
ሁሉ እስራኤላውያን ናችሁ! ታዲያ ስለዚህ
ጕዳይ ምን ማድረግ የሚገባን ይመስላችኋል?”

8 ሕዝቡም ሁሉ በአንድነት ቆመው እንዲህ
አሉ፥ “ከእኛ መካከል በድንኳንም ሆነ በቤት
ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው ወደ ቤቱ አይ
መለስም፤ 9 የምናደርገውም ይህ ነው፤ ዕጣ
በመጣል በጊብዓ ላይ አደጋ የሚጥሉ ሰዎችን
እንመርጣለን፤ 10 ከእስራኤል ሕዝብ አንድ
ዐሥረኛው ለሚዘምተው ሠራዊት ምግብ ያዘጋ
ጃል፤ የቀሩት ግን ዘምተው ይህን የመሰለ ሥነ
ምግባር የጐደለው አስከፊ በደል ስለፈጸሙ የጊ
ብዓን ሕዝብ ይቀጣሉ።” 11 ስለዚህም የእስራ
ኤል ሰዎች ሁሉ በከተማይቱ ላይ አደጋ ለመ
ጣል ዐቅደው በአንድነት ተሰበሰቡ።

12 የእስራኤል ነገዶች በመላው በብንያም
ግዛት ተዘዋውረው እንዲህ የሚል ቃል የሚናገ
ሩትን መልእክተኞች ላኩ፥ “ይህ የፈጸማች
ሁት ወንጀል ምንድን ነው? 13 እነርሱን ገድ
ለን ይህን ክፉ ነገር ከእስራኤል እናስወግድ
ዘንድ እነዚያን በጊብዓ ያሉትን ሥርዓት ስዋ
ጮች አሳልፋችሁ ስጡን።” የብንያም ሕዝብ
ግን የቀሩት እስራኤላውያን የነገሩአቸውን ነገር
አልተቀበሉም፤ 14 እንዲያውም እነርሱን ለመ
ውጋት ከብንያም ከተሞች ሁሉ ተጠራርተው

19፥22-24 ፦ ዘፍ. 19፥5-8 ። 19፥29 ፦ 1ሳሙ. 11፥7 ።

ወደ ጊብዓ መጡ ፤ 15-16 በዚያኑ ቀን ከየከተማ
ዎቻቸው የመጡ ሃያ ስድስት ሺ ወታደሮችን
አሰለፉ ፤ ከዚህም በቀር የጊብዓ ነዋሪዎች በተ
ለየ ሁኔታ የተመረጡና ግራኞች የሆኑ ሰባት
መቶ ሰዎች ሰበሰቡ ፤ ከእነርሱ እያንዳንዱ በወን
ጭፍ ድንጋይ ሲወረውር ሌላው ቀርቶ ጠጕር
የማይስት ነበር ፤ 17 እስራኤላውያን የብንያምን
ነገድ ሳይጨምሩ ብዛቱ አራት መቶ ሺ የሆነ
የሠለጠነ ሠራዊት አሰለፉ ።

### በብንያማውያን ላይ
### የተደረገ ጦርነት

18 እስራኤላውያን በቤትኤል ወዳለው የእም
ልኮ ስፍራ ሄደው በዚያ "በብንያማውያን ላይ
መጀመሪያ አደጋ መጣል የሚገባው የትኛው
ነገድ ነው?" ሲሉ እግዚአብሔርን ጠየቁ ።
እግዚአብሔርም "የይሁዳ ነገድ አስቀድሞ
ይዝመት" አላቸው ።
19 ስለዚህ በማግሥቱ ጠዋት ጕዞ ጀመሩ ፤
በጊብዓ ከተማ አጠገብም ሰፈሩ ፤ 20 በብንያም
ሠራዊት ላይ አደጋ ለመጣል ሄዱ ፤ ወታደሮቻ
ቸውንም በከተማይቱ ትይዩ አሰለፉ ፤ 21 የብን
ያም ሠራዊት ከከተማይቱ ወጥቶ ቀኑ ከመም
ሸቱ በፊት ሃያ ሁለት ሺ የእስራኤላውያንን
ወታደሮች ገደለ ፤ 22-23 እስራኤላውያንም ወደ
እምልኮው ስፍራ ሄደው እስከ ምሽት ድረስ
በእግዚአብሔር ፊት አለቀሱ ፤ "ወንድሞቻችን
በሆኑት ብንያማውያን ላይ አደጋ ለመጣል እን
ደገና እንዝመትን?" ሲሉም ጠየቁት ።
እግዚአብሔርም "አዎ ዝመቱ" አላቸው ።
የእስራኤላውያንም ሠራዊት እንደገና በመበረ
ታታት ወታደሮቹን ከአንድ ቀን በፊት በነበሩ
በት ቦታ አሰለፉአቸው ። 24 ሁለተኛም ጊዜ
በብንያም ሠራዊት ላይ ዘመቱ ፤ 25 እንዲሁም
ብንያማውያን ለሁለተኛ ጊዜ ከጊብዓ ወጡ ፤
በዚህም ጊዜ ዐሥራ ስምንት ሺ የሠለጠኑ የእ
ስራኤላውያንን ወታደሮች ገደሉ ፤ 26 ከዚህም
በኋላ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ወደ ቤትኤል
ሄደው አለቀሱ ፤ በዚያም ምንም ሳይበሉ
እስከ ምሽት በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጠው
ቆዩ ፤ ለደኅንነት የሚሆነውን የኅብረት መሥ
ዋዕትና ሌላም የሚቃጠል መሥዋዕት አቀ
ረቡ ፤ ይህን ሁሉ ያደረጉት በእግዚአብሔር
ፊት ነበር ፤ 27-28 በዚያን ዘመን የእግዚአብ
ሔር የቃል ኪዳን ታቦት በቤትኤል ነበር ፤
የአሮን ልጅ አልዓዛር የወለደው ፊንሐስ
የቃል ኪዳኑ ታቦት ጠባቂ ነበር ፤ ሕዝቡም
"ወንድሞቻችን የሆኑትን ብንያማውያንን ሰመ
ውጋት እንደገና እንዝመትን ወይስ እንተ
ወው?" ሲሉ እግዚአብሔርን ጠየቁ ።
እግዚአብሔርም "ሂዱና ተዋጉ! ነገ እኔ
በእነርሱ ላይ ድልን እንድትቀዳጁ አደርጋለሁ"
አላቸው ።

29 ስለዚህ እስራኤላውያን ጥቂት ወታደሮ
ችን በጊብዓ ዙሪያ እንዲሸምቁ አደረጉ ፤
30 ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሁሉ በሦስተኛው
ቀን በብንያም ሠራዊት ላይ ዘመቱ ፤ ወታደሮ
ቻቸውንም በጊብዓ ትይዩ አሰለፉአቸው ።
31 ብንያማውያኑንም ለመዋጋት ወጡ ፤ እየተ
መሩም ከከተማይቱ ራቁ ፤ ከዚህ በፊት እንዳ
ደረጉትም ገላጣ በሆነው አገር ወደ ቤትኤ
ልና ወደ ጊብዓ በሚወስዱት መንገዶች ላይ
ሠላሳ የሚሆኑ እስራኤላውያንን ገደሉ ፤
32 ብንያማውያንም "ልክ ከዚህ በፊት እንዳደ
ረግነው ፈጀናቸው!" አሉ ።
ነገር ግን እስራኤላውያን ወደ ኋላ በማፈግ
ፈግ ከከተማው አርቀው ወደ መንገዶቹ ለማስገ
ባት ዐቅደው ነበር ። 33 ስለዚህ ዋናው የእስራ
ኤል ሠራዊት ወደ ኋላ አፈግፍጎ በባዓልታማር
ተሰባስበው በተሰለፉ ጊዜ በጊብዓ ዙሪያ ያሉት
ሰዎች በከተማይቱ ዙሪያ ካለው ድንጋያማ
አገር ከሸመቁበት ስፍራ ድንገት ብቅ አሉ ፤
34 ከእስራኤል በልዩ ሁኔታ የተመረጡት ዐሥር
ሺ ሰዎች በጊብዓ ላይ አደጋ ጣሉ ፤ ውጊያውም
ከባድ ሆነ ፤ ይህ ሁሉ ሲሆን ብንያማውያን በቅ
ርብ ጊዜ እንደሚደመሰሱ ገና አልተገነዘቡም
ነበር ። 35 እግዚአብሔርም እስራኤላውያን በብን
ያማውያን ላይ ድልን እንዲቀዳጁ አደረገ ፤ እስ
ራኤላውያንም በዚያን ቀን ከብንያም ወገን ሃያ
አምስት ሺ አንድ መቶ ወታደሮችን ገደሉ ፤
36 በዚህም ጊዜ ብንያማውያን መሸነፋቸውን
ተገነዘቡ ።
በጊብዓ ዙሪያ በነበራቸው ሽምቅ ጦር ስለ
ተማመኑ ዋናው የእስራኤላውያን ሠራዊት
ብንያማውያን ያሸነፉት በመምሰል ወደ
ኋላው አፈገፈገ ። 37 ድብቁም ጦር በፍጥነት
ተንደርድሮ ወደ ጊብዓ ገባ ፤ በከተማይቱም
ውስጥ ተሰራጭቶ በዚያ ያገኘውን ሁሉ
ገደለ ፤ 38 ዋናው የእስራኤላውያን ሠራዊትና
ሽምቁ ጦር የሚግባቡበትን ምልክት ቀደም
ብለው አዘጋጅተው ነበር ፤ ታላቅ የጢስ
ደመና ከከተማይቱ ሲወጣ በሚያዩበት ጊዜ ፥
39 በጦር ሜዳ የነበሩት እስራኤላውያን የመ
ልሶ ማጥቃት እርምጃ ይወስዳሉ ፤ እስከ
አሁን ብንያማውያን ሠላሳ እስራኤላውያንን
በመግደላቸው "ከዚህ በፊት እንዳደረግነው
አሁንም ፈጀናቸው!" እያሉ ይደነፉ ነበር ።
40 ከዚህም በኋላ ምልክቱ ታየ ፤ ይኸውም
ጢሱ እንደ ደመና ሆኖ እየተትጐለጐለ ወደ
ላይ ይወጣ ነበር ፤ ብንያማውያንም ወደኋላ
ቸው ሲመለከቱ ከተማይቱ በሙሉ በእሳት
ተያይዛ ነበልባሉ ወደ ላይ ሲወጣ አዩ ፤
41 እስራኤላውያንም የመልሶ ማጥቃት እርምጃ
ቸውን በወሰዱ ጊዜ ፥ ጨርሰው መደምሰሳቸ
ውን ስለተገነዘቡ ብንያማውያን በፍርሃት ተሸ
በሩ ፤ 42 ከእስራኤላውያንም ፊት አፈግፍገው

ገሳጣ ወደሆነው ምድር ሸሹ፤ ነገር ግን
ማምለጥ አልቻሉም፤ በዋናው ሠራዊትና
አሁን ከከተማው ውስጥ በመውጣት ላይ
ባሉት ወታደሮች መካከል ተይዘው ተደመ
ሰሱ። 43 እስራኤላውያን ጠላትን ከብበው በጊ
ብዓ በስተ ምሥራቅ እስከሚገኘው ስፍራ
ድረስ ተከታትለው አሳደዱአቸው፤ በመንገ
ድም ሳሉ ብዙዎችን ገደሉ። 44 ከብንያማው
ያን ምርጥ ወታደሮች ዐሥራ ስምንት ሺ ተገ
ደሉ፤ 45 የቀሩት ወደ ኋላቸው ተመልሰው
ገሳጣ የሆነውን ምድር በማቋረጥ የሪሞን
አለት ተብሎ ወደሚጠራው ስፍራ ወጡ፤
ከእነርሱም አምስት ሺው በመንገድ አለቁ፤
ከዚያ የተረፉትንም እስራኤላውያን እስከ ጊድ
ዖም በማሳደድ ሁለቱን ሺ ገደሉ። 46 በዚያን
ቀን በአጠቃላይ የተገደሉት ብንያማውያን ሃያ
አምስት ሺ ሲሆኑ ሁሉም ምርጥ ጦረኞች
ነበሩ።

47 ነገር ግን ገሳጣ የሆነውን ምድር አል
ፈው የሪሞን አለት ተብሎ ወደሚጠራው
ስፍራ በመሄድ ለማምለጥ የቻሉት ስድስት
መቶ ሰዎች ብቻ ነበሩ። እነርሱም በዚያ
አራት ወር ቆዩ። 48 እስራኤላውያን ወደ ኋላ
ተመልሰው በቀሩት ብንያማውያን ላይ አደጋ
በመጣል ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆችንና
እንዲሁም እንስሳትን ጭምር በሙሉ ገደሉ፤
በዚያ አካባቢ ያሉትን ከተሞች ሁሉ በእሳት
አቃጠሉ።

## ምዕራፍ 21

### ለብንያም ነገድ ተወላጆች
### የተመደቡ ሚስቶች

1 እስራኤላውያን በምጽጳ በተሰበሰቡ ጊዜ
"ከእኛ መካከል ማንም ሰው ሴት ልጁን ለብ
ንያማዊ መዳር የለበትም" በማለት ለእግዚአብ
ሔር ስእለት በማድረግ ተማማሉ። 2-3 ስለዚ
ህም የእስራኤል ሕዝብ ወደ ቤትኤል ሄደው
በዚያ እስከ ምሽት ድረስ በእግዚአብሔር ፊት
ተቀምጠው ቆዩ፤ "የእስራኤል አምላክ የሆ
ንህ እግዚአብሔር ሆይ! ይህ ነገር የተደረገው
ለምንድን ነው? የብንያም ነገድ ከእስራኤል
መካከል ሊጠፋስ የተቃረበው ለምንድን
ነው?" እያሉም ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ
ምርር ብለው አለቀሱ። 4 በማግሥቱም ጠዋት
በማለዳ ሕዝቡ በዚያ መሠዊያ ሠሩ፤ ለደኅን
ነት የሚሆን የኅብረት መሥዋዕትና የሚቃ
ጠል መሥዋዕትም አቀረቡ፤ 5 "በምጽጳ በእግ
ዚአብሔር ፊት ስንሰበሰብ ወደዚያ ያልመጣ
ከእስራኤል ነገዶች መካከል አንድ ወገን
እንኳ ይገኛልን?" ብለውም ጠየቁ፤ ይህንንም
ያሉበት ምክንያት ወደ ምጽጳ ያልሄደ ማንም
ሰው ቢገኝ በሞት ለመቅጣት ተማምለው ስለ
ነበር ነው። 6 የእስራኤል ሕዝብ ወንድሞቻ
ቸው ለሆኑት ለብንያማውያን አዝነው ስለነበር
"ዛሬ እስራኤል ከነገዶቹ አንዱን አጥቶአል፤
7 ታዲያ ከሞት የተረፉት ብንያማውያን
ሚስት ያገኙ ዘንድ ምን እናድርግ? ምክንያ
ቱም ከሴቶች ልጆቻችን ማንኛይቱንም ለእነ
ርሱ እንዳንድር በመሐላ ቃል ገብተናል"
አሉ።

8 ከእስራኤል ነገዶች መካከል በምጽጳ በተ
ደረገው ስብሰባ ላይ ያልተገኘ ወገን እንዳለ
በጠየቁ ጊዜ በገለዓድ ከሚኖሩት ከያቤሽ
ወገን አንድም ሰው እንዳልሄደ ተረዱ። 9 የሠ
ራዊቱ ስም አንድ በአንድ በሚጠራበት ጊዜ
ከያቤሽ ወገን "አለሁ" ብሎ መልስ የሰጠ
ማንም አልነበረም፤ 10-11 ስለዚህ ጉባኤው
"ወደ ያቤሽ ሄዳችሁ ሴቶችንና ልጆችን
ጭምር ሁሉንም ግደሉ፤ ወንዶችንና ድንግል
ያልሆኑ ሴቶችን በሙሉ ግደሉ" የሚል
መመሪያ በመስጠት ከመካከላቸው ምርጥ የሆ
ኑትን ዐሥራ ሁለት ሺ ሰዎችን ላኩ። 12 በዚ
ህም ዐይነት በያቤሽ ካሉት ሕዝብ መካከል
አራት መቶ ድንግል የሆኑ ወጣት ልጃገረዶ
ችን አገኙ፤ ስለዚህም እነርሱን በከነዓን
ምድር በሴሎ ወደሚገኘው ሰፈር ይዘው
መጡ።

13 ከዚህ በኋላ መላው ጉባኤ የሪሞን አለት
ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ወደነበሩት ብንያማ
ውያን መልእክት ልከው ጦርነቱ እንዲቆም ተስ
ማሙ፤ 14 ብንያማውያንም ተመልሰው መጡ፤
ሌሎቹም እስራኤላውያን ከሞት በመትረፍ ከያ
ቤሽ ተማርከው የመጡትን ልጃገረዶች ሰጡአ
ቸው፤ ነገር ግን ቊጥራቸው ተመጣጣኝ ሆኖ
አልተገኘም።

15 ሕዝቡ ስለ ብንያማውያን እጅግ አዘኑ፤
ምክንያቱም እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ነገ
ዶች መካከል ያሰው አንድነት እንዲቋረጥ አድ
ርጎ ስለነበር ነው። 16 ስለዚህም የጉባኤው መሪ
ዎች እንዲህ አሉ፤ "በብንያም ነገድ ከእንግ
ዲህ ሴቶች አልተገኙም፤ ታዲያ ከሞት የተረ
ፉት ወንዶች ሚስት ማግኘት ይችሉ ዘንድ
ምን እናድርግ? 17 እስራኤል ከዐሥራ ሁለቱ
ነገዶች አንዱን ማጣት የለበትም፤ የብንያም
ነገድ እንዳይጠፋ አንድ ዘዴ መፈለግ አለብን፤
18 ይሁን እንጂ ሴቶች ልጆቻችንን ያገቡ ዘንድ
ልንፈቅድላቸው አንችልም፤ ምክንያቱም ከእኛ
መካከል ማንም ሰው ሴት ልጁን ለብንያማዊ
ቢድር የተረገመ እንደሚሆን በመሐላ ቃል ገብ
ተናል።"

19 ከዚህ በኋላ "በየዓመቱ በሴሎ ለእግዚአብ
ሔር የሚዘጋጀው በዓል እነሆ ቀርቦአል" በማለ
ትም አሰቡ፤ ሴሎ ከቤትኤል በስተ ሰሜን፥ ከለ
ቦና በስተ ደቡብ፥ በቤትኤልና በሴኬም መካ
ከል ካለው መንገድ በስተ ምሥራቅ ነበረች።

እለቻቸው፥ “እንግዲህ ወደየቤታችሁ ተመለ
ሱና ከእናቶቻችሁ ጋር ኑሩ፤ ለእኔና ለሟቾቹ
ባሎቻችሁ መልካም ነገር እንዳደረጋችሁ፥ እን
ዲሁም እግዚአብሔር ለእናንተ መልካም ነገር
ያድርግላችሁ፤ 9 እያንዳንዳችሁ እንደገና ባል
አግብታችሁ ትዳር እንድትመሠርቱ እግዚአብ
ሔር ይርዳችሁ።”
ከዚህ በኋላ ናዖሚ ለመሰናበት ሳመቻቸው፤
እነርሱ ግን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያለ
ቀሱ፥ 10 “አይሆንም! እኛ ከአንቺ ጋር ወደ
ወገኖችሽ እንሄዳለን እንጂ ተለይተንሽ እንቀ
ርም” አሉአት።
11 ናዖሚም እንዲህ አለቻቸው፥ “ልጆቼ
ሆይ! እባካችሁ ተመለሱ፤ ከእኔ ጋር ለመሄድ
የምትፈልጉት ለምንድን ነው? ለእናንተ ባሎች
የሚሆኑ ልጆች እንደገና መውለድ የምችል
ይመስላችኋልን? 12 ወደየቤታችሁ ተመለሱ፤
እኔ ሌላ ባል እንዳላገባ ዕድሜዬ አይፈቅድል
ኝም፤ ለመሆኑ ለማግባት ተስፋ ቢኖረኝና ዛሬ
ውኑ አግብቼ ልጆች ብወልድስ፥ 13 እነርሱ ለአ
ካለ መጠን እስኪደርሱ መጠበቅ ትችላላችሁን?
በዚህስ ምክንያት ሌሎች ባሎች ሳታገቡ ትቀራ
ላችሁን? ልጆቼ ሆይ! ይህ ከቶ የማይቻል መሆ
ኑን ታውቃላችሁ፤ እኔን እግዚአብሔር ተቆጥ
ቶኛል፤ በእናንተም ላይ በደረሰው ነገር በጣም
እዝናለሁ።”
14 እነርሱም እንደገና ማልቀስ ጀመሩ፤
በዚህ ጊዜ ዖርፋ ዐማቷን ስማ በመሰናበት ወደ
ቤት ተመለሰች፤ ሩት ግን ከሀማቷ ላለመለየት
ወሰነች። 15 ስለዚህ ናዖሚ “ሩት ሆይ! የባልሽ
ወንድም ሚስት ወደ ወገኖችዋና ወደ ባዕዳን
አማልክትዋ ተመልሳለች፤ እንግዲህ አንቺም
ከእርስዋ ጋር ብትመለሺ ይሻላል” አለቻት።
16 ሩትም እንዲህ አለቻት፥ “ተለይቼሽ እን
ድመለስ አታስገድጂኝ፤ አብሬሽ እንድሄድ
ፍቀጂልኝ፤ አንቺ ወደምትሄጂበት ሁሉ እሄዳ
ለሁ፤ አንቺ በምትኖሪበት እኖራለሁ፤ ከአሁን
ጀምሮ ሕዝብሽ ሕዝቤ ነው፤ አምላክሽም አም
ላኬ ነው፤ 17 በምትሞቺበት እሞታለሁ፤ በም
ትቀበሪበትም እቀበራለሁ፤ ከሞት በቀር ከአንቺ
የሚለየኝ የለም፤ ከአንቺ ለመለየት ባስብ እግዚ
አብሔር ይፍረድብኝ!”
18 ሩት ከእርስዋ ጋር ለመሄድ ቊርጥ አሳብ
ማድረጓን በተረዳች ጊዜ፥ ናዖሚ ሌላ ነገር አል
ተናገረችም።
19 ስለዚህ ሁለቱም አብረው ወደ ቤተል
ሔም ተጓዙ፤ ቤተልሔም ሲደርሱም የከተ
ማው ሰዎች ሁሉ ተገረሙ፤ እዚያም ያሉ
ሴቶች በመደነቅ “በእርግጥ ይህች ናዖሚ
ናትን?” አሉ።

20 እርስዋም እንዲህ አለች፥ “ሁሉን የሚ
ችል አምላክ ሕይወቴን መራራ ስላደረገው
‘ማራ’* በሉኝ እንጂ ‘ናዖሚ’ ብላችሁ አትጥ
ሩኝ፤ 21 ከዚህ አገር በሄድሁ ጊዜ ብዙ ነገር
ነበረኝ፤ እግዚአብሔር ግን ባዶ እጄን መልሶ
ኛል፤ ታዲያ ሁሉን የሚችል አምላክ ሲፈርድ
ብኝና ይህን ሁሉ ችግር ሲያደርስብኝ ‘ናዖሚ’
ብላችሁ ለምን ትጠሩኛላችሁ?”
22 እንግዲህ ናዖሚ ከሞአባዊት ምራትዋ
ከሩት ጋር ከሞአብ አገር የተመለሰችው በዚህ
ሁኔታ ነበር፤ እነርሱ ቤተልሔም በደረሱ ጊዜ
የገብስ መከር የሚሰበሰብበት ወቅት መጀመሩ
ነበር።

## ምዕራፍ 2

### ሩት በቦዔዝ እርሻ ልትቃርም ተሠማራች

1 ናዖሚ ሀብታምና ታዋቂ የሆነ ቦዔዝ የሚ
ባል ወገን ነበራት፤ ይህም ሰው የባልዋ የኤሊ
ሜሌክ የቅርብ ዘመድ ነበር፤ 2 ከዕለታት አንድ
ቀን ሩት ናዖሚን “ከእጫጆች እጅ የወዳደቀ
ውን እሀል ለመቃረም መከር ወደሚሰበሰብባ
ቸው እርሻዎች ልሂድ፤ እንድቃርም የሚፈቅ
ድልኝ ሰው እንደማገኝ እተማመናለሁ” አለ
ቻት፤ ናዖሚም “እሺ ልጄ፥ ሂጂ!” አለቻት።
3 ሩትም ወደ እርሻዎች ሄደች፤ ከአጫጆች
ኋላ እየተከተለችም ከእጃቸው የወዳደቀውን
እሀል ትቃርም ጀመር፤ እንደ አጋጣሚ የምት
ቃርምበት ቦታ የኤሊሜሌክ የቅርብ ዘመድ የሆ
ነው የቦዔዝ እርሻ ነበር። 4 ከጥቂት ጊዜ በኋላ
ቦዔዝ ራሱ ከቤተልሔም ተነሥቶ ወደ እርሻው
መጣ፤ አጫጆቹንም “እንደምን ዋላችሁ! እግ
ዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!” አላቸው።
እነርሱም “እግዚአብሔር አንተንም ይባር
ክህ!” አሉት።
5 ከዚህ በኋላ ቦዔዝ የአጫጆቹ ኀላፊ የሆነ
ውን ሰው “ያቺ ወጣት ሴት ማን ናት?” ሲል
ጠየቀው።
6 ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰ፥ “እርስዋ
ናዖሚን ተከትላ ከሞአብ አገር የመጣች እንግዳ
ናት፤ 7 አጫጆችን ተከትላ ከእጃቸው የወዳደቀ
ውን እሀል ለመቃረም እንድፈቅድላት ጠየቀ
ችኝ፤ ከጠዋት ጀምራ እስከ አሁን ስትቃርም
ነበር፤ አሁን ግን ትንሽ ዕረፍት ለማድረግ ወደ
ዳስ ተጠግታለች።”
8 በዚህ ጊዜ ቦዔዝ ሩትን እንዲህ አላት፥
“አንቺ ልጅ፥ ስሚ ልምከርሽ፤ እዚህ ያሉትን
ሴቶች ሠራተኞች ተከትለሽ ቃርሚ እንጂ ይህን
እርሻ ትተሽ ለመቃረም ወደ ሌላ ቦታ አት
ሂጂ። 9 እነርሱ የት እንደሚያጭዱ በመጠባበቅ
እየተመለከትሽ ከእነርሱ ጋር ሁኚ፤ ወንዶች

2* 1፥20 ማራ፦ በዕብራይስጥ “መራራ ወይም ሬት” ማለት ነው።
2፥2፦ ዘሌ. 19፥9-10፤ ዘዳ. 24፥19።

ሠራተኞቹ እንዳያስቸግሩሽ አስጠንቅቄአቸዋ
ለሁ ፤ ውሃም በሚጠማሽ ጊዜ እነርሱ ሞልተው
ወዳስቀመጡአቸው እንስራዎች እየሄድሽ ቀድ
ተሽ ጠጪ ።”
10 ሩትም ግንባርዋ መሬት እስኪነካ ራስዋን
ዝቅ አድርጋ እጅ ነሣችና ቦዔዝን “ይህን ያህል
በመጨነቅ ለእኔ ማሰብህ ስለምንድን ነው? እኔ
ባይተዋር ሆኜ ሳለሁ ይህን ያህል ቸርነት ለማ
ድረግ ምን አሳሰበህ?” አለችው ።
11 ቦዔዝም እንዲህ ሲል መለሰላት ፦ “ባልሽ
ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ለዐማትሽ ያደረግሽላትን
መልካም ነገር ሁሉ ሰምቻለሁ ፤ አባትሽንና
እናትሽን ፥ የትውልድ አገርሽንም እንደተው
ሽና ከዚህ በፊት በማታውቂው ሕዝብ መካከል
ለመኖር ወደዚህ እንደመጣሽ ተረድቻለሁ ።
12 ላደረግሽው መልካም ነገር ሁሉ እግዚአብ
ሔር ዋጋሽን ይክፈልሽ ፤ ጥበቃውን ፈልገሽ የእ
ስራኤል አምላክ ወደሆነው እግዚአብሔር መጥ
ተሻል ፤ ስለዚህ እርሱ ዋጋሽን ሙሉ በሙሉ
ይክፈልሽ ።”
13 ሩትም “ጌታዬ! ታላቅ ቸርነት አሳይተኸ
ኛል ፤ ምንም እንኳ እኔ ከአገልጋዮችህ እንደ
አንዲትዋ ልቈጠር የማይገባኝ ብሆንም መል
ካም ነገር በመናገር አጽናንተኸኛል” አለ
ችው ።
14 በምሳ ሰዓት ቦዔዝ ሩትን “ነይ ወደ ገበ
ታው ቅረቢ ፤ በወጡም እያጠቀስሽ እንጀራ
ብዪ” አላት ። እርስዋም ከአጫጆቹ ጋር ተቀመ
ጠች ፤ ቦዔዝም የተጠበሰ እሸት ሰጣት ፤ እስኪበ
ቃት ድረስ በላች ፤ ምግብም ተርፏት ነበር ።
15 እንደገናም ልትቃርም ስትነሣ ቦዔዝ ጐልማ
ሶቹን እንዲህ አላቸው ፦ “በነዶዎች መካከል
ያለውንም እንኳ ቢሆን ትቃርም ፤ በጭራሽ
አትከልክሉአት ፤ 16 እንዲያውም ከታሰረው ነዶ
እየመዘዛችሁ ተዉላትና ትቃርም ።”
17 ሩትም እስከ ምሽት ድረስ ከእርሻው
እህል ስትቃርም ዋለች ፤ በወቃችውም ጊዜ
ሀሥር ኪሎ ያህል ሆነ ።
18 እህሉንም ተሸክማ ወደ ከተማ ተመለ
ሰች ፤ ምን ያህል እንደሰበሰበችም ለናዖሚ አሳየ
ቻት ፤ ከምሳዋ ተርፎአት የነበረውንም ምግብ
ሰጠቻት ። 19 ናዖሚም “ይህን ሁሉ ከየት ሰበሰ
ብሽው? ስትቃርሚ የዋልሽበት እርሻ የማን
ነው? ይህን መልካም ነገር ያደረገልሽን ሰው
እግዚአብሔር ይባርከው!” አለቻት ።
ሩትም “እኔ ስቃርም የዋልሁበት እርሻ ባለ
ቤት ቦዔዝ የሚባል ሰው ነው” ብላ ለናዖሚ
ነገረቻት ።
20 ናዖሚም “ለሕያዋንና ለሙታን የሰጠውን
ተስፋ የሚፈጽም አምላክ ቦዔዝን ይባርከው!”
አለች ፤ ቀጥላም “ያ ሰው እኮ የቅርብ ዘመዳ
ችን ነው! እንዲያውም ለእኛ ኑሮ የማሰብ ኀላ
ፊነት ካለባቸው ሰዎች አንዱ እርሱ ነው ።”
21 ከዚህ በኋላ ሩት “ከሁሉ የሚደንቀው ፥
መከሩን ሰብስበው እስከሚጨርሱ ድረስ ከአጫ
ጆቹ ሳልለይ በእርሱ እርሻ እንድቃርም መፍ
ቀዱ ነው” አለች ።
22 ናዖሚም “እውነት ነው ልጄ ፤ በቦዔዝ
እርሻ ካሉት ሴቶች ጋር ሆነሽ ብትቃርሚ ይሻ
ልሻል ፤ ወደ ሌላ ሰው እርሻ ብትሄጂ ግን ምና
ልባት ጐልማሶች ያስቸግሩሻል” አለቻት ።
23 ስለዚህ ሩት የገብሱና የስንዴው መከር ተሰብ
ስቦ እስኪያበቃ ድረስ ከእነርሱ ጋር ሆና መቃረ
ምዋን ቀጠለች ፤ ከዐማትዋም ሳትለይ አብራ
ተቀመጠች ።

## ምዕራፍ 3

### ሩት ባል አገኘች

1 ከዚህ በኋላ ናዖሚ ሩትን እንዲህ አለቻት ፦
“ኀጆ ወጥተሽ ትዳር እንድትይዢ ባል ብፈልግ
ልሽ የሚሻል ይመስለኛል ፤ 2 ስትቃርሚ አብረ
ውሽ የነበሩት ሴቶች የሚያገለግሉት ቦዔዝ የቅ
ርብ ዘመዳችን እንደሆነ ከዚህ በፊት ነግሬሻ
ለሁ ፤ እነሆ! እርሱ ዛሬ ማታ ገብሱ ይወቃል ፤
3 ስለዚህ ሰውነትሽን ታጠቢና ሽቶ ተቀቢ ፤
የክት ልብስሽንም ልበሺ ፤ ከዚህ በኋላ እርሱ
ገብሱን ወደሚወቃበት አውድማ ሂጂ ፤ ነገር
ግን ራት ቀርቦ እስከሚበላና እስከሚጠጣ ድረስ
በፊቱ አትታዪ ። 4 የት እንደሚተኛ ካረጋገጥሽ
በኋላ ፥ እንቅልፍ ሲወስደው ወደ እርሱ ቀረብ
በዪና ከግርጌው በኩል ልብሱን ገልጠሽ በእግሩ
አጠገብ ተኚ ፤ ስለ ጋብቻ ጉዳይ ምን ማድረግ
እንደሚገባሽ እርሱ ራሱ ይነግርሻል ።”
5 ሩትም “ያልሽውን ሁሉ አደርጋለሁ” አለ
ቻት ።
6 ስለዚህ ሩት ወደ አውድማው ሄዳ ልክ
ዐማትዋ እንደነገረቻት አደረገች ። 7 ቦዔዝ ከበ
ላና ከጠጣ በኋላ ደስ ብሎት ነበር ፤ ወደ ገብ
ሱም ክምር ሄዶ ጋደም አለና እንቀላፋ ፤
ሩትም በቀስታ ወደ እርሱ ተጠጋች ፤ ልብሱ
ንም ገለጥ አድርጋ በእግሩ አጠገብ ተኛች ።
8 ወደ እኩለ ሌሊት ገደማም ቦዔዝ ድንገት
ነቅቶ ሲገላበጥ አንዲት ሴት በአጠገቡ ተኝታ
በማግኘቱ ተደነቀ ፤ 9 “አንቺ ማን ነሽ?”
ብሎም ጠየቃት ።
እርስዋም “ጌታዬ ሆይ! እኔ ሩት ነኝ ፤
አንተ የቅርብ ዘመድ ስለሆንህ ለእኔ ኑሮ የማ
ሰብ ኀላፊነት አለብህ ፤ ስለዚህ የትዳር ጓደኛዬ
እንድትሆን እፈልጋለሁ” ስትል መለሰችለት ።
10 ቦዔዝም እንዲህ አላት ፦ “እግዚአብሔር
ይባርክሽ ፤ አሁን በምታደርጊው ነገር ከዚህ

2፥20 ፡- ዘሌ. 25፥25 ።

ወዲያው ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች ፤ 14 የጐረ
ቤትም ሴቶች ናዖሚን እንዲህ አሉአት ፥
"የሚጦርሽን የልጅ ልጅ ስለ ሰጠሽ እግዚአ
ብሔር የተመሰገነ ይሁን ፤ እግዚአብሔር
ይህን ልጅ በእስራኤል ዝነኛ ያድርገው ።
15 ምራትሽ በጣም ትወድሻለች ፤ ሰባት ልጆች
ከሚያደርጉልሽ የበለጠ አድርጋልሻለች ፤
አሁን ደግሞ ሕይወትሽን የሚያድስልሽና በእ
ርጅናሽ ወራት የሚጦርሽን ወንድ ልጅ ወል
ዳልሻለች ።"
16 ናዖሚም ይህን ሕፃን ልጅዋ አድርጋ በመ
ቀበል አቀፈችው ፤ ተከባክባም አሳደገችው ።
17 የጐረቤት ሴቶች ልጁን "ኢዮቤድ"
ብለው ስም አወጡለት ፤ "ለናዖሚ ወንድ ልጅ
ተወለደላት !" እያሉም ለሰው ሁሉ አወሩ ።
የንጉሥ ዳዊት አባት የሆነውን እሴይን የወ
ለደ ይኸው ኢዮቤድ ነው ።
18-22 ከፋሬስ እንሥቶ እስከ ዳዊት ያለው
የትውልድ ሐረግ የሚከተለው ነው ፤ ፋሬስ
ሔጽሮንን ወለደ ፤ ሔጽሮን አራምን ወለደ ፤
አራም ዐሚናዳብን ወለደ ፤ ዐሚናዳብ ነአሶንን
ወለደ ፤ ነአሶን ሳልሞንን ወለደ ፤ ሳልሞን ቦዔ
ዝን ወለደ ፤ ቦዔዝ ኢዮቤድን ወለደ ፤ ኢዮቤድ
እሴይን ወለደ ፤ እሴይም ዳዊትን ወለደ ።

# መጽሐፈ ሳሙኤል

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

*መጽሐፈ ሳሙኤል ክፍል አንድ ፥ እስራኤል ከመሳፍንት አገዛዝ ወደ ንጉሣዊ መንግሥት የተሸጋገረችበትን ሁኔታ ይገልጣል ፤ ይህ ለውጥ በእስራኤል ብሔር አቀፍ ሕይወት ውስጥ ሊካሄድ የቻለው አብዛኛውን በሦስት ሰዎች ምክንያት ነው ፤ እነርሱም ፦ አንደኛው ከመጨረሻዎቹ ታላላቅ መሳፍንት አንዱ የነበረው ሳሙኤል ሲሆን ፥ ሁለተኛው የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ የነበረው ሳኦል ነው ፤ ሦስተኛው ደግሞ ወደ ሥልጣን ከመውጣቱ በፊት የነበረው የመጀመሪያ ታሪኩ ከሳሙኤልና ከሳኦል ታሪክ ጋር የተጣመረው ዳዊት ነው ።*

*የዚህ መጽሐፍ ዋና መልእክት በብሉይ ኪዳን እንደሚገኙት እንደ ሌሎቹ የታሪክ መጻሕፍት ሁሉ ፥ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን በረከትንና የኑሮ መሳካትን እንደሚያስከትል ፥ ያለ መታዘዝም ውድቀትንና ጥፋትን እንደሚያመጣ ያሳያል ። ይህም እግዚአብሔር ለካህኑ ለዔሊ ፦ "እኔ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ ፤ የሚንቁኝንም አዋርዳለሁ" በማለት በተናገረው ቃል ግልጥ ሆኖ ይታያል (2 ፥ 30) ።*

*ይህ መጽሐፍ ስለ ንጉሣዊ መንግሥት አመሠራረት የነበረውን የተለያየ ስሜት ይገልጣል ፤ ቀደም ሲል የእስራኤል እውነተኛ ንጉሥ እንደሆነ የሚታወቀው ራሱ እግዚአብሔር ነበር ፤ ነገር ግን ዘግየት ብሎ ከሕዝቡ በተነሣው ጥያቄ መሠረት ፥ እግዚአብሔር ለእነርሱ ንጉሥ መረጠላቸው ። ያም ሆነ ይህ ዋናው ቁምነገር ፤ ንጉሡም ሆነ ፥ የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር የበላይነትና ፈራጅነት ሥር መገኘታቸው ነው (2 ፥ 7-10) ። ይህም በእግዚአብሔር ሕግ ሥር ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች የሰዎች መብት በትክክል መከበር እንዳለበት የሚያመለክት ነው ።*

---

## ምዕራፍ 1

### ሕልቃናና ቤተሰቡ በሴሎ

1 በኰረብታማው በኤፍሬም አገር ራማ ተብላ
በምትጠራ ትንሽ ከተማ የሚኖር ትውልዱ ከኤ
ፍሬም ነገድ የሆነ ፥ ሕልቃና ተብሎ የሚጠራ
አንድ ሰው ነበር ፤ የእርሱም አባት ይሮሐም
ተብሎ የሚጠራ የኤሊሁ ልጅ ሲሆን ፥ ከጹፍ
ጐሳ ክፍል የቶሑ ቤተሰብ ነበር ፤ 2 ሕልቃናም
ሐናና ፈኒና ተብለው የሚጠሩ ሁለት ሚስቶች
ነበሩት ፤ ፈኒና ልጆች ነበሩአት ፤ ሐና ግን አን
ድም ልጅ አልነበራትም ፤ 3 ሕልቃና በየዓመቱ
ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ለመስገድና መሥዋ
ዕት ለማቅረብ ከራማ ወደ ሴሎ ይሄድ ነበር ፤
በዚያም ዘመን ሖፍኒና ፊንሐስ ተብለው የሚጠ
ሩት የዔሊ ልጆች የእግዚአብሔር ካህናት ሆነው
በሴሎ ያገለግሉ ነበር ። 4 ሕልቃና መሥዋዕቱን
በሚያቀርብበትም ጊዜ ሁሉ ከመሥዋዕቱ ሥጋ
አንድ ድርሻ ለፈኒና ይሰጣል ፤ እንዲሁም ለወን
ዶችና ለሴቶች ልጆችዋ ለእያንዳንዳቸው አንዳ
ንድ ድርሻ ያድላል ፤ 5 ሐናን ይወዳት ስለነበር
እጥፍ ድርሻ ይሰጣት ነበር ፤ ቢሆንም እግዚአብ
ሔር ልጅ ነሥቶአት መኻን ነበረች ፤ 6 እግዚአብ
ሔርም ልጅ ስለነሣት ጣውንትዋ ፈኒና ሐናን